

## ኢትዮ ቴሌኮም የገጠመው የሲስተም ችግር ለሁለት ወራት እንደሚቆይ ገለፀ

አቶ አብዱራሂም አህመድ

በገፅ 4




# ሰንደቅ

ሰንደቅ 10ኛ ዓመት ቁጥር 483 ረቡዕ ታህሳስ 01 2007 ዋጋ 7 ብር

# “መድረክ በጠራው ሰልፍ ላይ እስከ 30ሺ ሰው ሊሳተፍ ይችላል”

በመስረከም አያሴው

በምርጫ 2002 የተስተዋሉ ጉድለቶች ሳይስተካከሉ የምርጫ ጊዜ ሰሌዳ መወጣቱን እና ወደ ምርጫ 2007 መገባቱን በመቃወም ሊያደርገው ባሰበው ሰላማዊ ሰልፍ ላይ እስከ 30ሺ ሰው ሊሳተፉ እንደሚችሉ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ (መድረክ) ገለፀ፡፡

የፓርቲው ምክትል ሊቀመንበርና የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ጥላሁን እንዳሻው እንደገለፁት በ2002 ዓ.ም የተካሄደው ሀገራዊ ምርጫ ደረጃው የወረደ እና ዴሞክራሲያዊነቱን ያልጠበቀ በመሆኑ ህዝቡ በነፃነት ምርጫ መርጧል በማያስብል መልኩ መጠናቀቁን ተከትሎ በወቅቱ ፓርቲው በምርጫው ውስጥ ጉድለቶች መኖራቸውን በማንሳት ከገዢው ፓርቲ ጋር ለመደራደር ተደጋጋሚ ጥያቄዎችን ቢያቀርብም እስከ አሁን ድረስ አዎንታዊ ምላሽ ማግኘት አልቻለም፡፡ ይህን ጥያቄ ለምርጫ ቦርድም ገልፆ እንደነበረ የገለፁት አቶ ጥላሁን፣ ይልቁንም የነበሩት ግድፈቶች ምንም አይነት እርምት ሳይደረግባቸው የምርጫ ጊዜ ሰሌዳን በማውጣት ወደ ምርጫ 2007 መኳዝ መምረጡንም ገልፀዋል፡፡ በመሆኑም ገዢው ፓርቲ ለጥያቄው አዎንታዊ ምላሽ አለመስጠቱን በመቃወም የፊታችን ታህሳስ 5 ቀን 2007 ዓ.ም ሰላማዊ ሰልፍ ለማካሄድ አስቧል፡፡ ሰላማዊ ሰልፉ መነሻውን ግንፍሌ ወንዝ ድልድይ በማድረግ በቀበና ወንዝ ድልድይ እና በባልደራስ በኩል በማድረግ መድረሻውን ወረዳ 8 ኳስ ሜዳ አድርጎ ከጠዋቱ 3 ሰዓት እስከ 7 ሰዓት ይካሄዳል፡፡

ሰላማዊ ሰልፉ የፓርቲው ብቻ ሳይሆን የህዝቡ በመሆኑ ህዝቡ በንቃት ከተሳተፈ ወደፊት የማይገፉበት እና ግቡንም የማይመታበት ሁኔታ እንደሌለ አቶ ጥላሁን ገልፀው፣ የሰልፉ መረጃ ለህዝቡ በአግባቡ ከደረሰ ከአዲስ አበባ እና አካባቢዋ የተውጣጣ በትንሹ ከ20 እስከ 30ሺ.ህ የሚደርስ ህዝብ እንደሚሳተፍ ገልፀዋል፡፡ የቅስቀሳ ስራው በአግባቡ ከተሰራ ግን እስከ 100 ሺ.ህ የሚደርስ ህዝብም ሊሳተፍ እንደሚችል አቶ ጥላሁን ጨምረው ገልጸዋል፡፡

ፓርቲው ሰላማዊ ሰልፉን ለማካሄድ ጠይቆ የነበረው ቦታ መነሻውን የፓርቲው ጽ/ቤት በማድረግ በራስ መኮንን ድልድይ ፒያሳ ጆጎል አደባባይን ይዞ ቸርቸል ጎዳናን አልፎ መዳረሻውን ድላችን ሀውልት ለማድረግ የነበረ ሲሆን፣ ነገር ግን ፈቃድ ማግኘት ባለመቻሉ ሰልፉ መደረግ ስላለበት ሁለተኛውን አማራጭ ለመቀበል መገደዱን አቶ ጥላሁን ገልፀዋል፡፡ የፓርቲው መጀመሪያ ምርጫ በመሀከል ከተማ የሚያልፍ እና ከአራቱም የከተማዋ አቅጣጫ ሰዎች ሊሳተፉበት የሚችሉበት ቦታ መሆኑን የገለፁት አቶ ጥላሁን፣ አሁን በተፈቀደላቸው ቦታ በሚደረገው ሰልፍ ላይ ግን የተሳታፊው ቁጥር የተጠበቀውን ያህል ላይሆን እንደሚችል ገልጸዋል፡፡

ሰላማዊ ሰልፍን በተመለከተ ሕገ መንግሥቱ ማስፈቀድ ሳይሆን ማሳወቅ ስለሚል ፓርቲው እውቅና እንዲሰጠው ጠይቆ የእውቅና ደብዳቤ በአጭር ጊዜ ውስጥ መውሰዱ የተገለፀ ሲሆን፣ በፈቃድ ደብዳቤው ፓርቲው ቅስቀሳ የሚያደርግባቸውን መንገዶች ያካተተ ፍቃድ እንደተሰጠው ገልጿል፡፡ ፓርቲው በማይክሮፎን፣ ወረቀት በመለጠፍ እና በራሪ ወረቀቶችን ጭምር በመበተን ቅስቀሳ የማድረግ ፈቃድም እንደተሰጠው አቶ ጥላሁን ጨምረው ገልፀዋል፡፡ ፓርቲው ከዚህ ቀደም ካጋጠሙት ነገሮች ትምህርት ወስዶ እንደሆን የተጠየቁት አቶ ጥላሁን፣ በሰላማዊ ሰልፍ ወቅት ችግር የሚገጥመው ከፓርቲው ሳይሆን ከገዢው ፓርቲ የማደናቀፍ ስራ የተነሳ መሆኑን ገልፀው፣ ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ ቅስቀሳው እየተካሄደ እንደሆነ እና ከመጪው አርብ ጀምሮም ወረቀቶቹ እንደሚለጠፉ፣ በራሪ ወረቀቶችም እንደሚበተኑ አሳውቀዋል፡፡

# ወደ የመን ሲጓዙ ከሞቱት ኢትዮጵያዊያን የ21 ያህሉ አስከሬን ተገኘ

■ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የአሜሪካ ኤምባሲ ሐዘናቸውን ገለፁ



በገፅ 4

# ልጇን ገድላ ለሦስት ቀናት የደበቀችው እናት በ18 ዓመት እሥራት ተቀጣች

በገፅ 5

# አንድነት ፓርቲ በዘጠኙ ፓርቲዎች ትብብር ላይ የተወሰደውን እርምጃ አወገዘ

■ ፖሊስ ሰልፉ ሕገወጥ ነበር ብሏል

በጋዜጣው ሪፖርተር

በዘጠኙ ፓርቲዎች ትብብር አማካይነት ሊካሄድ የነበረው የአደባባይ የአዳር ሰልፍ ለመበተን ፖሊስ የወሰደውን የኃይል እርምጃ አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ አወገዘ፡፡ ፖሊስ በበኩሉ ሰዎቹ የተያዙት ሕገወጥ ሰልፍ በማካሄዳቸው ነው ብሏል፡፡

አምባገነኑ የኢህአዴግ መንግስት ሰላማዊ ታጋዮችና በሰላማዊ መንገድ የሚታገሉ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ማሳደዱን አሁንም ቀጥሎበታል ያለው የአንድነት መግለጫ የዘጠኙ ፓርቲዎች ትብብር ለህዳር 27 ቀን 2007 ጠርተውት በነበረው ሰላማዊ ሰልፍ ላይ በመንግስት ኃይሎች የተወሰደውን እጅግ አረመኔያዊ የሆነ ህገወጥ እርምጃ ፓርቲው በጥብቅ ያወግዛል ሲል በድረገፁ አስፍሯል፡፡

ፓርቲው አያይዞም “እነዚህ ፓርቲዎች የሀገሪቱ ህገ መንግስት፣ የስብሰባና ሰልፍ አዋጁ በሚፈቅደው መሰረት ለአዲስ አበባ መስተዳድር ሰልፍ እንደሚያደርጉ ቀኑንና ቦታውን ጠቅሰው አሳውቀዋል፣

በገፅ 5

ሕግ...13
ኢኮኖሚ...8
መዝናኛ...10
የኔ ሃሳብ...18

# በውጭ ለሚኖሩ ወገኖቻችን የተዘጋጀው የቤት ልማት ፕሮግራም የሚደገፍ ነው



የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሰሞኑን በውጪ ሃገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በማህበር ተደራጅተው ቤት እንዲሰሩ ለማገዝ ምዝገባ እንደሚጀምር በመንግሥት የመገናኛ ብዙሃን ማስታወቁ የሚታወስ ነው።

እንደሚኒስቴሩ ገለጻ ይህንኑ ለማሳካት ከክልሎች ከከተማ አስተዳደሮች ጋር በተደረገው ቅድመ ዝግጅት ላይ የተወያየ ሲሆን፥ የመመሪያ ማውጣት ሥራዎችና የመሬት ዝግጅቶች በአብዛኛው አካባቢዎች ላይም በመተግበር ላይ ነው ።

ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያዊያኑ በማህበር ቤቶች መመሪያ መሰረት ከ12 እስከ 24 በመሆን መደራጀት እንደሚችሉና በመረጡት ዲዛይን መሰረትም ቤቶቻቸውን ማስገንባት እንደሚችሉም ይፋ ተደርጓል።

መንግሥት የዜጎችን የመኖሪያ ቤቶች ችግር ለመቅረፍ በአዲስአበባ ከተማ ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ በማካሄድ ያለው የኮንዶሚኒየም ግንባታ በርካታ ዜጎች ተጠቃሚ መሆናቸው የማይካድ ሐቅ ነው። ሆኖም ፕሮግራሙ ሲጀምር የራሴ መኖሪያ ቤት የለኝም ብሎ ከተመዘገበው ከ350ሺ በላይ ቤት ፈላጊ ፍላጎት አንጻር ሲታይ ባለፉት 10 ዓመታት የተሰሩት ቤቶች የፍላጎቱን ግማሽ ያህል እንኳን መመለስ አለመቻላቸው ሲመዘን የሕዝቡ መሠረታዊ ችግር በመንግሥት አቅምና ጥረት ብቻ ሊቀረፍ እንደማይችል አመልካች ነው።

ከዚህ አንጻር በአሁኑ ወቅት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በውጪ ሀገር ለሚኖሩ ኢትዮጵዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በማኅበር ተደራጅተው የቤት ባለቤት እንዲሆኑ የያዘው ዕቅድ የሚደገፍ ነው። የመንግሥት የቤት ልማት ፕሮግራም ዓላማ አነስተኛና መካከለኛ ገቢ ያላቸውን ዜጎች በድኅማ ጭምር የቤት ባለቤት በማድረግ መሠረታዊ ችግራቸውን መፍታት ሲሆን በራሳቸው አቅም ሊሰሩ የሚችሉ ወገኖችን ቦታ በማቅረብና የባንክ ብድር በማመቻቸት ጭምር ማገዝ በውጭ ያሉ ኢትዮጵያዊን ወደሀገራቸው ጠቅልለው በመግባት ተረጋግተው በተለያዩ ኢንቨስትመንቶች ላይ እንዲሰማሩ ማገዝም ይሆናል።

እናም ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ይህንኑ ዲያስፖራ ወገኖቻችንን ፍላጎት ለማሳካት የያዘውን ዕቅድ ትክክለኛና የሚስመሰግነው ነው። ይህ ዕቅድ በጥቃቅን ምክንያቶች በአፈጻጸም እንዳይደናቀፍ ከወዲሁ ልዩ ጥንቃቄና ዝግጅትም ሊደረግ ይገባል።■

## ቁጥሮች

**3.2**

**ሚሊዮን**

በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ቁጥር

**ከ3 ሺህ**

**በላይ**

በኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች የተሰማሩ ዲያስፖራ ባለሀብቶች ቁጥር

ምንጭ:-

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

## መልዕክቶች

# የሚቀድመው ይቅደም

የታክሲ ባለንብረቶች አሁን ያለውን የተበታተነ እንቅስቃሴ በማስወገድ ወደ ኩባንያ አሰራር እንዲቀየር ለማድረግ እንቅስቃሴ መጀመሩን ከጋዜጣችሁ አንብበናል። ይህ ሃሳብ ጥሩ ቢሆንም በቅድሚያ ግን ሊሰራበት የሚገባ ጉዳይ አለ። በቅርቡ በከተማዋ ካሉ ከ6ሺህ በላይ ሚኒባስ ታክሲዎች መካከል በአግባቡ አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙት ከ23ሺ.500 እንደማይበልጡ መገለፁን የምናስታውሰው ነው። በርካታ ታክሲዎች በየመንደሩ ውስጥ እና በየስርቻው ያለ ስራ ቆመው የጎረምሶች ጫት መቃሚያ እና የሴት ልጆች መጎንተያ እየሆኑ ናቸው። እነዚህ ታክሲዎች በስራ ሰዓት እንዲህ አይነቱን አፀያፊ ስራ ሲሰሩ ነው የሚውሉት። እነዚህም በታክሲው ቁጥር ውስጥ ተካተው ወደ ኩባንያ የሚሸጋገር ከሆነ ውጤቱ የተጠበቀውን ያህል ላይሆን ስለሚችል መቅደም የሚገባው ነገር ቀድሞ ቢሰራ መልካም ነው። ከተማዋ በትራንስፖርት እጥረት በምትታመስበት በአሁኑ ወቅት እንደዚህ አይነት ተግባር የሚፈፅሙ ታክሲዎችን እንቅስቃሴ የሚቆጣጠር አንድ አካል አስፈላጊ ሳይሆን እንዳልቀረ ጥርጣሬ አለኝ።

በስልክ- ከደንበል አካባቢ የተሰጠ

# ማስተካከያ

"የምግባረ ሠናይ ድርጅቶችን የሚመለከተው የ70/30 መመሪያ ተሻሻለ" በሚል ርዕስ ባለፈው ሳምንት በወጣው ዜና ላይ "ከምግብ ዋስትና ጋር የተያያዙ ሥራዎች፣ የኤች አይቪ ቫይረስ በውስጣቸው ያለባቸው ሠራተኞች ደመወዝ፣ የአምቡላንስ ተሽከርካሪ ግዢ . . . በአስተዳደራዊ ወጪ እንዲካተቱ" የሚለው "እንዳይካተቱ" ወይንም በፕሮግራም ወጪ እንዲያዙ ተወስኗል በሚል ተስተካክሎ እንዲነበብ ከይቅርታ ጋር እንጠይቃለን።

"ሰንደቅ" ጋዜጣ በሰንደቅ የሕትመትና የማስታወቂያ አገልግሎት ኃ/የተ/የግ/ማኅበር በንግድ ሚኒስቴር በንግድ ሥራ ፈቃድ ቁጥር 14/673/7498/2004፣
በብሮድካስት ባለሥልጣን የምዝገባ ቁጥር 38/2001 የተመዘገበ ሳምንታዊ ጋዜጣ ነው

ዋና አዘጋጅ
ፍሬው አበበ
ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 የቤት ቁጥር 12/201
0911 61 79 35
abebeferew@gmail.com

ም/ዋና አዘጋጅ
ፋኑኤል ክንፉ
0911 865119
Kinfu2006@yahoo.com

አዘጋጅ
ፀጋው መላኩ

ከፍተኛ ሪፖርተሮች
አሸናፊ ደምሴ
መስከረም አያሌው

ግራፊክ ኤዲተር
ነብዩ መሥፍን
0911 18 09 33
nebiyou1st@yahoo.com

ኮምፒዩተር ጽሁፍ
አለምነሽ ታከለ
ሰብለወንጌል ንጉሴ
ምናለሽዋ ተ/አረጋይ

ህትመት ክትትልና ስርጭት
በዛብህ ተክሉ
0911 41 68 00

ማስታወቂያ ሽያጭ
ባይለየኝ ወርቁ
bayleyworku@gmail.com
0921 56 95 03
0912 95 67 95

አታሚ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት
አድራሻ፤ አራዳ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 07 የቤት ቁጥር 984

የአሳታሚው አድራሻ:- ቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 05/03 የቤት ቁጥር 027 ከአትላስ ሆቴል በስተጀርባ 011-6-62 81 90/ 011-6-18 40 34/ 0911 95 58 16 ፖ.ሣ.ቁ. 80964
www.sendeknewspaper.com

# ስለ ሕገ መንግሥት ማሻሻያ

# ሕጉ ምን ይላል?



ሰሞኑን በአሶሳ የተከበረው የብሔር ብሔረሰቦች በዓል

በጋዜጣው ሪፖርተር

አገራት ፍትሐዊነት የሚለውን የሕጎች ሁሉ የበላይ በሆነው (በተጻፈውና ባልተጻፈው) ሕገመንግሥት ያስቀምጣል። ሕገመንግሥቱ መሠረታዊ ፖለቲካ ሥርዓቱ የዜጎች መብትና ሚና ምን እንደሆነ፣ የኢኮኖሚ ፍልስፍናው ወይንም ፖሊሲው፣ በኢኮኖሚው ውስጥ የሰዎች መብት ምን እንደሆነ ይደነግጋል።

ሕገመንግሥት የአንድ ሀገር የበላይ ሕግ ነው። ሕገመግሥት በአንድ ሀገር ስለሚኖር የፖለቲካ ሥርዓት፣ የሥልጣን ባለቤትነት፣ የመንግሥት አካል አወቃቀር፣ የሥልጣን ክፍፍልና አሠራርን እንዲሁም የዜጎች መብቶችና ነጻነቶች በመንግሥትና በዜጎች መካከል ያለውን ግንኙነት የሚደነግግ ዋና የፖለቲካና የሕግ ሰነድ ነው።

በኢትዮጵያ ከ1923 ዓ.ም ጀምሮ የተለያዩ ይዘቶች ያሉዋቸው የተጻፉ ሕግጋተ መንግሥት በሥራ ላይ መዋላቸውንና በአጼው ዘመን ነበረው ሕገመንግሥት መሠረታዊ ይዘቱን ሳይቀይር የመሻሻል ዕድል ገጥሞት እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ።

## 1923 ዓ.ም

በ1923 በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ዘመናዊ ሕገመንግሥት ተረቅቆ ሥራ ላይ ይዋል እንጂ ከዚያም በፊት እንደሕገመንግሥት የሚያገለግሉ የተለያዩ ሰነዶች እንደነበሩ መረጃዎች ያሳያሉ። እነሱም "ፍትሐ ነገስት፣ ክብረ ነገስትና ሥርኣተ መንግስት" በመባል ይታወቃሉ። እነዚህ በዋንኛነት ሃይማኖታዊ ይዘት የነበራቸው ሲሆኑ ዓላማቸውም የነገስታቱን ፍጹማዊ ሥልጣን ማረጋገጥ ነበር።

የ1923ቱ ሕገመንግሥት የዜጎች ይሁንታ ሳያስፈልገው በንጉሱ መልካም ፈቃድ ወጥቶ ሥራ ላይ መዋሉ በመግቢያው ላይ በግልጽ ተመልክቷል።

"....እኛ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ንጉሰ ነገስት ዘኢትዮጵያ፣ በእግዚአብሔር ቸርነት፣ በሕዝብ ህብረት ለኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስትነት ተመርጠን ዘውዱንና ዙፋኑን በህግ አግባብ ተቀብለን ስንቀባ ለዚህ ታማኝ ለመሆን ለመረጠን ፈጣሪያችን የምንመልሰው ወሮታ፣ የተቀበልነውን አደራ እኛም ሠርተን፣ ጠብቀን ተከታያችንም በሕግ እንዲቀበለንና በደንብ እንዲሰራ ለሀገራችንም በመልካም አስተዳደር በሕግ የሚጠበቅበትን ደንብ ከማቆም በቀር ሌላ የምንመልሰው ወሮታ ስለሌለን ለኢትዮጵያ ልማት ለመንግስታችን ጽናት ለምንወደው ሕዝባችንም ጥቅምና ሀብት ሆኖ ደስ እንዲያሰኝ ተስፋ ስላደረግን አሳባችንን ገልጠንና አስረድተን የመንግሥት ሕግ እንዲቆም ቀረጥን..." ይላል።

## 1948 ዓ.ም

የ1923ቱ ሕገመንግሥት ተሻሻለ። ምክንያቱ ደግሞ በየጊዜው ከነበሩ ለውጦች ጋር አብሮ መሄድ አለመቻሉ ነበር። አሁንም ንጉሱ በሕገመንግሥቱ መግቢያ ላይ "...ከሃያ አራት ዓመት በፊት የንጉስ ነገስታችን ዘመን ሲጀምር በራሳችን ፈቃድ ለታማኙ ሕዝባችን ሰጥተን በኢትዮጵያ ንጉስ ነገስት ግዛት መቋቋሙን አውጀን ስለነበር፣ የደግ ነገር ሁሉ መገኛ ከሆነ፣ ሁሉን ከሚችል ከእግዚአብሔር በተሰጠን ጥንካሬና ብርታት በዘመነ መንግስታችን በተነሳው እጅግ ከፍ ባለው የፈተናና የመከራ ጊዜ የተወደደውን ሕዝባችንን መርተን አሰልፈን በሥልጣኔ ደረጃ ተደርሶበት የማይታወቅ እርምጃ ወደተገኘበት ዘመን ስላደረስነው፣ የተደረሰበትን ደረጃ ለማጠንከርና የአገሩን ጸጥታ ለማደላደል፣ ለወደፊቱም እርምጃና ለመጪው ትውልድ ደስታና ደህንነት ጠንካራ መሠረትን ለመመስረት በንጉሱ ነገስቱ መንግስታችን በረጅሙ ታስቦበትና በአያሌው ተጠንቶ የተሻሻለ ሕገመንግስት ስላዘጋጀን..." ሲሉ አስፍረዋል።

> ኢህአዴግ ወደሥልጣን ከመጣ በኋላ የኢትዮጵያ የሽግግር ወቅት ቻርተር ከመጽደቁ በፊት የሚነሱ ጥያቄዎች ነበሩ። ከእነዚህም ዋንኛ ጥያቄዎች መካከል የመንግስት አስተዳደር እንዴት ይዋቀራል እና ሕገመንግስት እንዴት ይረቀቃል የሚሉት ይገኙበታል

## 1980 ዓ.ም

የደርግ ሕገመንግስት የወጣው በሥልጣን ላይ ከወጣ ከአስራሶስት ዓመት በኋላ ነው። ሕገመንግሥቱ ያለህዝብ ተሳትፎና ውሳኔ የወጣ ሲሆን በህገመንግስቱ ሥልጣን የሠርቶ አደሩ ህዝብ መሆኑን ደንግጓል።

## 1987 ዓ.ም

ኢህአዴግ ወደሥልጣን ከመጣ በኃላ የኢትዮጵያ የሽግግር ወቅት ቻርተር ከመጽደቁ በፊት የሚነሱ ጥያቄዎች ነበሩ። ከእነዚህም ዋንኛ ጥያቄዎች መካከል የመንግስት አስተዳደር እንዴት ይዋቀራል እና ሕገመንግስት እንዴት ይረቀቃል የሚሉት ይገኙበታል። ለእነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት እንዲያስችል በሀገሪቱዋ ውስጥ በወቅቱ ነበሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲሰባሰቡ ተደርጓል። በዚህም መሠረት የተደረገላቸው ጥሪ የተቀበሉ 27 ያህል የሚሆኑ ፓርቲዎች የሰላምና ዴሞክራሲ ኮንፈረንስ ማካሄድ ችለዋል። በዚህ ኮንፈረንስ ለሽግግር ወቅት የሚያገለግል ቻርተር ጸድቆ ሥራ ላይ መዋል ችሏል። በዚሁ ቻርተር መሰረትም የህገመንግስት ኮምሽን ተቋቁሞ ሕገመንግስት ከተረቀቀ በኂላ የተለየ የህብረተሰብ ክፍሎች የተወከሉበት የሕገመንግስት ጉባዔ አማካይነት

በገፅ 21

# ኢትዮ ቴሌኮም የገጠመው የሲስተም ችግር ለሁለት ወራት እንደሚቆይ ገለፀ

በፀጋው መላኩ

ኢትዮ ቴሌኮም ሰሞኑን በገጠመው የሲስተም ችግር ደንበኞች የተንቀሳቃሽ ስልክ ሂሳባቸውን መሙላት፣ የሞሉትን ቀሪ ሂሣብ ማወቅ እንደዚሁም ሂሳብን ከአንድ ደንበኛ ወደ ሌላው ማዘዋወር ያልቻሉ ሲሆን፤ ችግሩም የደንበኞች መረጃን የሚይዘው ሲስተም ችግር መሆኑን አቶ አብዱራሂም አህመድ የኩባንያው የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ኃላፊ ለሰንደቅ ጋዜጣ ገለፁ።

እንደ አቶ አብዱራሂም ገለፃ ችግሩ የተፈጠረው በአዲስ አበባ ከተካሄደው የቴሌ ኮም የማስፋፊያ ሥራ ጋር በተያያዘ ከደንበኞች መረጃ ጋር ተያይዞ ያለው ሥራ ሙሉ በሙሉ ባለመጠናቀቁ ነው።

መሰል ችግር አልፎ አልፎ የሚገጥም መሆኑን የገለፁት ኃላፊው ሰሞኑን ከተፈጠረው ችግር ጋር በተያያዘ በ0910፣ በ0911፣ በ0912፣ በ0914፣ በ0918፣ በ0920፣ በ0925፣ በ0934፣ በ0936 እና በ0942 በሚጀምሩ የቅድመ ክፍያ የሞባይል ስልክ መስመሮች ላይ ችግሩ መፈጠሩን አረጋግጠዋል። ችግሩ ካለፈው አርብ ዕለት ጀምሮ መፈጠሩን የገለፁት አቶ አብዱራሂም፤ የአዲስ አበባ ማስፋፊያ ሥራ ሙሉ በሙሉ ቢጠናቀቅም ችግሩ የተፈጠረው ከደንበኞች መረጃ ጋር ካለው ሲስተም ጋር ሲሆን፤ ችግሩም መፍትሄ ሊያገኝ የሚችለው ከአንድ እስከ ሁለት ወራት ባሉት ጊዜያት ውስጥ መሆኑን ገልፀዋል።

ኢትዮ ቴሌኮም ቀደም ሲል የነበረውና የሞባይልና የኢንተርኔት ኔትወርክ ለማስፋት እንደዚሁም ደንበኞቹን የአራተኛ ትውልድ ብሮድባንድ (4G broadband) ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ለማድረግ ከሁዋዌና ከዜድቲኢ ኩባንያዎች ጋር በተናጠል ከእያንዳንዳቸው ጋር የ8 መቶ ቢሊዮን ዶላር የፕሮጀክት ስምምነትን መፈራረሙ ይታወሳል። ሁለቱ ኩባንያዎች እያንዳንዳቸው የ8 መቶ ሚሊዮን ዶላር የቴሌኮም ማስፋፊያ ፕሮጀክት ፊርማን ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር የተፈራረሙ ሲሆን፤ በስምምነቱ መሰረት የአዲስ አበባውን ማስፋፊያ ፕሮግራም የያዘው ሁዋዌ ኩባንያ ሥራውን ሙሉ በሙሉ አጠናቆ ማስረከብ የነበረበት ባለፈው ሰኔ ወር ላይ ነበር። ሆኖም ግን ፕሮጀክቱ ይጠናቀቃል ከተባለበት ከአምስት ወራት በኋላም ደንበኞች ቀደም ሲል ሲጠቀሙበት ከነበረው የተሻለ አገልግሎት እያገኙ አይደለም። በኢንተርኔትም ሆነ በሞባይል ስልክ ያሉት የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮች በተባባሰ ሁኔታ የቀጠሉ ሲሆን፤ ሰሞኑንም ተመሳሳይ ችግር ተከስቷል።■

# የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር የተሽከርካሪዎችና የመንገደኞች መሸጋገሪያ እንዲያካትት ጥረት እየተደረገ ነው

በፀጋው መላኩ

የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ግንባታ ፕሮጀክት በተወሰነ ርቀት የመንገደኞችና የተሽከርካሪዎች ማቋረጫን አላካተተም በሚል የተለያዩ ወቀሳዎች እየተሰነዘሩበት ይገኛሉ። ችግሮቹ በዋነኝነት ከሀያት - መገናኛ - ሃያ ሁለት እንደዚሁም ከቃሊቲ - ሳሪስ - ላንቻ - መሿለኪያ የሚታዩ ሲሆን፤ ለችግሩም መፍትሄ ለመስጠት ጥረት እየተደረገ መሆኑን የአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን ኢንጂነር ፈቃደ ኃይሌ ለሰንደቅ ገልፀዋል።

በከተማዋ እየተካሄደ ካለው የባቡር መሰረተ ልማት ጐን ለጐን በአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን ባለቤትነት የሚመራ የ3 ቢሊየን ብር የመንገድ ግንባታ እየተከናወነ ሲሆን፤ ከባቡሩ ዲዛይን ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽንና የአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን በተለያዩ ጊዜያት ሲወዛገቡ ቆይተዋል። ከአወዛጋቢ ጉዳዮቹ መካከል አንዱ የባቡሩ መስመር ግንባታ የተሽከርካሪዎችን እንደዚሁም የእግረኞችን መታጠፊያና መሸጋገሪያ ታሳቢ ያላደረገ ነው የሚል ነው። ለችግሩ መፍትሄ ለመስጠት ባቡሩ ሥራ እስኪጀመር ድረስ ብቻ ተሽከርካሪዎች ሀዲዱን እንዲያቋርጡ እየተደረገ መሆኑን የገለፁት ኢንጂነር ፈቃደ፤ ለችግሩ ዘላቂ መፍትሄ ለመስጠት ግን የተለያዩ ጥረቶች እየተደረጉ መሆኑን ገልፀዋል።

እንደምሳሌ ያህልም በመገናኛ ሲ ኤም ሲ መስመር ማዕድን ሚኒስቴር አካባቢ፣ ሳህሊተ ምህረት አደባባይና ሲ ኤም ሲ አደባባይ በቋሚነት የመኪኖች መታጠፊያ እንዲኖር የሚደረግ መሆኑን ኢንጂነር ፈቃደ ገልፀዋል። የባቡሩን መሰረተ ልማት ግንባታና እሱን ተከትለው የሚሄዱትን ነባር መንገዶች ተጣጥመው ግንባታቸው እንዲካሄድ ሰፊ ጥረት ሲደረግ የነበረ መሆኑን የገለፁት ሥራ አስኪያጁ፤ ለዚሁ መንገድ ግንባታም ወደ 3 ቢሊዮን የሚጠጋ ብር የተመደበ መሆኑን አመልክተዋል።

እስካሁን ባለው ሂደትም ሰባ በመቶው የፋይናስ አፈፃፀም የተመዘገበ መሆኑን አመልክተው፤ መንገዶቹንም የእግረኛውን መንገድና መብራትን ባካተተ መልኩ እስከ መጪው የካቲት ድረስ ለማጠናቀቅ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ጨምረው አመልክተዋል። ከዚሁ ጋር በተያያዘም መንገዶቹ ከባቡሩ መስመር ጋርም የተሳለጠ ፍሰት እንዲኖራቸው ለማድረግ አንዱ የተሽከርካሪዎች መታጠፊያ በመሆኑ ለዚህም መፍትሄ ለመስጠት የባቡር ኮርፖሬሽን ከአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን ጋር እየሰራ መሆኑን አመልክተዋል።■

# ወደ የመን ሲጓዙ ከሞቱት ኢትዮጵያዊያን የ21 ያህሉ አስከሬን ተገኘ

## - ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የአሜሪካ ኤምባሲ ሐዘናቸውን ገለፁ

በጋዜጣው ሪፖርተር

በጀልባ ወደ የመን ሲጓዙ ከሞቱት 70 ኢትዮጵያውያን መካከል እስከትላንት ጠዋት ባለ መረጃ መሰረት 21 የሚሆኑት አስከሬናቸው መገኘቱ ተገለፀ። የጀልባው ባለቤትና በህገወጥ መንገድ የሰዎች አዘዋዋሪ ነው የተባለው ግለሰብ በፖሊስ እየተፈለገ ነው። ሌሎች የሞቱ ሰዎችን ለማግኘት ፍለጋው ተጠናክሮ መቀጠሉን የዴይሊ ሜል ዘገባ ያመለክታል።

ሰሞኑን ወደየመን ስትጓዝ የነበረች ጀልባ ሰጥማ ከ70 በላይ ኢትዮጵያዊን ለሞት መዳረጋቸው እንዳሳዘናቸው የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር አስታወቁ።

አምባሳደር ፓትሪያሺያ ሀስላክ ለመገናኛ ብዙሃን በላኩት የሐዘን መግለጫ፤ በየመን አቅራቢያ ሰሞኑን በቀይ ባህር በተከሰተው የጀልባ መስጠም አደጋን ተከትሎ የኢትዮጵያ ዜጎችን ጨምሮ የሌሎች ሀገራት ዜጎች ሞት እንዳሳዘናቸውና ለኢትዮጵያ መንግሥትና በአደጋው ሐዘን ለደረሰባቸው ቤተሰቦች እንዲሁም ለጓደኞቻቸው በሙሉ መጽናናትን እንደሚመኙ ገልፀዋል።

በተመሳሳይ ሁኔታም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በቃለአቀባዩ አምባሳደር ዲና ሙፍቲ በኩል በአደጋው የተሰማውን ሐዘን ገልጿል።

በየአመቱ ከምስራቅ አፍሪካ በሺዎች የሚቆጠሩ ስደተኞች በህገ ወጥ መንገድ በባህር አቋርጠው ወደ የመን ለመግባት ይሞክራሉ። በባለፉት አምስት አመታት ከ500 ሺ በላይ የኢትዮጵያ፣ የኤርትራ እና የሶማሊያ ስደተኞች በቀይ ባህርና በኤደን ባህረ ሰላጤ በአስቃቂ ሁኔታ በማቋረጥ ወደ የመን ገብተዋል።■

# ሜታ አቦ ቢራ የምርት ግብዓቱን ሙሉ በሙሉ ከሃገር ውስጥ መጠቀም ሊጀምር ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር

የዲያጂዮ አካል የሆነው ሜታ አቦ ቢራ አክስዮን ማህበር ለምርት ግብዓት የሚያስፈልገውን የእርሻ ውጤቶች በ 2009 ዓ.ም ማለትም ለሜታ 50ኛ አመት የምስረታ በዓል ላይ መቶ በመቶ ከሃገር ውስጥ የሚረከብ መሆኑን ሰሞኑን አስታወቀ። ይህ ከሃገር ውስጥ የምርት ግብዓትን የመረከቡ ስልት ለአጠቃላይ የሜታ ምርቶች እውን የሚሆን ሲሆን ለአንዳንድ ብራንዶች ላይ ብቻ የሚወሰን አይሆንም።

በአሁኑ ሰዓት ከግማሽ በላይ የሚሆነው የድርጅቱ ጥሬ ግብዓት ከሃገር ውስጥ የሚገኝ ነው። ላለፉት ሶስት አመታት በኢትዮጵያ ቢራ ኢንዱስትሪ ውስጥ የሃገር ውስጥ ግብዓትን በመጠቀም ሜታ ፈር ቀዳጅ ድርጅት ሲሆን "በኢትዮጵያ ግብርና እድገት አጋርነት ፕሮግራም" አማካይነት ከአርሶ አደሮች ጋር በቅንጅት የገብስ ፕሮጀክት ላይ በመስራት የሚገኝ የመጀመሪያው አለም አቀፍ ቢራ ፋብሪካ ነው።

ከኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ፣ የኦሮሚያ ግብርና ቢሮ፣ ቴክኖ ሰርብ፣ ሲንጀንታ፣ BASF፣ ኒያላ ኢንሹራንስ እና የሃገር ውስጥ አከፋፋዮች ጋር በአጋርነት በመስራት ሜታ 6 ሺ 113 የሚሆኑ ከአርሲ፣ ምዕራብ አርሲ እንዲሁም ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን የሃገሪቱ ክፍሎች የተወጣጡ አርሶአደሮች ጋር ስምምነት በማድረግ ከ 5 የአርሶ አደሮች ማህበራት ጋር እና ከ 39 የአርሶ አደሮች ሸማቾች ማህበር ጋር በመቀናጀት በመስራት ላይ ይገኛል።

በ2008 ዓ.ም መጨረሻ ቢራ ፋብሪካው 10ሺ አነስተኛ አርሶ አደሮችን በዚህ ፕሮግራም ላይ ያሳትፋል። በ2009 ዓ.ም ደግሞ ይህንን ቁጥር በእጥፍ ለማሳደግ አቅዷል።

የሜታ አቦ ቢራ አ/ማህበር ማኔጂንግ ዳይሬክተር ፍራንሲስ አግቦንላሆር "ዲያጂዮ ለኢትዮጵያ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ልማት ያለውን ቁርጠኝነት በቀጣይነት በማሳየት ላይ ይገኛል። ለምርት አስፈላጊ ግብዓቶቻችንን ሙሉ በሙሉ ከሃገር ውስጥ ለማድረግ የምናደርገው ጉዞ እንዲሁም አሁን በደረስንበት ደረጃ እጅግ በጣም ኮርቻለሁ። በቀጣይነትም ከኢትዮጵያ መንግስት፤ ከብዙ የዚህ መርሃ ግብር ተሳታፊ አርሶ አደሮቻችን እና ቁልፍ አጋሮቻችን ጋር በመቀናጀት ከፍተኛ ደረጃ ላይ እንደምንደርስ እርግጠኛ ነኝ" በማለት ተናግረዋል።

**ዲያጂዮ አለም አቀፍ ድርጅት ሲሆን ምርቶቹም በአለም ዙሪያ ከ 180 በላይ በሚሆኑ ሃገራት ውስጥ ይሸጣሉ**

ሜታ የሃገር ውስጥ ግብዓቶችን ለመጠቀም እያከናወነ ያለው ስራ በግብዓት አቅርቦት ሂደት ላይ ሰፊ ምኅዳር አለው፤ ከእነዚህም መካከል የተለያዩ የገብስ አይነቶች አቅርቦት፣ የዘር አቅርቦት፣ እና የሜካናይዜሽን እገዛን ያካትታል። ከሜታ ጋር ውል የሚያደርጉ አርሶ አደሮች በቅድሚያ በድርጅቱ ሙሉ በሙሉ የሚሸፈን እና አርሶአደሮቹ ከስራው በኃላ የሚከፍሉት የምርጥ ዘር አቅርቦት፣ የዳፕ እና ዩሪያ ማዳበሪያዎች፣ የተባይ መከላከያ፣ የፈንገስ መከላከያ እና የተለያዩ ስልጠናዎች ይሰጣሉ። ከእነዚህም በተጨማሪ የእህል መድህን ዋስትና እና ለአርሶ አደሩ ማህበራት አጠቃላይ የአቅም ግንባታ ስልጠና ይሰጣል።

የሜታ የሃገር ውስጥ ግብዓቶችን የመጠቀሙ ስልት በአፍሪካ ውስጥ ለሚገኙ የዲያጂዮ ድርጅቶች ውስጥ እ.ኤ.አ በ 2008 ዓ.ም ከ70 በላይ የሚሆነውን የምርት ግብዓት ከሃገር ውስጥ ለማድረግ በተቀመጠው የዲያጂዮ አፍሪካ ራዕይ መሰረት ነው። በ2009 ዓ.ም መጨረሻ ደግሞ ከዚህም የበለጠ ለማድረግ ያለመ ራዕይ ነው።

የፋብሪካው ግብዓቶችን ሙሉ ለሙሉ ከሃገር ውስጥ የማድረጉ ቁርጠኝነት በኢትዮጲያ ውስጥ ዘላቂ ልማትን ለማስቀጠል ካለው አጀንዳ አንዱ አካል ነው። የዚህ ስልት ዋነኛው አላማ በምንንቀሳቀስባቸው ሃገራት እና ማህበረሰብ ውስጥ መዋለ ነዋይን ለማፍሰስ ካለን እቅድ አካል ነው። ከዚህ በተጨማሪ ድርጅቱ በኃላፊነት የመጠጣትን ባህል ለማስፈን፣ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል። ለዚህም ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው በቅርቡ በመላው ሃገሪቱ ይፋ የሆነው እና ጠጥቶ ማሽከርከር ላይ የግንዛቤ ለውጥ እንዲመጣ አስተዋፅዖ በማድረግ ላይ የሚገኘው "የሹም ሹፌር" ዘመቻ ነው። በአለም አቀፍ ደረጃ ደግሞ ዲያጂዮ የአለም ጤና ድርጅትን የአልኮልን ጎጂ አጠቃቀም ለማስወገድ ከያዘው አለም አቀፍ እስትራትጂ መሰረት የCEO Commitment የሚለውን የትብብር ሰነድ ከፈረሙ የቢራ፣ የወይን እና የአልኮል መጠጥ አምራቾች ድርጅት አንዱ ነው።

ዲያጂዮ የተለያዩ የአልኮል፣ የወይን እና የቢራ መጠጦች ላይ የተሰማራ የአለማችን መሪ የፕሪሚየም መጠጦች ንግድ ነው። ምርቶቻችን ጆኒ ዎከር፣ ክራውን ሮያል፣ J&B፣ ቡኬነንስ፣ ዊንድሶር እና ቡሽሚልስ ውስኪ፣ እስሚርኖፍ፣ ሲሮክ፣ ኬቴል ዋን ቮድካ፣ ቤይሊስ፣ ካፒቴን ሞርጋን፣ ታንክሬይ፣ ሜታ ቢራ እና ጊነስ በማምረት ይታወቃል።

ዲያጂዮ አለም አቀፍ ድርጅት ሲሆን ምርቶቹም በአለም ዙሪያ ከ 180 በላይ በሚሆኑ ሃገራት ውስጥ ይሸጣሉ። ድርጅቱ በኒውዮርክ እና በለንደን እስቶክ ኤክስቼንጅ ላይ የተመዘገበ ነው።■

## አንድነት ፓርቲ በዘጠኙ...

በአዋጁ መሰረት ደግሞ ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ እንጂ ፍቃድ መጠየቅ ግድ የሚል አይደለም። ነገር ግን ህገወጥ በሆነ ሁኔታ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት ሰላማዊ ሰልፍ ለማካሄድ ከሰማያዊ ፓርቲ ጽህፈት ቤት እየወጡ የነበሩትን ሰልፈኞች በመንግስት ኃይሎች ከፍተኛ የሆነ ድብደባ እንዲፈፀምባቸው ተደርጓል። ከዚህም ባሻገር የትብብሩ ፓርቲዎች አመራሮችና አባላት አፍሶ በመውሰድ በጨለማ ክፍል ውስጥ አስሯቸው ይገኛል። ወዳጅና ዘመድ እንዳይጠይቃቸው መደረጉም የአንድነት ከፍተኛ አመራሮች ሶስተኛ ፖሊስ ጣቢያ በአካል ተገኝተው አረጋግጠዋል። የአዲስ አበባ አስተዳደር ይሄ ጉዳይ በአግባቡና ህጉ በሚፈቅደው መንገድ መፍታት ሲችል፤ በሚዲያ እርምጃ እወስዳለሁ ብሎ ማወጁና በሰላማዊ ሰልፈኞች ላይ ግፍ እንዲፈፀም በማድረጉ ሀላፊነቱን መውሰድ አለበት። በተለይ ኢህአዴግ የ2007 ምርጫ እየቀረበ ባለበት ሁኔታ እንዲህ ዓይነቱ አፈናና ህገወጥ እርምጃ መውሰዱ ምርጫውን ችግር ውስጥ የሚከት ጉዳይ መሆኑ ሊገነዘብ ይገባል። አንድነት ፓርቲ ይሄ ጉዳይ በዝምታ የሚያየው ነገር አይሆንም፤ በቅርቡም አስፈላጊውን መረጃዎች ሁሉ አሰባስቦ ጋዜጣዊ መግለጫ ይሰጥበታል።"

የዘጠኙ ፓርቲዎች አመራሮችና አባላት በህገ መንግስቱ ላይ የተቀመጠውን ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ መብት ከመጠቀም ውጪ ያጠፉት ምንም ዓይነት ነገር ስለሌለ በአስቸኳይ ሊፈቱ ይገባል። ገዥው መንግስት ከህግና ከስርዓት ውጪ በሰላማዊያን ዜጎች፣ በፖለቲካ ፓርቲ አመራሮችና አባላት ላይ እየወሰደ ያለውን አፈና፣ ድብደባና እስር እንዲያቆም፤ የህግ የበላይነትን፣ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን እንዲያከብር አለም አቀፉ ማህበረሰብ ተገቢውን ጫና እንዲያሳድሩ አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ (አንድነት) ፓርቲ ጥሪውን ያቀርባል። በተለይ ደግሞ የጉዳዩ ባለቤት የሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ ይህ ህገወጥና አረመኔያዊ ድርጊት በዝምታ ሊያልፈው አይገባም፤ ኢህአዴግን በቃህ ሊለው ይገባል ሲል በመግለጫው ጠቅሷል።

በሌላ በኩል የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮምሽን ባለፈው እሁድ ዕለት ባወጣው መግለጫ ህገ ወጥ ሰልፍ ያደረጉ ጥቂት ግለሰቦች በቁጥጥር ስር ውለው ምርመራ እየተካሄደባቸው መሆኑን አስታውቋል።

ኮሚሽኑ በዚሁ መግለጫው በአሸባሪነት የተፈረጀው የግንቦት 7 ልሳን ከሆነው ኢሳትና ከሌሎች የውጭ ጸረ ሰላም ሀይሎች የገንዘብ፣ የሀሳብና የሞራል ድጋፍ የሚያገኙት እነዚህ ጸረ ልማት ሀይሎች ምንም አይነት ህጋዊ እውቅና ሳይኖራቸው ህገ ወጥ ሰልፍ ሲያደርጉ በቁጥጥር እንደዋሉ ጠቅሷል።

የቅስቀሳ ጽሁፍ በተለያዩ ስፍራዎች በመለጠፍ እና በመበተን እንዲሁም ልዩ ልዩ ማህበራዊ ድረ ገጾችን በመጠቀም አፍራሽ መልእክቶችን ሲያስተላልፉ ሰንብተዋል ይላል የኮሚሽኑ መግለጫ።

ፖሊስ በመግለጫው ግለሰቦቹ ከህገወጥ ድርጊታቸው እንዲቆጠቡ እና ህግን እንዲያከብሩ በተደጋጋሚ ጊዜያት ምክርና ማስጠንቀቂያ ቢሰጣቸውም አሻፈረኝ በማለት የጸጥታ ሀይሎችን ተንኩሰዋል ብሏል።

የ9ኙ ፓርቲዎች ትብብር ሰልፉ በፖሊስ ኃይል ከተበተነ በኋላ ባወጣው መግለጫ ህዳር 27 እና 28 ቀን 2007 ዓ.ም ሊያካሂድ አስቦት የነበረው የአዳር ሰልፍ ጋር በተያያዘ ከ300 በላይ አመራሮችና አባሎች እንደታሰሩበትና በታሳሪዎቹም ላይ ድብደባ እንደተፈፀመባቸው ይፋ አድርጓል።

በተለያዩ ቦታዎች ፖሊስ በቁጥጥር ሥር ያዋላቸውን የዘጠኙ ፓርቲዎች አባላት ፍ/ቤት በማቅረብ ለምርመራ ተጨማሪ ጊዜ እንደጠየቀባቸውም ታውቋል።■

# ልጇን ገድላ ለሦስት ቀናት የደበቀችው እናት በ18 ዓመት እሥራት ተቀጣች

በአሸናፊ ደምሴ

የአንድ ዓመት ዕድሜ ያለውን ህፃን ልጇን ተሰድቤበታለሁ፤ ተዋርጄበታለሁ በሚል መነሻ በተኛበት አንቃ በመግደል ለሶስት ቀናት በሻንጣ ውስጥ እንዲቆይ ያደረገችው ተከሳሽ፤ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 20ኛ ወንጀል ችሎት ጥፋተኛ በመባሏ በ18 ዓመት ፅኑ እስራት እንድትቀጣ ማክሰኞ ህዳር 30 ቀን 2007 ዓ.ም ተፈረደባት።

የ18 ዓመት ዕድሜ ያላት ተከሳሿ አስቴር ሽፈራው ስትባል፤ የፌዴራሉ ዐቃቤ ሕግ በክስ መዝገቡ እንደሚከተለው አትቷል። ተከሳሿ ሰውን ለመግደል በማሰብ ታህሳስ 10 ቀን 2005 ዓ.ም ከንጋቱ 12 ሰዓት ሲሆን፤ በአዲስ አበባ ከተማ አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ልዩ ቦታው መንደር 8 ቀርሳ በሚባለው አካባቢ በቤት ሠራተኝነት በተቀጠረችበት የወ/ሮ ወርቂ መኮንን እና አቶ ለማ ዘውዴ ቤት በተሰጣት ሰርቪስ ክፍል ውስጥ የአንድ ዓመት ዕድሜ ያለውን ህፃን ልጇን ቤቢ ጌታቸውን ጨካኝነቷን በሚያሳይ ሁኔታ ገድላዋለች ይላል። ዐቃቤ ሕግ ስለግድያው አፈፃፀም ሲገልጽም፣ ተከሳሽ ህፃኑ በተኛበት ወቅት በእጇ አንቃ የገደለችው መሆኑን፤ እንዲሁም ድርጊቱን ከፈፀመች በኋላ ለሶስት ቀናት አስክሬኑን በማዳበሪያ ውስጥ ጠቅልላ በሻንጣ ያስቀመጠች በመሆኑ የህፃኑ አስክሬን በመሽተቱ ምክንያት ሊታወቅ መቻሉን በመጥቀስ የፈፀመችው ከባድ የሰው መግደል ወንጀል ነው ሲል ያትታል።

**ዐቃቤ ሕግ በቅጣት አስተያየቱ ግለሰቧ በፈፀመችው ወንጀል ያልተፀፀተችና ጥፋቷንም አምና ይቅርታ ያልጠየቀች በመሆኑ በሞት እንድትቀጣ ጠይቋል**

ተከሳሿ የዐቃቤ ሕግን ክስ በሚገባ ልትከላከል ባለመቻሏ ፍርድ ቤቱ ህዳር 25 ቀን 2007 ዓ.ም ውሎው ጥፋተኛ ናት ሲል በይኗል። ዐቃቤ ሕግ በቅጣት አስተያየቱ ግለሰቧ በፈፀመችው ወንጀል ያልተፀፀተችና ጥፋቷንም አምና ይቅርታ ያልጠየቀች በመሆኑ በሞት እንድትቀጣ ጠይቋል።

የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 20ኛው ወንጀል ችሎት በበኩሉ የቅጣቱን መነሻ ዕድሜ ልክ በማድረግ እና ተከሳሿ የወንጀል ሪከርድ የሌለባት እንዲሁም የኑሮ ደረጃዋ ዝቅተኛ መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት በ18 ዓመት ፅኑ እስራት እንድትቀጣ ሲል ትናንት በዋለው ችሎቱ ፍርዱን አስተላልፏል።■

# ሰው ለመግደል የሞከረው በ14 ዓመት ተቀጣ

በአሸናፊ ደምሴ

የፌዴራሉ ዐቃቤ ሕግ በቂም በቀል ተነሳስቶ፤ ሰውን ለመግደል በማሰብ የግል ተበዳይን በመስታወት ስባሪ ደጋግሞ ሆዱን በመውጋት የሆድ ዕቃ ጉዳት፣ የግራ ጆሮ ማቁሰል፣ የማጅራት ግዝገዛና በቀኝ እጅ ላይ ወግቶ ከፍተኛ ጉዳት አድርሷል ሲል በመሰረተበት ክስ ጥፋተኛ ሆኖ በመገኘቱ በ14 ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ሲል የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት 10ኛ ወንጀል ችሎት ባሳለፍነው አርብ ህዳር 26 ቀን 2007 ዓ.ም ወሰነ።

እንደዐቃቤ ሕግ የክስ መዝገብ ከሆነ፤ ተከሳሽ አቶ እንዳለ ወልዴ አበጋዝ ሰውን ለመግደል አስቦ ሐምሌ 11 ቀን 2005 ዓም በግምት ከጠዋቱ ሶስት ሰዓት አካባቢ፤ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 04/05 ክልል ውስጥ ልዩ ቦታው ሻውልደማ ትምህርት ቤት ተብሎ ከሚጠራው ስፍራ የግል ተበዳይ አቶ ሽመርጋ ገዳን ጨካኝነቱን በሚያሳይ ሁኔታ ደጋግሞ በመስታወት ስባሪ በመውጋት፤ አንደኛ ትንሹን አንጀት በመቆራረጥና የሆድ ዕቃ ጉዳት በማድረስ፤ ሁለተኛ በግራ ጆሮው ላይ በመውጋት እና በቀኝ እጅ ላይ በመወጋት ያቆሰለና ጉዳት ያደረሰ በመሆኑ እንዲሁም የግል ተበዳይን ማጅራት በመገዝገዝ ያቆሰለ በመሆኑ በፈፀመው ከባድ የሰው መግደል ሙከራ ወንጀል ተከሷል ይላል።

ዐቃቤ ሕግ የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን ለችሎቱ በማቅረብ ያስረዳ ሲሆን፤ ተከሳሽ በበኩሉ የተመሰረተበትን ክስ በሚገባ ሊከላከል ባለመቻሉ ጥፋተኛ ተብሏል።

የግራ ቀኙን ክርክር የመረመረው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 10ኛ ወንጀል ችሎት ድርጊቱ በሙከራ የቀረ መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት ዐቃቤ ሕግ ያቀረበውን የሞት ቅጣት ጥያቄ ወደጎን በመተው በ14 ዓመት ፅኑ እስራትና ለ5 ዓመት በሚደርስ ከማህበራዊ መብቶቹ እንዲታገድ ሲል የቅጣት ውሳኔውን አስተላልፏል።


Rainbow Exclusive Car Rental & Tour Services

# Vacancy Announcement

Rainbow Exclusive Car Rental & Tour Services PLC a member of the MIDROC Ethiopia Technology Group Companies is looking for a qualified and experienced candidate to fill the following vacant post:

- Job Position ---------------------------Senior, Secretary
- Job Grade --------------------------- G-8
- Qualification -------------------------- College Diploma or TVET Level V in Secretarial Science and Office Management or related field of study.
- Work Experience ---- ---------------------3 years and above
- Terms of Employment -------------------- Permanent
- Required No. ------------------------------ 1
- Salary --------------------------------------- As Per the Company's Scale
- Place of work --------------------------------Addis Ababa

Interested applicants who meet the requirement should submit their non returnable application, along with CV and photocopies of other relevant document in person to the Head Office located at Sarbet to apply directly to the human resource services department.

Valid for five working days of this announcement.

**For further details: Telephone Number 0113722638**

በዚህ ዓምድ ስር የሚወጡ ጽሁፎች የፀሐፊውን እንጂ የኤዲቶሪያሉን አቋም አያንፀባርቁም

# በምርጫ ለማሸነፍ የኩንተስ ምክር

## -ለኢህአዴግና ተቃዋሚዎች የሚሆን

በመኩሪያ መካሻ



በጥንታዊቷ ሮማ የተባ አንደበት የነበረው አንድ ሰው በ64 ዓመተ ዓለም ብቅ አለ:: ይህ ሰው ማርከስ ቱሊየስ ቺቼሮ ነበር:: ቺቼሮ በበጋው የ64 ዓመተ ዓለም ለሮማ ሪፑብሊክ ምክር ቤት አባልነት ይወዳደር ነበር:: በዚያን ወቅት የ42 ዓመት ጐልማሳ ሲሆን በአንዲት አነስተኛ አርፒኒዮና በምትባልና ከሮም ደቡብ በምትገኝ ከተማ ተወለደ:: አባቱም ሀብታም የከተማዋ ነጋድራስ ሲሆን ልጆቹ ማርክስና ኩንተስ (ታናሹ) በወቅቱ በትምህርት እንዲበለጽጉ በማሰብ ወደ ግሪክ ልኮ ፍልስፍናና ዲስኩር እንዲማሩ አድርጓል::

ማርከስ የለማ አእምሮና ወርቃማ ምላስ የታደለ አንደበተ ርቱዕ ሰው ነበር:: ማርከስ ያልታደለው ስጦታ ቢኖር ከባለፀጋ አለመወለድን ብቻ ነው:: በወቅቱ የነበረው የሮማውያን ማህበረሰብ ደግሞ ለመደብ ልዩ ሥፍራን ይሰጥ ስለነበር እንደነ ማርከስ ቺቼሮ ያሉ የመጫኛ ነካሽ ልጆች በሪፐብሊኳ ሁነኛ ሥፍራ ማግኘት አይችሉም:: ይህ ሰው ግን የማይበገር ሳተና በመሆኑ አሠራሩ ትክክል አለመሆኑን ለማረጋገጥ ቆርጦ ተነሳ::

በወጣትነቱ ማርከስ ፖምፔይ በተባለው ዝነኛ ሰውና የሮማ ጄኔራል በሆነው ፖምፔይ ሥር ወታደራዊ አገልግሎት አበርክቷል:: እንደሚታወሰው ታላቁ ፖምፔይ የጁሊየስ ቄሳር ተቀናቃኝ ሆኖ የሮማን መንግሥት ይታደጋታል:: ወጣቱ ፖምፔይ የማርከስ ደጋፊ ሲሆን በተከታታይ በሚደረጉ የፖለቲካ አካሄዶቹ ሁሉ እርዳታ አድርጐለታል:: ማርከስ ገና በ25 ዓመቱ በነፍስ ለተከሰሰ ሰው ጥብቅና ቆሞ የመጀመሪያውን የፍርድ ቤት ውሎውን አሸንፏል:: ከዚያም በተከታታይ የቆመላቸው ታዋቂ ሰዎች እንዲረቱ በማድረጉ መልካም ዝናው በየአደባባዩ ጐመራ:: ይህም ሁኔታ በፖለቲካ ታዋቂነት ስሙ በሪፑብሊኳ እንዲገን አደረገ:: በመሆኑም በሚያመረቃ መልኩ በሪፑብሊኩ የአስተዳደርና ፋይናንስ እንዲሁም በታችኛው የምክር ቤት ሹመቶች ላይ በተሿሚነት አገልግሏል:: በዋና የሮማውያን ምክር ቤት አባል ለመሆን ከመኳንንት ዘር መውጣት የግድ አስፈላጊ በመሆኑ የማርከስን ጥረት ታላቅ ፈተና ውስጥ ከቶት እንደነበር ይታወሳል::

በሪፐብሊኩ የምክር ቤት አባል ሆኖ ለመቅረብ ምንም እንኳ የመኳንንትና "ሰማያዊ-ደም" ያለው የዘር መሠረት የሌለው ቢሆንም እጅግ አስቸጋሪውን የምርጫ ዘመቻ ለማድረግ ወሰነ:: "ማሸነፍ!" አለብኝ ብሎ ስለተነሳም ባለ "ሰማያዊ ደም" ተፎካካሪዎቹን ኩም ለማድረግ እንዲህ ቀላል የሆነ ትግል እንደማይገጥመው መገመት ችሏል:: ለዚህ ደግሞ ታናሽ ወንድሙና የተግባር ሰው የሆነው ኩንተስ ታላቅ ወንድሙ ምክር እንደሚያስፈልገው አረጋገጠ:: በዚህም ወስኖ የምርጫ ምክር ለመለገስ ተነሳሳ:: ኩንተስ በአራት ዓመት ከማርክስ የሚያንስ ሲሆን በባህሪው ተናዳጅና ጨካኝነት ነበረበት:: በተጻራሪው ደግሞ ለማርክስ ታማኝ የሆነና የታላቅ ወንድሙ ማሸነፍ ለእሱም ቢሆን ለእውቅናና ሀብት መንገድ ከፋች መሆኑን ያምናል:: ከማርከስ የቅርብ ጓደኛ ከሆነው አቲከስ እህቱን አግብቶ አንድ ወንድ ልጅም ወልዷል::

ወንድሙ በምርጫ እንዲያሸንፍ ዘንድ ለመርዳት ቆርጦ የተነሳው ኩንተስ የምክር ቤት ምርጫው ዘመቻ እንደተጀመረ ለማርከስ በምርጫው ሂደት እንዴት መሳተፍ እንዳለበት የሚገልጽ ደብዳቤ አዘጋጀ:: ይህም ደብዳቤ ለዘመናት ሳይታወቅ የቆየና በላቲን ቋንቋ "Commentariolum Petitionis" የተሰኘው ነበር:: አንዳንድ የሮማውያን ሥነ-ጥበብ አዋቂዎች ኩንተስ ስለመጻፉ የሚጠራጠሩ ቢሆንም ሌሎች ተቀናቃኞቻቸው ደግሞ ኩንተስ በትክክል የደብዳቤዉ ፀሐፊ እንደሆነ ያምናሉ:: ዋናው ጉዳይ ማንም ይጻፈው ማን ጉዳዩ ያለው በፀሐፊው ማንነት ላይ ሳይሆን የጹሑፉ ምንነት ላይ ነው :: በትክክል ማለት የሚቻለው ግን ፀሐፊው በመጀመሪያው ምዕተ ዓለም የነበረውን የሮማውያንን ፖለቲካ የሚያውቅና እንዴት ምርጫን ማሸነፍ እንደሚቻል የተገነዘበ ነበር ማለት ይቻላል:: ይህ ምርጫን የማሸነፍ ዘዴ ለዚያን ወቅት ብቻ ሳይሆን ዛሬም እኛ ለተሰለፍንበት የፖለቲካ ምህዳር ጠቃሚ ማስታወሻ እንደሆነ ይታመናል:: ይህን የምርጫ ምክር በማናቸውም የምርጫ ዘመቻ ላይ መጠቀም አሸናፊነትን ያስጨብጣል::

በቺቼሮ ወንድማማቾች ዘመን ሮም በሰባት ጉብታዎች መካከልና በታይበር ወንዝ አጠገብ የተከተመች አናሳ ከተማ ብትሆንም በወቅቱ ታላቅ ኢምፓየር ሆና ሙገሳን ያገኘች ናት:: የሮማ ፖለቲካም በውስን ሊሂቃኖችዋና በጣት በሚቆጠሩ የመኳንንት ቤተሰቦች ቁጥጥር ሥር የወደቀ ነበር:: የሮማ ዜጐች በሜዲተራኒያን ክልል የሚኖሩ በመሆኑ ቀሪ የምርጫ ሳጥን የሚታሰብባት አልነበረችም:: ከሮም ከተማና ከአካባቢዋ በሚገኙ ከተሞች የተውጣጡ ዕጩዎች ናቸው የምርጫ ውድድር የሚያደርጉት::

ማንኛውም ሮማዊ ለምክር ቤት አባልነት ለመመረጥ በመጀመሪያ የግዴታ ወታደራዊ አገልግሎትን መፈፀም ይኖርበታል:: በተጨማሪም በተከታታይ በታችኛው የመንግሥታዊ አካላት ቢሮዎች ውስጥ (Cursus honorum) ወይም "የክብር ጐዳና" ተመርጦ ማገልገልን ይጠይቃል:: በዚህ ረዥም ሂደት ውስጥ በአስተዳደሩ አነስተኛ እርከኖች አቃቤ-ንዋይ ሆኖ ከማገልገል ይጀምራል:: በሁለተኛ ደረጃም የሲቪል ፍርድ ቤቶች ኃላፊነት ይከተላል:: እንዲህ እያለ ኃላፊነቱ የሮማን ጠቅላይ ግዛቶች ወደ ማስተዳደር ኃላፊነት ይሸጋገራል:: የተወሰኑና ምርጦቹ ብቻ ናቸው ለምክር ቤት ምርጫ የሚወዳደሩት:: ምርጫውም በሮም ከበርቴዎች ከፍተኛ ቁጥጥርና ጥበቃ ይደረግለታል::

ሮማውያን የግሪካውያንን "አንድ ሰው፣ አንድ ድምጽ" አስተሳሰብ ይከተላሉ:: ማንኛውም ለአቅመ አዳም የደረሰ ወንድ ዜጋ ድምጽ መስጠት ይችላል:: እርግጥ ሁኔታው እጅግ በተወሳሰበ ቡድናዊ ጦርነት ተጠርንፏል:: ግለሰቦች የቡድናቸው አባል በምን መልኩ ድምጽ መስጠት እንዳለበት ድጋፍ ያደርጋሉ:: በምክር ቤቱ ደግሞ ቡድኑ ነው አንድ ድምጽ የሚሰጠው:: እነዚህ ቡድኖች መሠረታቸው ወታደራዊ ወይም ጐሳዊ ሊሆን ይችላል:: በእነ ቺቼሮ ዘመን ግን የነበረው የምርጫ ሁኔታ በመደባዊ የሀብት ብቃት ተለውጧል:: በአብዛኛው ዝቅተኛ ሕብረተሰብ ዘንድ ሀብታሙ ዜጋ የበላይነትን ይይዛል:: የምርጫ ሥርዓቱ በሮምና በሮም ዙሪያ ለሚኖሩ ቅድሚያን ይሰጣል:: ስለዚህ ከሮማ በርቀት የሚኖር ገበሬ ወይም ነጋዴ ተጉዞ ምርጫ ለማድረግ የሚያስችለው ሁኔታ አልነበረም ማለት ይቻላል::

ምንም እንኳ በምርጫው ዘመቻ ወቅት መራጮችን መግዛትና የምርጫ ብጥብጦች ቢከሰቱም በዋና መዲናዋ ለሚኖሩና ወደ ሮም ተጉዘው ምርጫ ለሚያደርጉ የምርጫው ሁኔታ የተስተካከለና ትክክለኛ እንደሆነ መናገር ይቻላል:: ዜጐች ካምፓስ ማሪተስ አደባባይ በመገኘት ከንጋቱ ጀምሮ የመጨረሻውን የምርጫ ውድድር ዲስኩር ያዳምጣሉ:: ከዚያም በየምርጫ ጣቢያቸው ተከፋፍለው ድምጻቸውን ይሰጣሉ:: ምርጫው የሚካሄደው በምስጢር የድምጽ አሰጣጥ ዘዴ ሲሆን መራጩ የሚፈልገውን ዕጩ ስም በአንዲት አነስተኛ ጣውላ ላይ በመጻፍ በትልቅ ቅርጫት ውስጥ ይጥላል:: ከዚያም በየምርጫው ጣቢያ የተሰጠው ድምጽ በትክክል ተቆጥሮ ይፋ ይደረጋል:: የመጀመሪያው ከፍተኛ ድምጽ ያገኘው አሸናፊነቱ ይገለጻል:: ሁለተኛው ተመራጭ በረዳት የምክር ቤት አባልነት እንዲሠራ ይፋ ይደረጋል:: ከፍተኛ ድምጽ ያገኘው የከፍተኛው ምክር ቤት የሆነው በፋሻ የተጠመጠመ መጥረቢያ የሆነውን ምልክት ከፍ አድርጐ ያነሳል:: ይህም የተመራጩን ሰው ሥልጣን ምሉእነት ያመለክታል:: በሌላ አነጋገር በትረ-ሥልጣን መጨበጥ ነው:: አሸናፊው ከጥር 1 ቀን ጀምሮ የሮማን ሪፑብሊክ ለመምራት የሚችል ተመራጭ ሆኖ በከፍተኛ ሥነ-ሥርዓት

**ምንም እንኳ በምርጫው ዘመቻ ወቅት መራጮችን መግዛትና የምርጫ ብጥብጦች ቢከሰቱም በዋና መዲናዋ ለሚኖሩና ወደ ሮም ተጉዘው ምርጫ ለሚያደርጉ የምርጫው ሁኔታ የተስተካከለና ትክክለኛ እንደሆነ መናገር ይቻላል**

በገፅ 19

በዚህ ዓምድ ስር የሚወጡ ጽሁፎች የፀሐፊውን እንጂ የኤዲቶሪያሉን አቋም አያንፀባርቁም

# ስለ ታቦተ-ጽዮን ያለው ታሪክና እውነታው ምንድን ነው?!

በዲ/ን ተረፈ ወርቁ

ህዳር 17 ቀን 2007 ዓ.ም በዚሁ ጋዜጣ በወጣ ጽሑፌ የታቦተ ጽዮንን መሰረቅ የሐሰት ዜና መነሻ በማድረግ ስለ ጽላተ ሙሴ ያሉትን፣ የወጡትንና እየወጡ ያሉ ታሪካዊ የሆኑ መረጃዎችን፣ የጥናትና የምርምር ሥራዎችን በአጭሩ ለመዳሰስ ሞክሬያለኹ:: በዛሬው ጽሑፌም በክርስትናው ዓለም የታቦተ ጽዮን ብቸኛ ባለ አደራና ጠባቂ እንደሆነች የምትናገረው የኢትዮጵያ ቤ/ን፣ ከረጅም ዘመናት ጀምሮ ከአገረ እስራኤልና ከአይሁድ ሕዝብ ታሪክ፣ ባህልና ትውፊት ጋር ያላትን ጥብቅ የሆነ ቁርኝት መሠረት በማድረግ ስለ ታቦተ ጽዮን የጀመርኩትን ዳሰሳ እቀጥላለኹ:: የዛሬው ጽሑፌን በአንድ ገጠመኜ ልጀምር::

በ፳፻ ዓ.ም. የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም በየሦስት ዓመት አንድ ጊዜ የሚደረገውን ፲ኛውን ዓለም አቀፍ የአይሁዳውያን ኮንፈረንስ አዘጋጅቶ ነበር:: በዚህ ኮንፈረንስም ላይ ከሰሜን አሜሪካ፣ ከአውሮፓ፣ ከኤዥያና ከአፍሪካ የተሰባበሱ በአይሁዳውያን ታሪክ፣ ሃይማኖት፣ ሕግ፣ ባህልና ቅርስ ላይ ሰፊ የሆነ ምርምርና ጥናት ያደረጉ በርካታ ምሁራን ተሳትፈውበት ነበር:: የእኛዎቹ ቤተ-እስራኤላውያንም በዚህ ኮንፈረንስ ላይ ንቁ ተሳታፊዎች ነበሩ::

በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም የአርት ጋለሪም ከዚሁ በርካታ የጥናት ጽሑፎች በቀረቡበት አይሁዳውያኑ ኮንፈረንስ ጋር ጎን ለጎንም የኢትዮጵያውያን ቤተ እስራኤላውያንን ጥንታዊ ታሪክ፣ እምነት፣ ባህልና ቅርስ የሚዘክር ዐውደ ርእይም ተዘጋጅቶ ነበር:: ታዲያ በወቅቱ ለዚህ ዓለም አቀፍ ኮንፈረንስ ከመጡ እስራኤላውያን እንግዶች ጋር የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ግቢን፣ የጆኔፍ ኬኔዲ መታሰቢያ ቤተ መጻሕፍትንና እንዲሁም የባህል ማዕከልን አብረን ጎብኝተን ነበር:: ታዲያ በጉብኝታችን መካከል እነዚህን እስራኤላውያን እንግዶችን እጅጉን ያስገረማቸው ነገር አጋጥሟቸው ነበር::

ይኸውም የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን የባህል ማዕከልን ጎብኝተን ከጨረስን በኋላ ለማስታወሻ ፎቶ ለመነሳት በባህል ማዕከሉ መግቢያው በር ላይ ቆመን ሣለን እስራኤላውያኑ ድንገት ከእንቅልፋቸው እንደነቁ ኹሉ በአድናቆትና በመገረም በአንድ ድምፅ ‹‹ዘ ዴቪድ ስታር›› ሲሉ ጮኹ:: ወደ ባህል ማዕከሉ መግቢያ በር ጠጋ ብለውም በበሩ ላይ ተቀረጸውን የዳዊትን ኮከብ በካሜራቸው ለማስቀረትም መረባረብ ያዙ:: በእነዚህ አይሁዳውያን የተገረምኩት እኔ ገንጠል ብዬ ኹኔታቸውን በአትኩሮት መከታተል ያዝኩ::

በፊታቸው ላይ ልዩ አድናቆት፣ የታሪካቸውና የማንነታቸው ቅርስ፣ ክብርና ኩራት በፈነቀለው ልዩ ስሜት ዓይናቸው የደስታን ዕንባን ያዘለው የሚስለው እነዚህ እስራኤላውያን እንግዶች የዳዊትን ኮከብ በአንጋፋው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የባህል ማዕከል በር ላይ ተቀርጾ ማየታቸው ስሜታቸውን ለምን እንደዚህ እንደለዋወጠውና እንደነካው በጥቂቱም ቢሆን ተረድቼያቸው ነበር::

ለአንድ ሺህ ስምንት መቶ ዓመት በላይ ከርስታቸው ተነቅለው እንደ ጨው ዘር በዓለም ኹሉ ተበትነው፣ ታሪካቸው የሰቆቃ፣ የመከራና የስደት የኾነባቸው ተንከራታች ሕዝቦች:: በኹለተኛው ዓለም ጦርነት ወቅትም ወገኖቻቸው በያሉበት እየታደኑ ስድስት ሚሊዮን የሚሆን ሕዝባቸው እጅግ ዘግናኝና አሰቃቂ በሆነ መንገድ ያለቁባቸው ሕዝቦች፣ የአገራቸውን ጥንታዊ ታሪክ፣ የአባቶቻቸውን ቃል ኪዳንና ጽኑ እምነት በጉልህ የሚዘክርየመታሰቢያ ቅርስ የአፍሪካ መዲና በኾነችው በአገረ ኢትዮጵያ ማየታቸው ምን ያህል ልባቸውን ወይም ስሜታቸውን ሊነካው እንደሚችል መገመት አያዳግትም::

ይህ እስራኤላውያኑ እንግዶች የተደነቁበት የዳዊት ኮከብ በቤተ መንግሥቱና በቤተ ክህነቱ እስካሁንም ድረስ በታሪክነቱ በቅርስነት ተጠብቆ መቆየቱንና አሁንም ድረስ ይህ ምልክት በቤተ መንግሥት፣ በአንዳንድ ታላላቅ በኾኑ የኢትዮጵያ ገዳማትና አድባራት እንደሚገኙ ለእንግዶቹ አጫወትኳቸው:: ይህን እውነታም ዳግመኛ ያዩትና ያረጋግጡ ዘንድም የቀድሞ ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ስድስት ኪሎ ካምፓስ የብረት አጥር ይዤያቸው ኼድኩ::

በዩኒቨርስቲው ረጅም አጥር የዳዊትን ኮከብ ከመስቀል ምስል ጋር በአንድነት ተቀርጾ ያዩት አይሁዳውያኑ እንግዶች በመጽሐፍና በጆሮ ብቻ የሚያውቁትን ታሪክ እውነታውን በዓይናቸው አይተው ስላረጋገጡ ከፊታቸው ላይ ልዩ ስሜቴ ነበር የሚነበብባቸው:: በአብሮነት ቆይታችንም ይህን የመሳሰሉ የኢትዮጵያንና የአይሁዳውያኑን ታሪካዊ ግንኙነትና እምነት አስመልክቶ በሰሜኑ የአገራችን ጉብኝታቸው በርካታ ታሪካዊ እና መንፍሳዊ ቅርሶች እንዳሉ ገልጬላቸው ወደ ኮንፈረንሱ አዳራሽ ተመለስን::

ይህ ገጠመኜን ለማንሳት የወደድኩት ያለ ምክንያት አይደለም:: በኢትዮጵያውያንና በእስራኤላውያን መካከል ስላለው ሺህ ዘመናትን ያስቆጠረ የጋራ ታሪክ፣ ባህል፣ ቅርስና እምነት ጋር ተያይዞ የሚነሡ በርካታ ታሪካዊ ሐቆች፣ ባህሎች፣ መንፈሳዊ የኾኑ ቅርሶች ስላሉን ነው:: እንደ ኢትዮጵያ ቤ/ን መምህራንና የታሪክ ሊቃውንት ትንታኔ የአይሁዳውያኑ ሕዝብ ነጻ አውጪ ሊቀ ነቢያት ሙሴ ኢትዮጵያውያዊቷን ሴት ከማግባቱ ጋር ተያይዞ የኢትዮጵያና የእስራኤል ሕዝብ ግንኙነት የታሪክ ውሉ ከዚህ የጋብቻና አምቻ ትስስር ወይም ግንኙነት ይመዘዛል ሲሉ ያስረዳሉ።

በአንጻሩም ደግሞ አንዳንድ የቤተ ክርስትያኒቱ ሊቃውንቶች በኢትዮጵያውያኑና በእስራኤላውያን መካከል ስላለው ታሪክ ሲተነትኑ ከፍጥረተ ማግሥትና ከአይሁዳውያኑ አባት ከሆነው ከአብርሃም ታሪክ ጋር በመያያዝ ወደኋላው በመጓዝ ይተርካሉ:: ይህን ትንታኔያቸውን ሲያጠናክሩም የሰው ልጆች ኹሉ አባት የኾነው አዳም በገነት ከፈጣሪው እግዚአብሔር ጋር ሲነጋገር የነበረው በግዕዝ ቋንቋ መሆኑን በማንሣት የቃል ኪዳን ሕዝብ በኾኑት በእስራኤላውያኑ በኢትዮጵያውያን ሕዝቦች መካከል እግዚአብሔር ልዩነት እንዳላደረገ ያስረዳሉ:: ለዚህም ማስረጃ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡-

‹‹እናንተ ኢትዮጵያውያን ለእኔ እንደ እስራኤላውያን አይደላችሁምን!›› ኢትዮጵዊ መልኩን ነብር ዥንጉርጉርጉርነቱን ይለውጣልን?!›› የሚሉና ሌሎችም ተመሳሳይ የኾኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን በመጥቀስ እነዚህ ኹለቱ አገራት በአምላክ ዘንድ የአንድ ሳንቲም ኹለት ገጽታ ያህል ክብር፣ ቃል ኪዳንና የታሪክ መወራረስ ያላቸው አንድም፣ ኹለትም ሕዝቦች አድርገው ያስሏቸዋል፣ ያስቀምጧቸዋል።

እንዲሁም የክርስትና ሃይማኖት ገና በምድረ እስራኤል በኹለት እግሩ ባልቆመበት በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን የአይሁድ አምልኮትን ሲፈጽም ወደ ኢሩሳሌም ተጉዞ በነበረው በጃንደረባው አማካኝነት አገራችን ኢትዮጵያ ከዓለም ሁሉ አስቀድማ የክርስትና እምነት የመቀበሏ እውነታም ከዚሁ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ከእስራኤላውያን ሕዝቦች ባልተናነሰ በአምላክ ልብ ውስጥ ከነበራቸው መታሰብ፣ ክብርና ዘላለማዊ ቃል ኪዳን ጋር የተያያዘ መሆኑን ያሰምሩበታል።

ሃይማኖት፣ ታሪክንና ባህልን መሠረት ያደረገው የኢትዮጵያውያንና የእስራኤላውያን ታሪካዊ ትስስር ቅድመ ልደት በ፱፻፶ዓ.ዓ. የአክሱም ንግሥት በሆነችው በሳባና በእስራኤላውያኑ ንጉሥ ሰለሞን ግንኙነት ጅማሬ በኹለቱ አገራት መካከል ሌላ ፖለቲካዊ አንድምታ ያለው የታሪክ መሠረትን ጥሏል:: ‹‹ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ሥዩመ እግዚአብሔር›› በሚል አሳዛኝ ፍጻሜውን እስካገኘበት እስከ ፲፱፻፷፮ ድረስ ለሺህ ዘመናት የቆየን ዘውዳዊ ሥርዓትን በኢትዮጵያ ለማንበር የቻለን ‹‹ሰለሞናዊ›› እየተባለ የሚጠራ ሥርወ መንግሥትን እውን ለማድረግ ተችሎት ነበር::

ከዚህም በላይ ደግሞ ይኸው የሰለሞንና የአክሱማይቷ ንግሥት የሳባ ግንኙነት በአይሁዳውያኑ አምላክ በያሕዌ እጅ ዐሥርቱ ትዕዛዛት የተጻፉበት ጽላትና ማደሪያው የሆነው ታቦቱ ወደ አክሱም ምድር እንዲመጣ ምክንያት ኾኗል:: ከ፴፻ ዓመታት በላይ በባርነት ፍዳ መከራቸውን ሲያዩ ከነበረበት ከግብፅ ባርነት ነጻ ባወጣቸው በመሪያቸው በሙሴ አማካኝነት የተቀበሉት ጽላት በእስራኤላውያኑ ሕዝብ ታሪክ ውስጥ ትልቅ ስፍራና ክብር ያለው መንፈሳዊ ቅርስ ነበር፤ አሁንም ነው::

እጅግ አስፈሪ፣ አስደንጋጭ በሆነ መለኮታዊ ነጎድጓድ፣ እሳትና ሰማያዊ ብርሃን መውረድ፣ በብርቱ አውሎ ነፋስና ወጀብ፣ በሲና ተራራ መናወጽና የምድሪቱ መንቀጥቀጥ፣ በመላዕክት ሥርዓት በሙሴ አማካኝነት የተቀበሉት የአምላካቸው የያሕዌ ትእዛዛት የተጻፉበት ጽላት በእነርሱና በአምላካቸው መካከል የሞትና የሕይወት ምስክር ሆኖ የቆመ ሕያውና ዘላላማዊ ቃል ኪዳን ነበር ማለት ይቻላል::

> የሰው ልጆች ኹሉ አባት የኾነው አዳም በገነት ከፈጣሪው እግዚአብሔር ጋር ሲነጋገር የነበረው በግዕዝ ቋንቋ መሆኑን በማንሣት የቃል ኪዳን ሕዝብ በኾኑት በእስራኤላውያኑ በኢትዮጵያውያን ሕዝቦች መካከል እግዚአብሔር ልዩነት እንዳላደረገ ያስረዳሉ

ይህን እጅግ የከበረና መለኮታዊ ትእዛዛት የሰፈሩበት ጽላትና ማደሪያው የሆነው ታቦቱን በተመለከተ ቢያንስ ላለፉት ኹለት ሺህ ዓመታት ገደማ የት እንደተሰወረና በማን እጅ እንዳለ እንኳን ሌላው ዓለም ቀርቶ ራሳቸው ቀደምት ባለቤት የሆኑት እስራኤላውያኑ እንኳን ከአንዳንድ መላ ምቶች በስተቀር አፉቸውን ሞልተው የሚናገሩት ይህ ነው የሚሉት ተጨባጭ የሆነ መረጃም ሆነ ማስረጃ የላቸውም:: ለዚህ ዓለም ኹሉ እንቆቅልሽ ስለሆነበት እጅግ የከበረ፣ ታላቅና መንፈሳዊ ቅርስ ባለቤት፣ ጠባቂና ባለ አደራ አድርጋ የምትናገረው ግን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስትያን ብቻ ናት::

ስለዚሁ ዓለም ደብዛው ስለጠፋበት የቃል ኪዳኑ ታቦት መናገርና በእርግጠኝነት መግለጽ ብቻም ሣይሆን ብሉይን ከሐዲስ ኪዳን ጋር አስማምታ የታቦት ሥርዓትን ጠብቃ እስካሁን ዘመን ድረስ የቆየች ብቸኛዋ የሐዲስ ኪዳን ቤተ ክርስትያንም ይኸቺው የኢትዮጵያ ቤ/ን መሆኗ ለብዙዎቹ እንዴት ሲሆን ቻለ በሚል ግርምትን የሚጭር ጉዳይ ሆኖ እሳካሁን ድረስ ዘልቋል። እስቲ ከዚህ ከንጉሥ ሰለሞንና ከንግሥት ሳባ ግንኙነት ጋር ተያይዞ ያሉትን አንዳንድ ታሪካዊ መረጃዎችንና ጥናቶች በአጭሩ ለማየት እንሞክር::

ስለ ንግሥተ ሳባ የእስራኤል ጉብኝነትና ይህን ተከትሎም የታቦተ ጽዮንን ወደ ኢትዮጵያ መምጣት በሰፊው የሚተርከው ብቸኛው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስትያን የመረጃ ምንጭ የክብረ ነገሥት መጽሐፍ ነው:: ይህ መጽሐፍ ኢትዮጵያውያን በታሪካቸው ትልቅ ክብርና ስፍራ የሚሰጡት መጽሐፍ ነው:: በመቅደላ ጦርነት ወቅት እንግሊዞች ይህን መጽሐፍ ከበርካታ ቅርሶች ጋር ዘርፈው ወደ አውሮፓ ምድር አሻግረውት ነበር:: እናም ዐፄ ዮሐንስ በታኅሣሥ ፲፬ ቀን ፲፰፻፷፬ ዓ.ም. ስለዚህ መጽሐፍ ጉዳይ ለእንግሊዟ ንግሥት ቪክቶሪያ የሚከተለውን የተማፅኖ ደብዳቤ ጽፈውላት ነበር::

‹‹አገሬና ሕዝቤ የሚመራበትን የኢትዮጵያን ሕግጋት የያዘ ክብረ ነገሥት የተሰኘ መጽሐፍ በእናንተ ዘንድ አለ። እባካችሁ በማን እጅ እንዳለ አፈላልጋችሁ ስደዱልኝ። ያለ እዚህ መጽሐፍ የአገሬ ሕዝብ አይታዘዙኝምና ...::›› በዚህ የንጉሡ የተማጽኖ ደብዳቤም በእንግሊዝ ንግሥት ትእዛዝ ይህ መጽሐፍ ለዐፄ ዮሐንስና ለሕዝባቸው እንደተመለሰላቸው የታሪክ መዛግብት ያረጋግጣሉ::

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስትያንና በቤተ መንግሥቱ ላለፉት ሺህ ዘመናት አገልግሎት ሲሰጥ በነበረው በዚሁ መጽሐፍ ላይ ‹‹The Ark of the Covenant: Evidences Supporting the Ethiopian Traditions›› በሚል ርእስ የዶክትሬት ድግሪ ማሟያ የሚሆነውን የጥናት ድርሳን ያቀረበው አሜሪካዊው ምሁር ዶ/ር ቤርናድ ሊማን የክብረ ነገሥት መጽሐፍ ስለ ታቦተ ጽዮን ታሪካዊ አመጣጥን በተመለከተ የሚያቀርበውን ትንታኔና ትውፊት የሚያጠናክር ታሪካዊ መረጃዎች ብሎ በዚሁ ድርሳኑ ላይ የጠቀሰውን አንድ አርኪዮሎጂስቶች ቡድን ግኝትን መሠረት አድርጎ ያቀረበውን መረጃ እንመልከት::

በዚሁ ድርሳኑ ላይ ዶ/ር ሊማን የአርኪዮሎጂ ባለሙያዎች ከውቅሮ ደቡብ ምዕራብ ስምንት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በሚገኘው በጥንታዊው በአባ ገሪማ ገዳም በቁፋሮ ያገኟቸው ኹለት ትላልቅ የሳባውያንን እጣን መሠዊያዎችን ይጠቀሳል። እነዚህ ቅደመ ልደት ፰፻ ዓ.ዓ. ገደማ እንደነበሩ የተገመቱት እነዚህ ኹለት ትላላልቅ የዕጣን መሠዊያዎች ላይ የተቀረጹ ጽሑፎች ንግሥት ሳባንና ንጉሥ ሰለሞንን በተመለከተ የክብረ ነገሥት መጽሐፍ የሚያቀርበውን ትረካ የሚደግፉ መሆናቸውን ያስምሩበታል።

የንግሥተ ሳባንና የንጉሥ ሰለሞንን ግንኙነት በተመለከተ ከመጽሐፍ ቅዱስ በተጨማሪም ቅዱስ ቁርአንም የንግሥተ ሳባን የእስራኤል ጉብኝት በተመለከተ በሚናገረው አንቀጽ፣ ‹‹ንግሥት ሳባ የሳባውያንና የግሪካውያን አማልክት ትታ ፊቷን ወደ የእስራኤል አምላክ በማዞር የሰለሞንን እምነት እንደተቀበለች ያብራራል።›› በተመሳሳይም ሊባኖሳዊው የታሪክ ምሁር ፕሮፌሰር ከማል ሳሊቢ እስራኤላውያን በባቢሎን ወረራ ጊዜ መቅደሳቸው ሲፈርስ ወደ የመን የተሰደዱ አይሁዳውያን ቅድመ ልደት ፭፻፹፯ ዓ.ዓ. እስከ ፫፻፴፪ ዓ.ም. በአክሱማውያን ቤተ መንግሥት ውስጥ ትልቅ ተጽእኖ እንደነበራቸው።›› አትቶ ጽፏል።

ፕ/ር ከማል ሳሊቢ በዚሁ ጥናታዊ ጽሑፉ እንደሚያስረዳው አክሱማውያን ክርስትናን ከተቀበሉ በኋላም የክርስትና ሃይማኖትን ከአይሁዳውያኑ ሃይማኖት ሕግ፣ ባህል፣ ሥርዓትና ወግ ጋር በማቀናጀት ያካሂዱ እንደነበር ዘግቧል። ይህን አክሱማውያን ከእስራኤላውያን ጋር የነበራቸውን የሃይማኖት፣ የታሪክና የባህል ግንኙነት በተመለከተም በሰጠው ድምዳሜም እንዲህ ነው ያለው፡- ‹‹Aksum was the True Zion as well as the keeper of the True Faith (Monophysite

በገፅ 18




# ለአስፓልት ኮንክሪት መንገድ አማራጭ የሆነው የሴሜንት ኮንክሪት

በፀጋው መላኩ

በአገራችን በስራ ላይ ካሉት የሲሚንቶ ፋብሪካዎች መካከል አንዱ የድሬዳዋ ሲሚንቶ ፋብሪካ ነው:: ድሬዳዋ ሲሚንቶ ፋብሪካ ቱሬ ሲሚንቶ ፋብሪካ ቀጥሎ በድሬዳዋ ከተማ የሚገኝ ፋብሪካ ነው:: ፋብሪካው በአሁኑ ሰዓት ክሊነከር የተባለውንና በከፊል ያለቀለትን የሲሚንቶ ግብዓት በማምረት ወደ ጂቡቲና ሶማሌላንድ እንደዚሁም በቅርቡ በኩባንያው ወደ ተገዛውና ቆቃ ወደሚገኘው እህት ኩባንያውም እንደሚልክ ከኃላፊዎቹ ገለፃ መረዳት ችለናል:: ከዚህም በተጨማሪ የሶማሌላንድ ገበያንም ለመጠቀም ከኦማንና ከግብፅ ምርቶች ጋርም የገበያ ውድድርን እያካሄደ ነው::

የሀገር ውስጥ የሲሚንቶ ፋብረካዎች በዋነኝነት ሁለት አይነት ሲሚቶዎችን ያመርታሉ:: እነዚህም ምርቶች ኦፒሲ እና ፒፒሲ በመባል የሚታወቁ ናቸው:: ሁለቱ የሲሚንቶ ምርት አይነቶች ለተለያየ የግንባታ ግብአትነት የሚውሉ ሲሆን መሰረታዊ ልዩነታቸውም የተቃጠለው ክሊንከር ምርት ወደ አለቀለት የሲሚንቶ ምርት ለመውሰድ በሚጨመረው የጂፕሰም መጠን ነው::

ናሽናል ሲሚንቶ ሁለቱንም የምርት አይነቶች የሚያመርት መሆኑ ተመልክቷል:: ኩባንያው ወደ ጂቡቲና ሀርጌሳ የሚልከው የክሊንከር ምርትን ብቻ ሳይሆን ያለቀለትን ሲሚንቶ ጭምር መሆኑን የኩባንያው የሽያጭ ክፍል ኃላፊ አቶ ዘመድኩን ጌታቸው ገልፀውልናል::

ፋብሪካው የአቧራና የጪስ መቆጣጠሪያ የቴክኖሎጂና አካባቢያዊ የእፅዋት ተከላን ስላከናወነ የፋብሪካው አካባቢ ንፅህናም የተጠበቀ መሆኑን ለመመልከት ችለናል:: በውስጡ የተተከሉት የብክለት መቆጣጠሪያ ማሽኖች ፋብሪካው እንደሌሎች ሲሚንቶ ፋብሪካዎች ምንም አይነት ጭስ ወደ ከባቢ አየር እንዳይለቅ አድርጎታል:: ፋብሪካው ሰማኒያ ዓመት ሊያገለግለው የሚችል የግብአት ምርት በዙሪያው የሚገኝ መሆኑን ኃላዎፊቹ ገልፀውልናል::

በመንገድ የኮንክሪት ግንባታ አይነቶች በዋነኝነት ሁለት አይነት የግንባታ አይነቶች አሉ:: እነዚህም አስፓልት ኮንክሪትና ሴሜንት ኮንክሪት በመባል ይታወቃሉ:: አስፓልት ኮንክሪት በዋነኝነት በሀገራችን የተለመደ የመንገድ ግንባታ ዘዴ ሲሆን የመንገዱ የመጨረሻ ግብአት የሬንጅ ምርት ነው:: ሬንጅ ከተለያዩ ሀገራት በከፍተኛ የውጪ ምንዛሪ የሚገዛ በመሆኑ በዚያው መጠን በአስፓልት ኮንክሪት የሚገነባ መንገድ የወጪ መጠን ከፍተኛ መሆኑን መረጃዎች የሚያመለክቱት::

የጥገና ወጪው ከአስፓልት ኮንክሪት አንፃር ሲተያይ አነስተኛ ነው:: በግንባታ ላይ ያሉ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች በቀጣይ ወደ ማምረት ሲገቡ ከፍተኛ ምርት ገበያው ላይ ስለሚኖር ኩባንያዎቹ የምርት ፍላጎት ችግር እንዳይገጥማቸውና በሙሉ አቅማቸው እንዲያመርቱ በኢትዮጵያ የመንገድ ግንባታ ስራ የአስፓልት ኮንክሪት ግንባታ ሊለመድ የሚገባ መሆኑን የናሽናል ሴሜንት የሥራ ኃላፊዎች ገልጸውልናል::

የሲሚንቶ ኮንክሪት መንገድ ግንባታ እንዲለመድ በድሬዳዋ ከተማ የተለያዩ ሰርቶ ማሳያ ግንባታዎችን ከማከናወን ባለፈ ከድሬዳዋ ጂቡቲ የሚገነባው መንገድም ከአስፓልት ኮንክሪት ይልቅ በሲሚንቶ ኮንክሪት እንዲገነባ ለመንግስት ሃሳብ ያቀረቡ መሆኑን አቶ ዘመድኩን ገልፀውልናል::

ከዚህም በተጨማሪ በድሬዳዋ ከተማም መሰል የመንገድ ግንባታን በማከናወን ግንባታው እንዲለመድ ለማድረግ ከከተማው መስተዳደሩ ጋር ኩባንያው እየተነጋገረ መሆኑ ነው የተመለከተው:: ከጥንካሬ አኳያ ሬንጅ አስፓልት በቀላል ጥገና ቢበዛ ሃያ አምስት አመት እድሜ የመቆየት አቅም ሲኖረው፤ የሲሚንቶ ኮንክሪት መንገድ በአንፃሩ ቀላል ጥገና እየተደረገለት እስከ አርባ ዓመት መቆየት የሚችል መሆኑን ባለሙያዎቹ ገልፀውልናል::

ከግንባታ ዋጋ አንፃርም ቢሆን የሲሚንቶ ኮንክሪት ከአስፓልት ኮንክሪት ብቻ ሳይሆን ከኮብል ስቶንም ጭምር የተሻለ መሆኑን ነው ያብራሩት:: በተደረገው ጥናትም አንድ ሜትር ካሬ መንገድን ለመስራት እስከ ሁለት መቶ ሰባ ብር የሚጠይቅ ሲሆን ያንኑ ተመሳሳይ የመንገድ ስፋት በሲሚንቶ ኮንክሪት ለመስራት ግን አንድ መቶ ዘጠና ብር ብቻ የሚያስፈልግ እንደሆነ ለመረዳት ችለናል:: ከዚህም በተጨማሪ የሲሚንቶ ኮንክሪት አስፓልት በግንባታው ሂደት እንደ አስፓልት ኮንክሪት ውስብስብ ቴክኖሎጂን አለመጠየቁ ራሱ ተመራጭ ያደርገዋል ተብሏል::

ፋብሪካው ከአዲስ አበባ ጅቡቲ ከሚገነባው የባቡር መንገድ ውስጥ ከድሬዳዋ ጅቡቲ ላለው የግንባታ ክፍል ሲሚንቶ በማቅረብ ላይ ነው:: ለዚህም አቅርቦት የሚውል ራሱን የቻለ የምርት ማቀነባበሪያ መሳሪያም ተክሏል:: ተቀባይ ኩባንያዎችም ምርቱን በስፋት ስለሚወስዱ ሲሚንቶው ሳይታሸግ የሚወስዱበት የራሳቸው ታንከር አላቸው::



በተደረገው ጥናትም አንድ ሜትር ካሬ መንገድን ለመስራት እስከ ሁለት መቶ ሰባ ብር የሚጠይቅ ሲሆን ያንኑ ተመሳሳይ የመንገድ ስፋት በሲሚንቶ ኮንክሪት ለመስራት ግን አንድ መቶ ዘጠና ብር ብቻ የሚያስፈልግ እንደሆነ ለመረዳት ችለናል

## ለዓለም አቀፉ ነዳጅ ዋጋ ማሽቆልቆል እየተሰጡ ያሉ ምክንያቶች

የአንድ ድፍድፍ በርሜል ዋጋ አንዳንድ ጊዜ ከአንድ መቶ ዶላር ትንሽ ከፍ ብሎ ከቆየ በኋላ ከተወሰኑ ዓመታት ወዲህ ድግሞ በበርሜል ከሰማኒያ እስከ መቶ ዶላር የነበረ ሲሆን በቅርቡ ግን ወደ ሰባ ዶለር አሽቆልቁሏል:: የፔትሮለየም ላኪ አገራት ድርጅት የሆነው ኦፔክ አባል ሀገራት 30 ሚሊዮን በርሜል ነዳጅ በየዓመቱ ለማቅረብ በ2011 ስምምነት ላይ የደረሱበት ሁኔታ ነበር::

ይህም የምርት አቅርቦት መጠን ቀድሞ እንደሚደረገው የዋጋው ሁኔታ እየታየ የመቀነስና የመጨመር አዝማሚያ ሳይታይበት ላለፉት ተከታታይ ዓመታት ባለበት እንዲቀጥል ተደርጓል:: ከአቅርቦቱ መትረፍረፍ ጋር በተያያዘ የኦፔክ አባል ሀገራት መጠኑ እንዲቀንስ ሃሳብ ቢያቀርቡም ከአባል አገራቱ መካከል ከፍተኛ የነዳጅ አምራች በሆነችው

አሜሪካም ቢሆን በከፍተኛ ደረጃ አሳት ከሚባለው ክምችት ውስጥ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን መጠቀም መጀመሯ በዓለም አቀፉ የነዳጅ ዋጋ መውረድ ሳይም የራሱን አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደሩ ነው የሚነገረው

በገፅ 20

## በኬኒያ ባንኮች የሳይበር ጥቃት በመሰንዘር ዘረፋ ሲያከሂዱ የነበሩ ሰባ ቻይናውያን ተያዙ




ቻይናዊያኑ ተጠርጣሪዎች በ ፍ/ቤት

በኬኒያ ባንኮች ላይ የሳይበር ጥቃትን በማካሄድ የሀገሪቱን ገንዘብ በህገወጥ መንገድ ለማዘዋወር የሚያስችላቸውን የመረጃ ቴክኖሎጂ ስርአት በድብቅ ሲዘረጉ ደርሼባዋለሁ ያለቸውን ሰባ

የባንክ የገንዘብ ዝውውርን ለማካሄድ የሚያስችሉ ሶፍትዌሮችና የተለያዩ ውስብስብ የቴሌኮም መሳሪያዎች ተገኝተዋል

ቻይናውያንየኬኒያ ፖሊስ በቁጥጥር ማዋሉን ደይሊ ኔሽን ጋዜጣ ሰሞኑን ባሰራጨው ዘገባ ገልጧል:: የኬኒያን ፖሊሰ የምርመራ ሂደት ዋቢ ያደረገው ይሄው ዘገባ ግለሰቦቹ ተደራጅተው ቤት በመከራየትና የሀገሪቱንም የቴሌኮም ስርአት

በገፅ 18




# ከመሻሻል ይልቅ እየከፋ የመጣው የዓለም የገቢና የሐብት ልዩነት

- *የችግሩ መፍትሄስ?*
- *ስለሐብትና ገቢ ልዩነት እንዲሁም መለኪያዎች በጥቂቱ*
- *የሀብትና የገቢ ልዩነት እየከፋ የመጣባቸው ምክንያቶች በባለሙያዎች እይታ*
- *በዓለማችን የሚገኙ 3 ሐብታሞች ሀብታቸው 48 ሀገራት ተደምረው ካላቸው ይልቃል ስለመባሉስ?*

በሳይ ከአዳማ

እነሆ መሸጋገሪያ፤ የህንድ ዋና ከተሞች 'ሁለት' ናቸው የሚል አባባል እንሰማለን፡፡ ከተሞቹም ኒውዴልሂ እና ኦልድ ዴልሂ፡፡ አንደኛው (ኒውዴልሂ) እውነተኛው የሀገሪቱ ዋና ከተማ ሲሆን፤ ሁለተኛው (ኦልድ ደልሂ) የዳቦ ስም ነው፡፡ የዳቦው ስም የወጣው ደግሞ በመዲናይቱ በነዋሪዎቿ መካከል የተፈጠረውን ከፍተኛ የገቢና የሀብት ልዩነት ለማሳየት እንደሆነ ይነገራል፡፡ ሌላም ያክላሉ፡፡ በአንደኛው የመዲናይቱ ጥግ በወርቅ ማንኪያ የሚበላ ማኅበረሰብ ሲኖር በሌላው ጥግ ግን የሚላስ የሚቀመስ የሌላው በሽ ነው ይላል፡፡ አንድ የሀገራችን ኮሜዲያንም በመዲናችን የሁለት ጫፎች ምሳሌ ተደርገው ስለሚወስዱት ቦሌና ቂርቆስ / ጨርቆስ/ እንዲህ ብሎ ነበር፡፡ በቦሌ ክትፎ ቅቤ በዛበት ተብሎ የቅርጫት ሲሳይ ሲሆን በጨርቆስ ግን ከቅርጫት ውስጥ ከልጣጭ ጋር የተጣለ ሙዝ ካለ በሚል በፍለጋ ይኳትናል፡፡

ቁርጥን ስለማወቅ እና ቁርጥ ሥጋ ከመብላት ጋር ተያይዞ በአንድ ወቅት በማኅበራዊ ድረ ገጽ ጣል የተደረገውንም ቀልድ ልብ ይሏል፡፡ አሁን ወደዛሬው ዋነኛ ማጠንጠኛ ርዕሰ ጉዳያችን ተሻግረናል፡፡

### ስለ ሐብትና ገቢ ልዩነት እንዲሁም ስለመለኪያዎቹ በጥቂት

ሐብትና ገቢ በትርጓሜ ደረጃ ተመጋጋቢ ናቸው ሊባል ይችላል፡፡ ገቢ ሀብት ነው፡፡ ሐብትም ገቢ፡፡ ሐብት ተንቀሳቃሽ እና የማይንቀሳቀስ በሚሉ ሁለት ሰፋ ያሉ ምዕራፎች ይከፈላል፡፡ የሐብትና የገቢ ልዩነት በግለሰቦች፣ ቡድኖች፣ ማኅበረሰቦች፣ ህዝቦች እና ሀገራት መካከል በተጨባጭ የሚታይ እና ተቆጥሮ የሚደረስበት የልዩነት ማሳያን መሰረት ያደርጋል፡፡ እገሌ፣ እና እገሌ፣ እነዚያ እና እነዚህ ያላቸው ሀብትና ገቢ መሳ ለመሳ ይነፃፀርና ነው እውነታን መሰረት ያደረገ ልዩነት አለ ወይስ የለም፣ ልዩነቱ ትንሽ፣ መካከለኛ ወይም የተለጠጠ ነው ለማለት የሚቻለው፡፡ የጠቃቀስናቸው ጥቅል እውነታ እንደተጠበቁ ሆኖ ከዘርፉ ባለሙያዎች አንፃር እነሆ ከሀብትና ገቢ ልዩነት መለኪያዎች በአብዛኛዎቹ ዘንድ ተግባር ላይ ስለዋለውና ጊኒ ኮፊሸንት ስለተሰኘው የጊኒ ኮፊሸንት /Gini Coefficient/ አመጣጥ ከታዋቂው ጣልያናዊ ስታትስቲሺያንና የማኅበረሰብ ባለሙያ ጌራዶ ጊኒ ጋር ይያያዛል፡፡ ጣልያናዊው ከአንድ ምዕተ ዓመት በፊት በአንድ አጋጣሚ ያቀረበው ሙያዊ ትንተና በብዙዎች የዘርፉ ባለሙያዎች ዘንድ የሞቀ አቀባበል ተለገሰው፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮም እንደ የገቢና የሀብት ልዩነት መለኪያ የተጠቀመው ቀመር ዛሬመ ድረስ በቅብብሎሽ የሚመራበት ሆኗል፡፡ የጌራዶ ጊኒ የዜጐች የሀብት ክፍፍል ቀመር በሁለት ቁጥሮች መካከል መሆኑን ያስቀምጣል በ'0' እና በ'1' መካከል፡፡ እነዚህ ቁጥሮች ተደምረው፣ ተቀንሰው፣ ተባዝተውና ተካፍለው የሚገኙ የመጨረሻ የስሌት ውጤቶች ናቸው፡፡ ትርጓሜአቸውም ታሳቢ የተደረጉ መሠረታዊ የሃሳብ ስሌቶችን በአግባቡ በሚያሳይ መልኩ የተቃኙ ናቸው፡፡ የሀብትና ገቢ ልዩነቱ 0 ነው ሲባል በዜጐች መካከለ ፍፁም ፍትሐዊነት ስለመኖሩ የሚገልፁ ሲሆን፤ '1' ነው ሲባል ደግሞ በተቃራኒው ፍፁም ኢ-ፍትሐዊነት ስለመኖሩ ያመላክታል፡፡ በእርግጥ በደምሳሳው ሲታይ በነባራዊው ዓለም ወደ ሁለቱ የተጠጋ ሊኖር ይችላል እንጂ ይህን ያህል የተለጠጠ ልዩነት ተፈጥሮአዊ አለመሆኑንና የማጋጠም ዕድሉም አለ ለማለት የማያስደፍር ስለመሆኑ ይነገራል፡፡

### በዓለማችን የሚገኙ 3 ሀብታምች ሐብታቸው 48 ሀገራት ተዳምረው ካላቸው ይልቃል ስለመባሉስ?

ዓለም አቀፍ የገንዘብ ፈንድ /IMF/ ጨምሮ የተለያዩ ተቋማት በቅርቡ በባለሙያዎች አስጠንተው ይፋ ያደረጉት መረጃ የሀብትና የገቢ ልዩነት ከመሻሻል ይልቅ እየከፋና እየባሰበት መምጣቱን ይገልፃሉ፡፡

በድሃውና ሀብታሙ መካከል ልዩነቱ በአስጊ ደረጃ ላይ ስለመገኘቱም በሪፖርቶቻቸው ይፋ አድርገዋል፡፡ የዚህ መነሻው ደግሞ "ባለው ይጨመርለታል" እንዲሉ ሀብታሙ የበለጠ በሀብት እየፈረጠመ እና እየደረጀ ሲሄድ በተቃራኒው ድሃው የቁልቁል በመንደርደር እየቆረቆዘ እንዲሄድ ግድ ሆኖበታል፡፡

22 ሀገራትን በአባልነት ያቀፈው የኢኮኖሚ ትብብር እና ልማት ድርጅት (Organization for Economic co-operation and Development) በጉዳዩ ላይ ባለሙያዎች ጥናት አድርጎ የጥናቱን ውጤት ይፋ አድርጓል፡፡ የተቋሙ የጥናት ውጤት ከዓለም አቀፉ የገንዘብ ፈንድ ጋር ተመሳሳይ አንድምታ የታየበት ነው፡፡ ዛሬ ላይ ሆኖ ወደኋላ 25 ዓመታትን ማዕከል ያደረገው የጥናት ውጤት በአባል ሀገራቱ ዜጐች መካከል ችግሩ ስር እየሰደደ መምጣቱን አረጋግጧል፡፡ በዚህም በሀገራቱ ከሚገኙ 10 በመቶ የሚሆኑ ሀብታም ዜጐች ሀብትና ገቢያቸው በሀገራቱ ከሚኖሩ 10 በመቶ ከሆኑት ድሆች ሪከርድ የሆነ በ7 ዕጥፍ በልጦ ታይቷል፡፡ ቀድሞም ቢሆን ልዩነቱ የዋዛ ባልነበረው በአሜሪካም ዛሬ ላይ የትየለሌ ሆኗል፡፡ የተሻሉ በተባሉት በጀርመን፣ ዴንማርክ እና ስዊድን እንኳን ሁኔታው አሳሳቢ ስለመሆኑ ተገልጿል፡፡ በእነዚህ በማኅበራዊ ዋስትናና በሥራ ፈጠራ የተሻለ ትኩረት ሰጥተው ይሰራሉ በተባሉት እንኳን ቀድሞ በአማላይ የዜጐች የገቢና የሀብት ልዩነት አልያም የሀብታሙ ገቢ ከድሃው በ5 ዕጥፍ ይበልጥ የነበረው በአንድ ደረጃ ከፍ ብሎ ብልጫው ወደ 6 ዕጥፍ ደርሷል፡፡ በመሆኑም በምድራችን በመቶና በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ብቻ አብዛኛውን ሀብት እንዲቆጣጠሩት ግድ ሆኗል፡፡

በዩናይትድ ኔሽንስ ዩኒቨርስቲ የዓለም አቀፍ የኢኮኖሚክስ ኢንስቲቲዩት ይፋ ያደረገው መረጃም ለዚህ አባባላችን ማጠናከሪያ ነው፡፡ እናም እንደተቋሙ ጥናትና ውጤት በዓለም ላይ 3 ሰዎች ብቻ ያካበቱት ሀብት 48 ድሃ ሀገራት ተዳምረው ካላቸው ይልቃል ሲል ስጋቱን ጭምር አስቀምጧል፡፡


ፕሬዚዳንት ኦባማ ለልዕለ ኃያሏ ሀገር ህልምና ራዕይ ከፊቷ የተደቀነ ስጋት ብለው የገለፁት በተግባር የታየ ነው፡፡ በሀገሪቱ አንድ በመቶ የሆኑት ሐብታሞች ብቻቸውን፣ ከአሜሪካ 90 በመቶ ከሆኑ ዜጐች ሀብት የላቀው በእጃቸው ይገኛል፡፡ ይህም ሳይበቃ በተገባደደው የፈረንጆች (2014) መባቻ የተደረገው ጥናት ሌላ እውነት ይፋ አድርጓል ጥናቱን ያደረገው ኦክስፋም የተባለው ዓለም አቀፍ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ይህቼን ምድር መኖሪያ ያደረጉ 85 የናጠጡ ሀብታሞች ያላቸው ሀብት አስገራሚ በሚል ነበር የገለፀው፡፡ የእነዚህ 100 እንኳን የማይሞላ የዓለም ሀብታሞች ሀብት ከዓለም ህዝብ ግማሽ ከሆነው ከ3-5 ቢሊየን ህዝብ ሐብት በልጦ መገኘቱንም አብራርቷል፡፡

**በእነዚህ በማኅበራዊ ዋስትናና በሥራ ፈጠራ የተሻለ ትኩረት ሰጥተው ይሰራሉ በተባሉት እንኳን ቀድሞ በአማላይ የዜጐች የገቢና የሀብት ልዩነት አልያም የሀብታሙ ገቢ ከድሃው በ5 ዕጥፍ ይበልጥ የነበረው በአንድ ደረጃ ከፍ ብሎ ብልጫው ወደ 6 ዕጥፍ ደርሷል**

በሀገራት ደረጃ ከፍተኛ የሀብት ልዩነት እ.ኤ.አ በ2005 በቺሊ ዝቅተኛው ደግሞ በስሎቬኪያ ከተመዘገበ ወዲህም ከመሻሻል ይልቅ ብሶበት መገኘቱን ነው የጠቃቀስናቸው የመረጃ ምንጮች ያረጋገጡት፡፡ በዚሁ መሰረት በዜጐች መካከል በገቢና በሀብት ልዩነት ጣራ የነካው የደቡብ አፈሪካው ሲሆን፣ ከዓለም በቀዳሚነቱ ይጠቀሳል፡፡

በዚያች ነጮችና ጥቁሮች ለዓመታት በአንድ ላይ በኖሩባትና አሁንም እየኖሩባት ባለው የማንዴላ ሀገር፣ በዜጐች መካከል የተመዘገበው የገቢና የሀብት ልዩነት በዓለም ሀገራት በዓለም ላይ ከተመዘገበውም የላቀ መሆኑ የዚያች ሀገር ቀጣይ ዕጣ ፈንታ ላይ ጥላ አጥልቶበታል ነው የተባለው፡፡ ከአንዳንድ ወገኖች እንደሚሰማው ሀገሪቱ አፓርታይድን አስወግዶ ካገኛቸው የፖለቲካ ነፃነት የዘለለ ትርጉም ያለው የዜጐች እኩልና ፍትሐዊ ተጠቃሚነት አለመኖሩ ከመናገር ያለፈ በተጨባጭ እየታየ ያለ ጉዳይ ነው፡፡ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ የአንበሳውን ድርሻ የሚቆጣጠሩት ነጮቹ የመሆኑ ጉዳይም ፀሐይ የሞቀው ሐቅ ነው፡፡ እናም ኢ-ፍትሐዊ የሐብት ክፍፍሉ በተፈጥሮ ፀጋ በበለፀገችው ሀገር ዳግም ሌላ ችግር ወልዶ ወዳልተፈለገ

በገፅ 20



# የፍቅር "ማርትሬዛ"

በአሸናፊ ደምሴ

የተዳፈነ ፍቅርን፣ የተወጠነ ዓላማን፣ ያልታሰበ ክስተትንና ገንዘብ ያልገዛውን እውነተኛ ማንነት የሚያሳይ ፊልም ነው፤ ማርትሬዛ። "የፍቅር ዋጋው ስንት ነው…?" ሲል የሚጠይቀው ይህ ፊልም ከአስር ዓመታት የውጪ ሀገር ቆይታ በኋላ ወደ ሀገሩ የተመለሰን ዶክተር፤ ትርምስ የበዛበት የፍቅር ታሪክና ድንገት ሳይታሰብ በፈነዳ ክስተት መካከል እውነተኛ ፍቅር እንዲሁም ገንዘብና ውለታ ካቆሙት ጓደኝነት ጋር ሲታገል ያሳየናል።

ዶክተር ሰለሞን (ታሪኩ ብርሃኑ (ባባ)) ራሱን ከጐዳና ህይወት አንስቶ በጥረቱና በዶ/ር ቤዛ (መቅደስ ትዕዛዙ) ረዳትነት የውጪ የትምህርት ዕድሉን አሳክቶ ህይወቱን መለወጥ የቻለ ሰው ነው። ያም ሆኖ በእጅጉ በግል ተፅዕኖዋ ስር የከተተችውን ዶክተር ቤዛን ተሰናብቶ ለጋራ ፕሮጀክታቸው መሳካት ከዓመታት በኋላ ወደ አገሩ፤ አዲስ አበባ ሲገባ እንመለከታለን።

እናቷን በልጅነቷ ያጣችው ሃና (ሰላም ተስፋዬ) አባቷ እናትም አባትም ሆነው ያሳደጓት ሲሆን የስዕል ችሎታዋን አዳብራ በራሷ "ስቱዲዮ" ውስጥ ዓለሟን አጥራ የምትኖር ተደርጋ ተስላለች። ስለምን የወንድ ጓደኛ አታበጂም? ወይም ጓደኛዋ በቀልድ መልክ እንዳለችው "መቼ ነው የራስሽን ሰው የምትስይው?" ለሚለው ጥያቄ የሰጠችው መልስ፤ "ሽራና ብሩሽ ሲገኝ ነው" ስትል ለፍቅር የተዘጋጀ ንፁህ ልብ እንዳላት ትናገራለች።

ዶ/ር ቤዛ (መቅደስ ትዕዛዙ) የጐዳና ተዳዳሪዎችን ለመርዳት በሚያቅደው ፕሮጀክት ውስጥ ዶ/ር ሰለሞንን ከኋላ ሆና በመደገፍና በማስተባበር ከባህር ማዶ የምትጫወት አይነት ሴት ናት። ቤዛ የዶ/ር ሰለሞን ፍቅረኛና ከወራት በኋላም የትዳር አጋር መሆኗን ለማወጅ ወደ አዲስ አበባ ለመምጣት የተነሳች ቢሆንም፤ የታሰበው ቀርቶ ያልታሰበው ሲሆን "ማርትሬዛ" ያሳየናል።

ለዶ/ር ሰለሞን እንደ ጓደኛም እንደሾፌርም የሚያገለግለው ዮሐንስ (ቴዎድሮስ ስዩም) እንደ ብዙ ፊልሞቹ ሁሉ እዚህም ሣቅ ፈጣሪ ሆኗል። ከተለያዩ ሴቶችና ከባለትዳሮች ጋር ሳይቀር "መውጣት" የሚያምረው ይህ ገፀ-ባህሪ ወሲብ የሱስ ያህል የተጣባው፤ ሴት አውል ተደርጐ ተስሏል። ከሁሉም ጐልቶና አስቂኝ ትዕይንቶችን የሚያሳየው ግን ከአለቃው ሚስት ጋር በተደጋጋሚ ወስላች መሆኑ ነው።

ዶክተር ሰለሞን በጐዳና ህይወቱ መካከል የሃናን አባት አግኝቶ የኑሮው አቅጣጫ መለወጥ መጀመሩን ለጓደኛው ለዮሐንስ ሲነግረው እንሰማለን። ያም በመሆኑ አዲስ አበባ በገባ በሁለተኛው ቀን ፍለጋው "ጋሼ" ብሎ የሚጠራውን የሃናን አባትና ሃናን ያገኛቸዋል።

"ገንዘብና ውለታ ፍቅር አይሆንም" የሚለው ዶ/ር ሰለሞን፤ ከዶ/ር ቤዛ ጋር ለአስር ዓመታት ያሳለፈው ህይወት የፍቅር ጉጆውን



| የፊልሙ ርዕስ | ማርትሬዛ |
|---|---|
| አቅራቢው | ታምራት ፊልም ፕሮዳክሽን |
| ድርሰትና ዝግጅት | ብስራት መሐመድ |
| ፕሮዳክሽን | ጋራድ ፊልም ፕሮዳክሽን |
| ተዋንያን | ታሪኩ ብርሃኑ (ባባ)፣ ሰላም ተስፋዬ፣ ቴዎድሮስ ስዩም፣ መቅደስ ትዕዛዙ፣ እስከዳር አባይ (ፒና)፣ ኤፍሬም ታደሰ እና ሌሎችም ተሳትፈውበታል። |
| ኤክስኪዮቲቭ ፕሮዲዩሰር | ታምራት ጳውሎስ |
| ስክሪፕት ሱፐርቫይዘር | ታሪኩ ብርሃኑ እና እስማኤል ሃሰን |
| ካሜራና ኤዲቲንግ | ዳንኤል ግርማ |
| ሳይት | አቤ አሰፋ |

አለመስራቱን አረጋግጧል። ለዚህም ከሃና ጋር የነበረው የእህትና ወንድምነት ግንኙነት፣ እርሷ ለእርሱ ያላት ፍቅርና እርሱ ለእርሷ እንደታናሽ እህት የሚያደርግላት እንክብካቤና ጥንቃቄ ግድቡን እንዳፈረሰ ወራጅ ውሃ ሁለቱንም ድንገት አጥለቅልቆ ሲወስዳቸው እናያለን።

"ዲያስፖራዎች ስትባሉ አገራችሁ የምትታያችሁ ለሠርግና ለለቅሶ ጊዜ ብቻ ነው እንዴ?" ሲል የሚጠይቀው ቀልድ አዋቂው ዮሐንስ፤ ዶክተር ቤዛ ጋብቻዋን በኢትዮጵያ ከፈፀመች በኋላ ተመልሳ ወደ ውጪ ሀገር የመሄድ ጽኑ ፍላጐት እንዳላትና እዚህ (ኢትዮጵያ ውስጥ) የመኖር ምንም ሀሳብ እንደሌላት ስትናገር፤ ሀሳቧ ግር የሚለው ዶ/ር ሰለሞንን እናየዋለን።

ውሎ ሲያድር ፍቅር ከመሰለው የዶ/ር ቤዛ እስር እየላላ የመጣው ዶ/ር ሰለሞን፤ በአለባበስም ሆነ በአስተሳሰቧ ነፃነት እየተማረከባት በመጣችውና የታናሽ እህቱ ያክል ከሚሳሳላት ሃና ጋር በፍቅር ይወድቃል።

ይህ ፍቅራቸውም የቀድሞ ወዳጁን ዶ/ር ቤዛን ብቻ ሳይሆን ዱብ-ዕዳ ለሆነባቸው የሃና አባትም ክፉኛ ሐዘን ሲፈጥር እንመለከታለን።

በአዲሱ ፍቅርና በከረመው ፍቅር መካከል ሲዋልል፣ ሲደሰትና ሲፀፀት የምናየው ዶ/ር ሰለሞን፤ የመጣበት ፕሮጀክት ሰዎች ሁሉ ገንዘብ ላይ የሚያተኩሩና ከመንስኤው ይልቅ ውጤቱ ላይ ብቻ አተኩረው መስራታቸው የሚያስጨንቀው ሆኖ፤ ውጤቱን የተሻለ ለማድረግ ሲለፋ "ማርትሬዛ" ያሳዩናል።

"ለነገሮች ሁሉ ከውጤቱ ይልቅ ለመፍትሄው የሚረዳን መንስኤው ነው" ሲል የሚሞግተው ዶክተሩ፤ ፕሮጀክቱን በራሱ መንገድ ሲያሳካ የፍቅር ህይወቱ ግን ግራና ቀኝ የሚያመሳቅለው ሆኖ እናየዋለን። መጨረሻውን ለናንተ እተወዋለሁ።

ፊልሙ አዝናኝ ታሪክን በተዋዛና በቀላል መንገድ መናገር ችሏል፤ ያም ሆኖ "ማርትሬዛ" የራሱ ጥቃቅን ስህተቶች አላጣውም። ከእነዚህ ግር የሚያሰኙ ተጠቃሽ ክስተቶች መካከል አንደኛው ለአስር ዓመታት ውጪ ሀገር ቆይቶ የእነሃናን ቤተሰብ የተቀላቀለው ዶክተሩ በዛ መልኩ ወዲያው መዋሃድ መቻሉ ጥቂትም እንኳን ቢሆን ደንቀፍ የሚያደርግ የፀባይ ለውጥ እንዴት አላሳየም የሚያሰኝ ነው። ሁለተኛውና በጉልህ የሚነሳው ግን ዶክተሩ የመማሩንና የመብሰሉን ያህል አልፎ አልፎ ለነገሮች የሚሰጠው ስሜታዊ ምላሾች ከእርሱ የሚጠበቁ አይደሉም።

በተረፈ ግን "ማርትሬዛ" በቀላል እንደማይገኝ ጽኑ እና የከረመ ፍቅር በውለታና በገንዘብ ሳይሸነፍ በሦስት ወር ውስጥ ሲመነዘር የ1፡40 ደቂቃ ፊልም ነው።■

## አንዳንድ

በመስከረም አያሌው

# ቼ ጉቬራ ለሴት ልጁ የፃፈው የሰላምታ ደብዳቤ

### ፌብሪዋሪ 15/1996

ውዲቷ ሂልዳታ፤

ምንም እንኳን ብዙ ቆይቶ የሚደርስሽ ቢሆንም ይኼው አሁን እየፃፍኩልሽ ነው:: ስለ አንቺ ዘወትር አስባለሁ፤ መልካም የልደት ቀን እንዲሆንልሽ እመኛለሁ:: አሁን አንቺ አድገሻልና እንደ ልጅ ትናንሽ ተራ የሆኑ ነገሮችን አይደለም የምፅፍልሽ::

ጠላቶቻችንን የምችለውን ያህል ለመፋለም አሁንም በጣም ርቄ ነው የምገኘው፤ ለተወሰነ ጊዜም በዚሁ አይነት እቆያለሁ:: ይህ ያንንም ያህል ትልቅ ነገር ባይሆንም አንድ ነገር እየሰራሁ እንደሆነ ይሰማኛል:: በመሆኑም እኔ ያንቺው ነኝና በኔ በአባትሽ ኩሪ::

ልብ አድርጊ! አሁንም ገና ብዙ የትግል ዓመታት ከፊታችን አሉ:: አንቺም ሙሉ ሴት ስትሆኚ በትግሉ ውስጥ የራስሽን ድርሻ ትወጪያለሽ፤ እስከዚያው ድረስ ግን ራስሽን እያዘጋጀሽ ቆይ:: በጣሙን አብዮታዊ ሁኚ:: ይህን ማለት አንቺ ላንቺ ጎበዝ ተማሪ መሆን ማለት ነው:: ያለሽበት ዕድሜ ብዙ የምትማሪበት ነው:: ሁሌም ትክክለኛ የሆኑ ምክንያቶችን (ፍትህን) ለመደገፍ የተዘጋጀሽ ሁኚ:: እናትሽንም ታዘዢያት፤ ስሚያት፣ ሁሉንም ነገር እንደምታውቂ አድርገሽ ራስሽን አታስቢ:: ይሄ ከጊዜ ሂደት ጋር የሚመጣ ነው::

በትምህርት ቤትሽ ምርጥ ከሚባሉት መሀል ለመሆን ታገይ:: በማንኛውም ረገድ ምርጥ ሁኚ! አብዮታዊ አመለካከት ይኑርሽ:: ይህ ማለት በአንቺ እድሜ ብዙ መማርና ልምድን መቅሰም ማለት ነው:: ሁሌም ቢሆን ምክንያታዊና ተጨባጭ አመለካከቶችን ተከተይ!!

በትምህርት ቤት በማንኛውም ነገር ተፎካካሪ ለመሆን ሞክሪ:: ይህ ማለት ምን ማለት መሆኑ መቼም አንችን ይገባሻል፤ ይህ ማለት ብልጫ ያላት ተማሪና አብዮታዊ አመለካከት ያላት ሰው መሆን ናቸው:: በሌላ አነጋገር መልካም ስነ-ምግባር ማሳደር፣ ጠንቃቃ መሆን፣ የአብዮትና የጓዶች ፍቅረ ማሳደር ወዘተ. የመሳሰሉ ናቸው:: እኔ በአንቺ ዕድሜ ላይ በነበርኩ ጊዜ እንዲህ አልነበርኩም:: ሰው የሰው ጠላት በነበረበት የተለየ ማህበረሰብ ውስጥ ነበርኩ:: አንቺ የምትኖሪበት ግን ምቹ ሁኔታ ያለበት ሌላ ዘመን ነውና ተጠቀሚበት::

በቤት ውስጥም ትናንሾቹን መንከባከቡን፣ እንዲያጠኑ መምከሩን፣ መልካም ጠባይ እንዲኖራቸው ማድረጉን እንዳትዘነጊ:: እንደ ታላቅ እህቷ ላንቺ ልዩ አመለካከት ያላትን አሌይዲታን በተለይ አደራ:: እሺ፤ ትልቂቷ ወይዘሪት:: የልደት ቀንሽ የሚያስደስት እንዲሆን በድጋሚ እመኝልሻለሁ:: እናትሽንና ያንቺን ጊና ሳሚልኝ:: በዓይነ ስጋ እስከምንገናኝ ድረስ ደህና ሁኚ::

አባትሽ




## ስለምላሳችን አስደናቂ እውነታዎች

- ያስ ምላስ ማውራት፣ ማጣጣም እና መዋጥ አይቻልም።
- በአፋችን ውስጥ ከሚኖሩት ባክቴሪያዎች ግማሽ ያህሉ የሚኖሩት ምላሳችን ላይ ነው።
- ከሴቶች ምላስ ይልቅ የወንዶች ምላስ እርዝመት ይበልጣል።
- የምላስ ጡንቻ በሰውነታችን ውስጥ ከሚገኙት ጡንቻዎች ሁሉ ጠንካራው ነው።
- መደበኛው የሰው ልጅ ምላስ ቀለም ወደሮዝ ያደላ ቀይ ሲሆን፤ የምላስን ቀለም በማየት የዚያን ሰው የጤንነት ሁኔታ መገመት ይቻላል።
- ምላስ ለማጣጣም እርጥበት ሲኖረው ይገባል። ደረቅ ምላስ የጣዕሙን አይነት መለየት አይችልም።
- ልክ እንደጣት አሻራ ሁሉ የእያንዳንዳችን የምላስ አሻራ የተለያየ ነው።
- የዓለማችን ረጅሙ ምላስ ተብሎ የተመዘገበው ከጫፍ እስከጫፍ የ3 ነጥብ 86 ኢንች እርእመት ያለው ምላስ ነው።
- የዓለማችን ሰፊው ምላስ ደግሞ የ3 ነጥብ 1 ኢንች ስፋት ያለው ነው።
- ምላስ በጥርሳችን ላይ የሚቀሩ ምግቦችን ማፅዳት በመቻሉ የተፈጥሮ ንፅህና መጠበቂያ ይባላል።

## ስትዞሩ

አንዷ አባቷ አውሮፕላን ነጂ ነበርና “በዚያ አውሮፕላን ከቢሾፍቱ ተነስተን በመንዝ በኩል አድርገን መገዘዝ ላይ አያቶቻችን አሉና ከዚያ አርፈን ጠይቀን ተንሸራሽረን ተመለስን” ብላ ለአዲስ ፍቅረኛዋ ትነግረዋለች:: ፍቅረኛዋም “ተይ መዘዝ ላይ ምን ሜዳ አለና ታርፋላችሁ” ይላታል:: ሴቷም “መሀልሜዳ፣ ሞላሌ፣ አመፀኛ ዋና አጠገብ ዝቅ ብሎ ሰላድንጋይ፣ ጁሐር” እያለች ያልሆነ ነገር ስትቀበጣጥር ፍቅረኛዋ “እንዲያው ስትዞሩ ትውላላችሁ እንጂ አንቺና አባትሽ አታርፉም” ብሎ ቀለደባት::■

## ባልና ሚስት

ባልና ሚስት በትልቅ እንስራ አሞጭ የመሰለ ማር ይዘው ገበያ ወጥተዋል:: ባል እንጋሬም ይዞ ስለነበር ማሩን ለሚስቱ ሰጥቶ ገበያ ከመጣ ሽጪ ብሎ እንጋሬ ተራ ሄዷል:: በከተማ የታወቀ አንድ እብድ ደህና ሰው መስሎ ማር ሊገዛ በቅድሚያ ግን ልቅመሰው ይላል:: የዋህዋ ሴት መሸፈኛውን ገልጣ በል ቅመስ ትለዋለች:: እብዱም እያጣጣመ በአምስት ጣቱ መዛቅ ይጀምራል:: ባል ከሩቅ አይቶ በሴትየዋ እንክልቱነት አዝኖ “አንቺ ይህ እብድ ማሬን ሲጨርስ ዝም ብለሽ ታይዋለሽ? ብሎ እሳት ለብሶ እሳት ጎርሶ ይመጣል:: እብዱም የሚበቃውን ያህል ይዞ ገለል ብሎ ቆሟል:: “ማር እገዛለሁ፣ ልቅመሰው ብለውኝ እኮ እየቀመሱ ነው” ትላለች ሚስት:: ባልም “ ኧረ ይቺ መንገሌ ምን ይገዛል እብድ እኮ ነው” ብሎ ማሩን ሊሸፋፍን ገባ:: እብዱም “እንዲያ እያልክ ንገራት እንጂ!” ብሎ ፈረጠጠ ይባላል::

የፍቅር ስነቃል-
በዘሪሁን ክፍሌ

## መርፌና ክር

ክሩስ ተጠቀመ ልብስ ላይ ተሰፍቶ
በደግ ጓደኛው በመርፌ ተረድቶ
ምስኪኑ መርፌ ግን ይኖራል ሲለፋ
በራሱ ቀዳዳ ሌላውን ሲሰፋ

ምልክት -
በሳምሶን ይርሳው■

## ሽሙጥ

ሽሙጥ እንዴት ይጥፋ
ይኑር ለዘላለም
ለሀበሻ መጽናኛ
ሌላ ነገር የለም::

የኛ ነገር -
በግርማ ወ/ማርያም■

## መስቀልና ዙፋን

አንተ ያልከው ነገር በድፍረት በይፋ
እውነት ነው ተብሎ ጡሩንባ ተነፋ
ግን አንተ ያልከውን በእኔ አፍ ላይ ባወጣው
ቀጣፊ ተብዬ መስቀል ላይ በወጣሁ::

ጽሞና እና ጩኸት -
ከፋሲልከ

## ተነቅሼዋለሁ

አንገቴ ላይ ባስረው በክር አንጠልጥዬ
በጥው ወሰዱት ማተቤን ከላዬ
ቢጠነክር ብዬ በገመድ ደረብኩት
መቼ ፋታ ሰጡኝ ፈጥነው መነተፉት
ሳልታክት ሞክርኩኝ በወርቅና በብር
ባዶ አንገት አስቀሩኝ ማተቤን ሳላስር
ችግሬን ለመቅረፍ አሁን ዘዴ አገኘሁ
ማተቤን ባንገቴ ተነቅሼዋለሁ::■

## ኪነ-ጥበብ እና ባህል

# በረከተ መርገም

በጥበቡ በለጠ

በዚህ ርዕስ የተፃፈችው የኃይሉ ገ/ዮሐንስ /ገሞራው/ ግጥም በኢትዮጵያ ውስጥ ተፅዕኖ ፈጣሪ ከሚባሉት የግጥም ሥራዎች በሙሉ ከፊት የምትሰለፍ ናት። ይህች ግጥም ከ1959 ዓ.ም በኋላ የመጣውን ትውልድ በመቀስቀስ እና በማንቃት ሁሌም ትጠቀሳለች። አብዮተኛ ትውልድ ፈልስፋላለች የሚሉም አሉ። ከሁሉም በላይ ደግሞ ፀሐፊዋን ኃይሉ ገ/ዮሐንስን ለመከራ የዳረገች ነች። ከርሱ በተፃራሪ የቆሙ ወገኖች ሁሉ ኃይሉን የሚያጠቁበት፣ የሚያሳድዱበት ግጥሙ ሆነች። የመከራን፣ የስቃይን፣ የእስራትን፣ የስደትን መስቀል የተሸከመባት ግጥሙ ነች።

በቅርቡ ከዚህ ዓለም በሞት የተለየው የወግ ፀሐፊው መስፍን ኃብተማርያም፣ በ“በረከተ መርገም” ግጥም በከፍተኛ ደረጃ ከተመሰጡ ሰዎች መካከል አንዱ ነበር። ባለ 21 ገፅ የበረከተ መርገምን ግም ከ40 ዓመታት በላይ በቃሉ ይዞ እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ በቃሉ ያነበንብ ነበር። እንደውም “ተጓገዥ በረከተ መርገም” The walking B.M ይባል ነበር። ይህ ሰው በዚህች በበረከተ መርገም የግጥም መድብል ውስጥ አስተያየቱን በ1966 ዓ.ም ፅፎ ነበር። እንዲህ ይላል፡-

“ስለ በረከተ መርገም ያለኝን አስተያየት ከመጀመሬ በፊት ለብዙ ዓመታት ሳደንቀው የኖርኩትን ወደፊትም የማደንቀውን ግጥም በገጣሚና በአንባቢ አይን ተመልክቼ ለመተንተን ይህን ዕድል በማግኘቴ ደራሲውን ለማመስገን እወዳለሁ። በ1959 ዓ.ም በቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዩኒቨርስቲ በተደረገው የግጥም ውድድር በረከተ መርገም አንደኛ ሆኖ ተመርጦ ነበር።

“በዚያን ጊዜ ደራሲው ሲያነብ ይሰማ የነበረውን የጋራ ጭብጨባ በተለይም አንብቦ ሲጨርስ ውጤቱን ለመስማት ሳይጓጓ “በቃኝ” ብሎ አንገቱን አቀርቅሮ አዳራሹን ባጣበቡት ሰዎች መካከል እየተሹለከለከ ሲወጣ በአዳራሹ የነበረውን አድናቆት የተመላበት ትዕይንት አስታውሳለሁ። በረከተ መርገም በልቤ መስረፅ የጀመረው ያን ጊዜ ነበር። እስከ አሁንም ባነበብኩት ቁጥር ትዝታ ይቀሰቅስብኛል። ጥሩ ግጥምነቱ ካዘላቸው ጠቃሚ ሃሳቦች ጋር እየተጣመረ በረከተ መርገምን አንድ ግዜ በሙሉ በቃል አጥንቼው የነበረው። ለዚህ ይመስለኛል እስከ አሁንም ልረሳው ያልቻልኩት” መስፍን ኃብተማርያም።



**በረከተ መርገም በአፄ ኃይለስላሴ ዘመን መንግሥት ቢፃፍም በእርሳቸውም ዘመን ሆነ ቀጥሎ በመጣው በደርግ ዘመን ተፈላጊ አልነበረም**

የመስፍን ኃብተማርያም አስተያየት ሰፊ ነው። የበረከት መርገምን ግጥም ከልዩ ልዩ ማዕዘናት እየተነተነ የሚሔድ ነው። የገጣሚውንም ፍዳ ያሳያል።

በረከተ መርገም በአፄ ኃይለስላሴ ዘመን መንግሥት ቢፃፍም በእርሳቸውም ዘመን ሆነ ቀጥሎ በመጣው በደርግ ዘመን ተፈላጊ አልነበረም። ምክንያቱም የሰው ልጅ ታላቅነት፣ የተከበረና ሰብዓዊነቱ የተጠበቀ ዜጋ እንዲሆን እሱን የሚጨቁኑትን ሁሉ የሚራገም ግጥም ነው። ስለዚህ ለሰው ቁብ የሌላቸው ስርዓቶች

በገፅ 18

# የገሞራው በሀገሩ መቀበር ለምን ያስቆጣል?

በድንበሩ ስዩም



<u>ድግሪማ ነበረን</u>
ድግሪማ ነበረን በአይነት በብዛት፣
ከቶ አልተቻለም እንጂ ቁንጫን ማጥፋት
ድግሪማ ነበረን ከእያንዳንዱ ምሁር
አልተቻለም እንጂ ቅማልን ከሀገር።
ድግሪ ተሸክሞ መስራት ካልተቻለ
አሕያስ በአቅሟ ወርቅ ትጫን የለ!!
ድግሪማ ነበረን - ለወሬ የሚበጅ
ሞያሌን ከሐገር -አልነቀለም እንጅ።
ድግሪማ ነበረን - በሊቃውንት ተርታ
አልረዳንም እንጂ - ሊሸኝ ድንቁርና።
አይሸኙበትም እንጂ - ድግሪማ ነበረን
አልመከተም እንጂ - ድህነት ሲያጉላላን።
ጥሮ ተጣትሮ ድግሪማ ማግኘት
ለመሆን አልነበር - ለሰው መድሃኒት።

ገሞራው /ኃይሉ ገ/ዮሐንስ/

ይህን ከላይ የሰፈረውን ግጥም የገሞራው ነው ብላ የሰጠችኝ ኤሚ እንግዳ ነች። ግጥሙ ፊደልን የቆጠረውን ሁሉ የሚያሳስብ ብሎም የሚያስቆጭ ነው። ገሞራው እጅግ አያሌ የሥነ - ግጥም ስራዎቹን ሲፅፍ የኖረ ባለቅኔ እንደነበር የሚታወቅ ነው። ከሰሞኑ በወጡ መረጃዎች ወደ ዘጠኝ ሺ ግጥሞችን፣ አርቲክሎችን፣ ማስታወሻዎችን የቋንቋና የባሕል ጥናቶችን እንደፃፈ ተነግሮለታል። የሕይወት ዘመኑን በሙሉ ሲፅፍ የኖረ ‘ስደተኛው ሊቅ’ ነበር።

ስለዚሁ የሥነ-ፅሁፍ ምሁር ስርዓተ-ቀብር አስመልክተው የሚፅፉ የተለያዩ ድረ-ገፆችን ለማንበብ ሞክሬ ነበር። አንዳንድ ፀሐፊያን ገሞራው ለምን በሐገሩ ኢትዮጵያ ተቀበረ ብለው ሲወቅሱ ይደመጣሉ። ገሞራው በስደት እንደኖረ በሰደት ይቀበር ይላሉ። ይሔ አስተሳሰባቸው የመነጨው ደግሞ ገሞራው በነበረው የፖለቲካ አቋም ምክንያት ነው። ይህ ሰው በስልጣን ላይ ካለው መንግሥት ጋር ተፃራሪ ስለሆነ በኢትዮጵያ መቀበር የለበትም

በገፅ 18

በኪዳኔ መካሻ (የሕግ ባለሙያ)
Kidane1983@yahoo.com

# ፍቺና የንብረት ክፍፍል

***- ጋብቻ በፍቺ በሚፈርስ ጊዜ ፍ/ቤቶች ሲከተሉት የሚገባው የጋራ ንብረት ክፍፍል መርህ፣***

***- ተጋቢዎች በፍቺ ጊዜ ንብረቱን በአይነቱ መከፋፈል ካልተስማሙ ክፍፍሉ በምን መልኩ መደረግ አለበት?***

***- እስከ ፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር የደረሱ ሶስት የፍቺ ንብረት ክርክሮች ላይ ምን አስገዳጅ የሕግ ትርጓሜ ተሰጠ?***

እንዴት ናችሁ ሰላም ነው? የዛሬው ወጋችን አያምጣውና ጋብቻ ሳይሳካ ቀርቶ በፍቺ መለያየት ግድ በሚሆንበት ጊዜ በጋብቻ የተፈሩ የባልና የሚስት የጋራ ንብረቶች እንዴት ይከፋፈላሉ:: የፌዴራሉ የቤተሰብ ሕጋችን በዚህ ጉዳይ ላይ ምን ይላል? እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የደረሱ የፍቺ የንብረት ክፍፍል ሙግቶች ላይ ሰበር ምን አስገዳጅ ውሳኔዎችን ሰጠ? የሚሉትን ነጥቦች እንመለከታለን:: ፍቅርን፣ መተሳሰብን አብሮ በጋብቻ እስከ መጨረሻው መዝለቅን እንጂ ፍቺን መለያየትን ሕጎቻችንም ሆኑ ማንኛውም ሰው ግድ ካልሆኑ በስተቀር ማንም አይመርጣቸውም:: ሆኖም የማይፈለገው ፍቺ ግድ ሆኖ በሚመጣበት ጊዜ የጋራ ንብረት ላይ ውጤቱ ምን ይሆናል የሚለውን ማወቁ አይከፋምና እንቀጥል::

## 1.የሁለቱ ቤቶች ክፍፍል

ዶ/ር ደስታና ሲስተር አስቴር በጋብቻ ተሳስረው ኖሩ:: ነገር ግን ትዳራቸው መዝለቅ ተሳነውና በፍቺ ተለያዩ:: ፍቺውን ተከትሎ የተደረገው የጋራ ንብረት ክፍፍል ክርክር አስነሳ:: በወላይታ ሶዶ እና በሀዋሳ ከተማ ከሚገኙት ሁለት ቤቶች ማን የትኛውን ይውሰድ የሚለው ጉዳይ ነበር:: ከሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተጀመረው የሁለቱ ቤቶች ክርክር እስከ ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ደረሰና ፍ/ቤቱ በወላይታ ሶዶ የሚገኘው ቤት ለዶ/ር ደስታ በሀዋሳ የሚገኘው ቤት ደግሞ በሀዋሳ ስለምትኖር የበለጠ ስለሚጠቅመን ለሲስተር አስቴር እንዲሰጥና የሀዋሳው ቤት ዋጋ ከወላይታው ስለሚበልጥ ልዩነቱን ሲስተር አስቴር ለዶ/ር ደስታ እንዲከፈሉ ወሰነ::

በውሳኔው ያልተደሰቱት ዶ/ር ደስታ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔውን እቃወማለሁ:: የክልሉ የቤተሰብ ሕግ ይሄን አይፈቅድም እኔና የቀድሞ ሚስቴ ባልተስማማንበት የተሰጠው የቤቶቹ የክፍፍል ውሳኔ የሕግ ስህተት ስለተፈፀመበት ይታረምልኝ አሉ:: ሰበር አቤቱታውን መርምሮ ውሳኔ ሰጥቷል:: ውሳኔውን እናቆየውና ሌላ ሙግት እናንሳ

## 2.በእጣ የተከፈለው ንብረት

ወ/ሮ ጥሩ ወርቅና አቶ ታፈሰም በጋብቻ ተሳስረው የጋራ ንብረት አፍርተው ሲኖሩ ጋብቻው አልሰመረምና በፍቺ ተቋጨ:: የንብረት ክፍፍልን በተመለከተ ጉዳዩን ያየው የሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የቀድሞ ባልና ሚስቱ የጋራ ንብረት የነበሩትን ሁለት ቤቶች የትኛው ለማን ይሰጥ በሚለው እንዳልተስማሙ ስለተረዳ "ለምን በዕጣ አላካፍላቸውም" አለና ቤቶቹን በዕጣ እንዲከፋፈሉ ወሰነ:: ዕጣው ሲወጣ ወ/ሮ ጥሩወርቅ እድለኛ ነበሩና የተሻለ ዋጋ ያለው ቤት ወጣላቸው:: አቶ ታፈሰ የደረሳቸው ቤት ደግሞ ዋጋው ወ/ሮ ጥሩ ወርቅ ከደረሳቸው ቤት ያነሰ በመሆኑ የዋጋ ልዩነቱን ብር 31,585.65 (ሰላሳ አንድ ሺ አምስት መቶ ሰማንያ አምስት ብር ከስልሳ አምስት ሳምነቲም) ወ/ሮ ጥሩወርቅ ለአቶ ታፈሰ እንዲከፍሉና ልዩነቱ እንዲካካስ ወሰነ::

እድለኛዋ ወ/ሮ ጥሩወርቅ በዕጣው የተሻለው ቤት ቢደርሳቸውም በውሳኔው ስላልተስማሙ ሀዋሳ ለከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤት ውሳኔውን ሲያፀና ለደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቤቱታ ቢያቀርቡም እዚያም አልተሳካም::

ስለዚህ ጥቅምት 23/2003 ዓም አዲስ አበባ 6 ኪሎ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቀረቡ:: አቤቱታቸው እጣ ቢወጣልኝም በእጣ መከፋፈሉን አልተስማማሁበትም፤ በዕጣ የደረሰኝን ቤት ብወስድ እጎዳለሁ:: የቀድሞ ባሌ አቶ ታፈሰ አትጎጂም የሚል ከሆነ የኔን እጣ ልተውለትና ልዩነቱን እኔ ከፍዬ ለኔ በዕጣ የደረሰኝ ቤት ይውሰድ:: እኔ ደግሞ ለሱ የደረሰውን ቤት ልውሰድ" ስለዚህ በማልስማማበት እጣ ንብረቱን እንድንካፈል መወሰኑ አላግባብ ነው::

አቶ ታፈሰ ለሰበር አቤቱታው በሰጡት መልስ ወ/ሮ ጥሩወርቅ እጣ እንለዋወጥ በምትለው አልስማማም:: የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ግን እንከን ስለሌለበት ይፅናልኝ አሉ::

ሰበር ሰሚው ችሎት ውሳኔዎቹን ሲመረምር ቤቶቹን በእጣ እንዲካፈሉ ፍ/ቤቱ የወሰነው በራስ ተነሳሽነት እንጂ ተከራካሪዎቹ ክፍፍሉ በእጣ ይሁን ብለው ስለተስማሙ አለመሆኑንና ፍ/ቤቱ ወደ እጣ የሄደው ተፋቺዎቹ በስምምነት ለማከፋፈል ባለመቻላቸውና ንብረቱም በአይነት ሊከፋፈል የማይችል በመሆኑ እንደሆነ ተገነዘበ:: ጉዳዩን መርምሮ ተፋቺዎቹ ባልተስማሙበት መልኩ የጋራ ንብረት በዕጣ የማካፈል አማራጭ በሕግ ተቀባይነት አለው የሚለውን መርምሮ ውሳኔ ሰጥቷል:: ከውሳኔው በፊት አንድ ሌላ ሙግት እንይ::

## 3.ነባር ቤት በጋብቻ ውስጥ ስለታየ የጋራ ይሆናል

ወ/ሮ አየለችና አቶ በላቸው በፍቺ የፈረሰውን ጋብቻቸውን ተከትሎ ወ/ሮ አየለች የቀረቡትን የጋራ ንብረት ክፍፍል አቶ በላቸው መልስ ሰጡ:: አከራካሪዎቹ ንብረቶች በጉለሌ ክ/ከተማ የሚገኘው ወ/ሮ አየለች፣ ከአቶ በላቸው በፊት ከነበራቸው ባለቤታቸው ጋር በጋራ ያፈሩትና በሳቸውና በቀድሞ ባለቤታቸው ለወለዷቸው ልጆች ስም የተመዘገበ ነው:: አቶ በላቸውም ይህን ሳይክዱ ከወ/ሮ አየለች ጋር ከተጋባን በኋላ ቤቱ እንደአዲስ ፈርሶ ስለተሰራ የጋራ ነው ብለው ነው:: በተጨማሪ የብሎኬት ማምረቻና የገበያ ማዕከል በሱሉልታ ከተማ የሚገኝ የኢንቨስትመንት ስራዎች ክፍፍል ላይም በቀድሞ ባልና ሚስቶች የተከራከሩ ሲሆን ክርክሩን አስተናግዶ የወሰነው የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በጉለሌ የሚገኘው ቤት የጋራ ነው:: ብሎኬት ማምረቻው የገበያ ማዕከሉና የሱልልታው ንብረቶችም የጋራ በመሆናቸው አቶ በላቸው ግማሹን ለወ/ሮ አየለች ከፍለው ንብረቱን ያስቀሩ ሲል ወሰነ::

ወ/ሮ አየለች በውሳኔው ባለመስማማት ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ይግባኝ ብታቀርብም ውሳኔው ሊሻር አልቻለም:: ስለዚህ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል አቤቱታው ከጋብቻው ቀድሞ የነበረው ቤት በጋብቻ ውስጥ ስለታደሰ ብቻ የጋራ በመባሉ ሌሎች ንብረቶችን ባል የግምቱን ግማሽ ከፍለው እንዲያስቀሩ በመወሰኑ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚል ነው:: ለአቤቱታው መልስ የሰጡት አቶ በላቸው ውሳኔው የሚነቀፍበት ምክንያት የለም፤ ወ/ሮ አየለች የጉለሌውን ቤት የግምቱን ግማሽ ከፍላ እንድታስቀር ስለተወሰነላት እሱን ለማካካስ ነው፤ እኔ ሌሎች ንብረቶችን ግምት ግማሽ ሰጥቻት እንዳስቀር የተወሰነው ብለዋል:: የሰበር ውሳኔ ይቆየንና ለ3ቱም ክርክሮች አግባብነት ያለውን ሕግ እንመልከት::

> ***ፍቺውን ተከትሎ የተደረገው የጋራ ንብረት ክፍፍል ክርክር አስነሳ:: በወላይታ ሶዶ እና በሀዋሳ ከተማ ከሚገኙት ሁለት ቤቶች ማን የትኛውን ይውሰድ የሚለው ጉዳይ ነበር***

## 4. ፍቺና የጋራ ሀብት

የጋብቻ ግንኙነት ከሚፈጥራቸው መብትና ግዴታዎች መሀከል በጋብቻው በመፈፀም፣ በጋብቻ ውስጥ እና በፍቺ ጊዜ የሚኖሩ የግል እና የጋራ ጉዳዮች አሉ:: የጋራ እና የግል ንብረቶች ከነዚህ መሀል የትኩረት ነጥቦቻችን ናቸው:: ከሕገመንግስታችን እንነሳለን::

4.1 የእኩልነት መርህ፡- በሕገ መንግስታችን አንቀጽ 34(1) ላይ ለጋብቻ የደረሱ ወንድና ሴት በዘር በብሔር በሃይማኖት ልዩነት ሳይደረግባቸው ጋብቻ የመመስረት መብት አላቸው:: በጋብቻ አፈፃፀም በጋብቻ ዘመንና፣ በፍቺ ጊዜ እኩል መብት እንዳላቸው ደንግጓል:: ዝቅ ብሎ በአንቀጽ 35(2) ላይ የሴቶችን መብት በደነገገበት አንቀፅ ሴቶች በጋብቻ ከወንዶች ጋር እኩል መብት እንዳላቸው ተጠቅሷል:: ሌሎች ዝርዝር ሕጎችም መደንገግና ተፈፃሚ መሆን ያለባቸው ይህን ሕገ መንግስታዊውን የእኩልነት መርህ መሰረት በማድረግ ነው::

4.2 የፍቺ ውጤቶች፡- ሰኔ 27/1992 የወጣው የተሻሻለው የፌዴራል ቤተሰብ ሕግ ከያዛቸው ቤተሰባዊ ጉዳዮች አንዱ ጋብቻንና ፍቺን የሚያስከትሉአቸው ውጤቶች ናቸው:: ክልሎች ሕገ መንግስቱን በማይቃረን መልኩ የራሳቸውን የቤተሰብ ሕግ የማውጣት ስልጣን ስላላቸው ከባህላቸው ጋር የሚናበብ የራሳቸውን የቤተሰብ ሕጎችን አውጥተው በስራ ላይ ይገኛሉ:: የፌዴራሉ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ የፍቺን ውጤት ከመደንገጉ በፊት ጋብቻ በንብረት ላይ የሚያስከትለውን ውጤቶች ደንግጓል::

በአንቀፅ 57 ላይ የባልና የሚስት የግል ሀብቶችን በተመለከተ ጋብቻው ሲፈፀም የነበራቸው ንብረት የግላቸው እንደሆነ ይደነግጋል:: ከጋብቻው በኋላም ለውርስ ወይም ለስጦታ ለግላቸው ያገኙት ንብረት የግላቸው ነው:: ከጋብቻው በኋላ ባል ወይም ሚስት የግል ሀብቱ በሆነ ንብረት ለውጥ ያገኘው ንብረት የግሉ መሆኑ የማይቀር ሲሆን በግብይት የተገኙ ንብረቶች ግን ባል ወይም ሚስት በግል ገንዘባቸው የገዙት ወይም የግል ንብረታቸውን ሸጠው ባገኙት ገንዘብ የገዙት ንብረት የግላቸው የሚሆነው በአንቀፅ 58(2) መሰረት አንደኛችን ንብረቱ የግል ይባልልኝ የሚል ጥያቄ ሲያቀርቡና ፍ/ቤት ተቀብሎ ሲያፀድቀው ነው::

የጋራ የሚባል ብቶቻቸው በአንቀጽ 62 መሰረት ባልና ሚስት ከግል ጥሪታቸውና ከግል ወይም ከጋራ ንብረታቸው የሚያገኙአቸው ገቢዎች የጋራቸው ናቸው:: ከላይ በአንቀፅ 58(2) በተጠቀሰው መልኩ በፍ/ቤት የግል ካላስባሉት ከጋብቻው በኋላ በግብይት የሚገኝ ንብረት ሁሉ የጋራቸው ሲሆን በስጦታ ውል ወይም በኑዛዜ ካልተገለፀ በቀር ለተጋቢዎቹ የተሰጡ ንብረቶችም የጋራ ናቸው:: በተጨማሪ ንብረቱ በአንደኛቸው ስም ብቻ ቢመዘገብም አንደኛው ተጋቢ በማስረጃ ካላረጋገጠው በቀር ሕግ በአንቀፅ 63 መሰረት ንብረቱ የጋራ እንደሆነ ይገመታል:: በጋብቻ ውስጥ የግል ወይም የጋራ ንብረቶች የሚፈጠሩት በዚህ አግባብ ሲሆን በጋብቻ ውልም የግል የነበራቸውን ንብረት ሌላኛው ተጋቢ እንዲያስተዳድረው ወይም እንዲያዝበት ሊሰጠው ይችላሉ::

በፍቺ ጋብቻው በሚፈርስበት ጊዜ በንብረት በኩል የሚኖረውን ውጤት በአንቀጽ 85(4) መሰረት በስምምነት ወይም በጋብቻ ውላቸው መሰረት ይጣራል:: ሆኖም በሕግ ፊት ተቀባይነት ያለው የጋብቻ ውል ወይም ስምምነት ከሌላ ንብረት የሚጣለውን የሚከፋፈለው ሕጉ ባስቀመጣቸው ድንጋጌዎች መሰረት ነው::

የጋራ ሀብትን በተመለከተ የሚፀና ስምምነት ካላቸው በስምምነት መካፈላቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በአንቀፅ 90 መሰረት እኩል ይካፈላል:: ይህ ሕገ መንግስታዊውን የተጋቢዎች የእኩልነት መርህ የሚያጠነክር ነው::

ክፍፍሉ በእኩልነት ላይ ተመስርቶ እያንዳንዱ ከጋራ ሀብቱ የተወሰነ ንብረት እንደደረሰው በማድረግ በአይነት መካፈል እንዳለበት አንቀፅ 91(1) ይደነግጋል:: በአይነት እና እኩል ማካፈል ካልተቻለ ልዩነቱ በገንዘብ እንዲካካስ የሚደረግ ሲሆን እያንዳንዱ ተጋቢ ይበልጥ ጠቃሚነት ያላቸውን ንብረቶች እንዲያገኝ ይደረጋል::

ሆኖም ንብረቱ በአይነት ለማከፋፈል የማያመች ወይም የማይቻል ከሆነና ንብረቱን ከሁለቱ ለአንደኛቸው እንዲሸጥ ማስማማት ካልተቻለ በአንቀፅ 92 መሰረት በስምምነት ሸጠው እንዲካፈሉ ይደረጋል:: በአሻሻጡ ሁኔታ ላይ ተፋቺዎች ካልተስማሙ በአንደኛቸው ጥያቄ ንብረቱ በግልፅ ጨረታ ተሸጦ እኩል እንዲካፈሉ እንደሚደረግ ይደነግጋል:: በመሆኑም ፍቺን ተከትሎ የሚነሱ የንብረት ክፍፍል ክርክሮች በነኚህ ሕጎች አግባብ መወሰን አለባቸው::

## 5.በሶስቱ ክርክሮች ላይ ሰበር ምን አለ

ከላይ ባነሳናቸው እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የደረሱ ሙግቶች ከፍቺ ጋር የሚነሱ የንብረት ክፍፍሎች የሚካሄዱበት የሕግ አግባብ በተመለከተ በሕግ በተሰጠው ስልጣን መሠረት አምስት ዳኞች በተሰየሙበት አስገዳጅ የሕግ ትርጓሜ ሰጥቷል:: እሰቲ እንያቸው::

5.1 የሁለቱ ቤቶች ክፍፍል፡- ከላይ በተራ ቁጥር 1 ያነሳነው በሁለት የተለያዩ ቤቶች ክፍፍል አግባብ ላይ የተነሳውን ክርክር የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ውሳኔዎች ቅፅ 11 ላይ የታተመው በሰ/መ/ቁ 49171 ጥቅምት 16/2003 የተሰጠው ውሳኔ ይህን ብሏል::

የፍቺ የንብረት ክርክር የእኩልነት መርህ ድንጋጌዎች መከተል እንዳለበትና በክፍፍሉ ሂደትም የተከራካሪዎች ስምምነት መኖር አለበት:: በዚህ ጉዳይ በክፍፍሉ ላይ ዶ/ር ደስታ አልተስማሙ፤ ሲ/ር አስቴር ደግሞ እኔ ሀዋሳ ስለምኖር እሱ ከሀዋሳ ውጭ ስለሆነ የሀዋሳው ቤት ቢሰጠኝ የበለጠ ተጠቃሚ እሆናለሁ በሚለው ክርክራቸው መሰረት ነው ውሳኔው የተሰጠው:: ሆኖም ሁለቱም በቤቶቹ

በገፅ 21


ህይወት

# የተዘነጋው የቢሊዮኖች ሚና


በመስከረም አያሴው

ዓለማችን በታሪክ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ የወጣቶቿ ቁጥር በ2014 ዓ.ም 1 ነጥብ 8 ቢሊዮን ደርሷል:: ይህ ማለት ከዓለም ህዝብ 18 በመቶው እድሜው ከ15 እስከ 24 ዓመት ክልል ውስጥ የሚገኝ ወጣት ነው:: በማደግ ላይ ካሉ ሀገራት ህዝብ መካከልም 88 በመቶዎቹ በዚህ የወጣትነት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ናቸው" ሲል ስቴት ኮብ ወርልድ ፖፑሌሽን በ2014 ሪፖርቱ አመልክቷል::

ይህን ያህል ቁጥር ያላቸው የአለማችን ወጣቶች ታዲያ በአሁኑ ወቅት ትኩረት ከማግኘት ይልቅ በሌሎች ተሸፍነው እንደሚገኙ ነው የተገለፀው:: በመሆኑም እነዚህ ወጣቶች ይልቁንም ለተፈጠረው የሀብት እጥረት እንደ ምክንያት እየተቆጠረ ይገኛሉ:: በርካታ ሀገራት ወጣቶችን በፖሊሲያቸው፣ በህግ አወቃቀራቸው እና በውሳኔ ሰጪነት ውስጥ እያሳተፏቸው አይደለም:: እስከ 60 በመቶ የሚሆኑት በታዳጊ ሀገራት ያሉ ወጣቶች ትምህርት ቤት የማይሄዱ፣ በመደበኛ ሥራ ላይ ያልተሰማሩ ነገር ግን መደበኛ ባልሆኑ ስራዎች ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ:: ከ500 ሚሊዮን በላይ ወጣቶችም የቀን ገቢያቸው ከሁለት ዶላር በታች የሆነ እና ኑሮን ለመቋቋም ብርቱ ጥረት እያደረጉ የሚገኙ ናቸው:: ለእነዚህ ወጣቶች ትኩረት ካለመስጠት የተነሳም ከፍተኛ ቁጥር ያለው ወጣቶች ያሉባቸው ታዳጊ ሀገራት ከዓለማችን ደሃ ሀገራት መካከል ቀዳሚ ተጠቃሾች ናቸው::








በዚህ የወጣትነት የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ዜጎች በየሀገራቸው ሁለንተናዊ ተሳትፎ ማድረግ ባለመቻላቸው ከሁሉም ነገር የተገለሉ በመሆናቸው ከሌላው የህብረተሰብ ክፍል እኩል ያሉትን ነገሮች መጠቀም አልቻሉም:: በተለይ ይህ የወጣትነት የእድሜ ክልል አንድ ሰው ወደ ስነ-ተዋልዶ የሚገባበት፣ የወሲባዊ ግንኙነት ስሜት የበለጠ የሚዳብርበት እድሜ እንደመሆኑ በስነ-ተዋልዶ ጤና ዙሪያ ያላቸው እውቀት አነስተኛ መሆኑን የተባበሩት መንግሥታት የስነ-ህዝብ ልማት አስቀምጧል:: በተለይ ግሎባላይዜሽን፣ ስልጣኔ እና እየተቀየረ የመጣው የሰዎች የአኗኗር ዘይቤ ወጣቶች በስነ-ተዋልዶ ጤና ላይ ሰፊ እውቀት ከማጣታቸው ጋር ተደማምሮ ወጣቶች ከፍተኛ ስጋት ከፊት ለፊታቸው እንዲደቀን አድርጓቸዋል ተብሏል::

በወጣቶች ላይ ካንዣበቡት የስነ-ተዋልዶ ጤና ችግሮችም ያለ ዕድሜ ጋብቻ፣ ያልተፈለገ እርግዝና፣ ጥንቃቄ የጎደለው ውርጃ፣ ኤች አይ ቪ ኤድስ እና የአባላዘር በሽታ የሚጠቀሱ ናቸው:: የአባላዘር በሽታን በተመለከተ የተባበሩት መንግሥታት እንደገለፀው በየዓመቱ 340 ሚሊዮን አዲስ የአባላዘር በሽታ ተጠቂዎች የሚገኙ ሲሆን፣ ከእነዚህ ውስጥም አንድ ሶስተኛው እድሜያቸው ከ25 ዓመት በታች የሆኑ ወጣቶች ናቸው:: በየዓመቱ በኤች አይ ቪ ኤድስ አዲስ ከሚያዙት ዜጎች መካከልም ከግማሽ በላይ የሚሆኑት እድሜያቸው ከ15 እስከ 24 ዓመት ያሉ ወጣቶች ናቸው::

በሚገርም ሁኔታ ደግሞ ተመርምረው ራሳቸውን ያወቁት 10 በመቶ ወንዶች እና 15 በመቶዎቹ ሴቶች ብቻ ናቸው:: የዓለማችን ከአንድ ቢሊዮን በላይ የሚሆኑ ወጣቶች ወደ መራቢያ እድሜ እየደረሱ መሆኑን የገለፀው ሪፖርቱ፤ ከእነዚህ ወጣቶች መካከል ታዲያ ያለእድሜያቸው የልጅ እናት እንዲሆኑ የሚደረጉ በርካቶች መሆናቸውን ይፋ አድርጓል:: በዓለማችን ላይ ስምንት ሚሊዮን 50ሺ የሚሆኑ ሴቶች እድሜያቸው ከ15 ዓመት በታች ሆኖ አርግዘው ይወልዳሉ:: እንደ ሪፖርቱ በታዳጊ ሀገራት በሚገኙ እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች ከሆኑ ሴቶች 19 በመቶዎቹ በዚህ እድሜያቸው ያረግዛሉ::

እነዚህ ሴቶች ወደ ትምህርት ቤት በሚሄዱበት እድሜያቸው አርግዘው በመውለዳቸው ያለ እድሜያቸው ኃላፊነት ይጣልባቸዋል:: ባልጠነከረ ሰውነታቸው ፀንሰው ከመውለድ በተጨማሪም ከትምህርት ገበታቸው ላይ መቅረት፣ በቤት ውስጥ በተለያዩ የጉልበት ሥራዎች ላይ መሰማራት እንዲሁም ከእድሜያቸው ለጋነት እና ተስፋ ከመቁረጥ የተነሳ በሌሎች ተፅዕኖ ስር መዋል እና ስለራሳቸው መወሰን አለመቻል ያጋጥሟቸዋል:: የዓለማችን ዘጠና አምስት በመቶ ውልደት የሚከናወነው በታዳጊ ሀገራት እንደመሆኑ ይህን ያህል ወጣት ሴቶች በዚህ አይነቱ ሂደት ውስጥ አልፈው ተስፋቸው እንደሚሸሽ መገመት ይቻላል::

በሀገራችን ኢትዮጵያ ከሚከናወኑ በርካታ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አንዱ የሆነው ያለ እድሜ ጋብቻም የአለም ወጣቶች የሚጋሩት ችግር እንደሆነ ተገልጿል:: ልክ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ታዳጊ ሀገራት ወጣቶች ታዲያ ይህ ያለ እድሜ ጋብቻ እጅጉን እንደሚያሰጋቸው ተገልጿል:: በታዳጊ ሀገራት ከሚገኙ ዘጠኝ ወጣት ሴቶች መካከል አንዷ እድሜዋ 15 አመት ከመሙላቱ በፊት ትዳር ትመሰርታለች:: በአሁኑ ወቅት 50 ሚሊዮን የሚሆኑ ወጣት ሴቶች ያለ እድሜያቸው ሊዳሩ ይችላሉ ተብለው በስጋት ቀጠና ውስጥ ናቸው::

በአሁኑ ወቅት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ወጣቶች በለጋ እድሜያቸው ወደ ልጅ እናትነት የመሸጋገር አደጋ እንደተጋረጠባቸው የገለፀው የተባበሩት መንግሥታት፤ በዚህም የወጣቶቹ የወጣትነት እና የጎልማሳነት እድሜ መለያ እንደሌለው ያትታል:: ከእነዚህ የወጣትነት እርግዝና ጋር በተያያዘ የሚነሳው ደግሞ ጥንቃቄ የጎደለው ውርጃ ነው:: በዓለም ላይ ከሚከሰቱት ጥንቃቄ የጎደላቸው ውርጃዎች መካከል 44 በመቶዎቹ በማደግ ላይ ባሉ

**ኤች አይ ቪን የተመለከትን እንደሆነ ከአራት ኢትዮጵያውያን ወጣት ሴቶች አንዷ እንዲሁም ከአስር ወጣት ወንድ ኢትዮጵያውያን መካከል አንዱ ስለ ኤች አይ ቪ ምንነት በቂ የሆነ ግንዛቤም ሆነ ኤች አይ ቪን መከላከል እንደሚቻል አያወቅም**

ሀገራት የሚከናወኑ ናቸው:: በዓለማችን ላይ በየዓመቱ 3 ነጥብ 2 ሚሊዮን የሚሆኑ ጥንቃቄ የጎደላቸው ውርጃዎች በወጣት ሴቶች ይፈፀማሉ::

ጥንቃቄ የጎደለው ውርጃን ለመፈፀም የሚወስኑትም ወጣት ሴቶች ስለስነ-ተዋልዶ ጤና በአስፈላጊው ቦታ አስፈላጊ ውርጃ ማግኘት ባለመቻላቸው አንዱ ምክንያት ነው:: በተጨማሪም ጥንቃቄ የተሞላበት መረጃ አገልግሎት የሚሰጡ ባለሞያዎች እና የጤና ተቋማት አለመሟላት፣ በጥንቃቄ ውርጃ ለመፈፀም የሚያስፈልጉ የገንዘብ እና የመሳሰሉት ድጋፎች እጥረት እንዲሁም እርግዝናው እንዳይከሰት አስቀድሞ ለመከራከል የሚረዳ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ለማህበረሰቡ አለመለመድ እንደ ምክንያት የተቀመጡ ናቸው::

በየዓመቱ ከዓለማችን ህዝብ መካከል 340 ሚሊዮን ሰዎች አዲስ በአባላዘር በሽታ ይያዛሉ:: እነዚህ ሰዎች ደግሞ እድሜያቸው ከ15 ዓመት እስከ 24 ዓመት በሆናቸው ወጣቶች ላይ ነው:: በአሁኑ ወቅት በዓለማችን ላይ 2 ሚሊዮን እድሜያቸው ከ15 እስከ 19 ዓመት የሆናቸው ወጣቶች ከኤች አይቪ ጋር የሚኖሩ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 780 ሺዎቹ ሴት ወጣቶች ናቸው::

እነዚህ ሴት ወጣቶች ከባህል፣ በፆታዊ እናበተለያዩ ማህበራዊ ምክንያቶች የተነሳ ከወንዶች ይልቅ በከፍተኛ ደረጃ ለአባላዘር በሽታ የተጋለጡ ናቸው:: ነገር ግን ይህን የአባላዘር በሽታ ወሲብን በማዘግየት፣ ህክምና በማድረግ እና በሌሎችም መንገዶች መከላከል እንደሚቻል ግንዛቤው ያላቸው በጣም ጥቂት ሴቶች ብቻ ናቸው::

ያለ እድሜ ጋብቻም ሆነ ጥንቃቄ የጎደለው ውርጃ ዞሮ ዞሮ የእናቶች ሞትን በከፍተኛ ደረጃ እንዲከሰት ማድረጉ አይቀርም:: አንዲት ሴት በለጋነት እድሜዋ ጋብቻ ፈፅማ ልጅ ስትወልድ በሚፈጠረው የሰውነት አለመጠንከር፣ አነስተኛ ክብደት ያለው ልጅ መውለድ እንዲሁም ረጅም ጊዜ የሚወስድ ምጥ ምክንያት ሴቷ ለሞት የምትዳረግበት አጋጣሚ ከፍተኛ ነው:: በዓለማችን ላይ በየዓመቱ 70ሺ ወጣት ሴቶች በወሊድ ወቅት በሚፈጠር ውስብስብ ችግር ምክንያት ህይወታቸውን ያጣሉ:: እነዚህ ወጣት ሴቶች ታዲያ ወደ ትምህርት ቤት በመሄጃ፣ ወደ ሥራ አለም በመግቢያ እድሜያቸው ህይወታቸው ይቀጠፋል::

ይህ ሴቷ ያለ እድሜዋ የልጅ እናት ለመሆን በምትጥርበት ወቅት በአንዲት ወጣት ሴት ላይ የሚደርሰው ችግር ጉዳቱ በእርሷ ብቻ አያበቃም:: ጉዳቱ ለሚወለደው ህጻን፣ ቤተሰብ፣ ማህበረሰብ እና ሀገርም ጭምር ነው:: ከእነዚህ ወጣት ሴቶች ከሚወለዱ ህጻናት መካከል 1 ቢሊዮን የሚሆኑት አንድ ዓመት ሳይሞላቸው ህይወታቸው ያልፋል::

ወደ ኢትዮጵያ ስንመጣ የሚገኙት መረጃዎች ውስን ቢሆኑም ልክ እንደ ሌሎች ታዳጊ ሀገራት ሁሉ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች በችግሮች የተተበተቡ ናቸው:: ኤች አይ ቪን የተመለከትን እንደሆነ ከአራት ኢትዮጵያውያን ወጣት ሴቶች አንዷ እንዲሁም ከአስር ወጣት ወንድ ኢትዮጵያውያን መካከል አንዱ ስለ ኤች አይ ቪ ምንነት በቂ የሆነ ግንዛቤም ሆነ ኤች አይ ቪን መከላከል እንደሚቻል አያወቅም:: ያለ እድሜ ጋብቻ ከፍተኛ እንደሆነ በሚነገርባት ሀገራችን ካሉ ወጣት ሴቶች መካከል 41 በመቶዎቹ እድሜያቸው 18 ዓመት ከመሙላቱ በፊት ትዳር የመሰረቱ ሆነው ተገኝተዋል::

በኢትዮጵያም ሆነ በአንዳንድ በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት በተለይ ሴት ወጣቶችን በለጋነት እድሜያቸው ትዳር እንዲመሰርቱ ለማድረጋቸው ወላጆችም ሆኑ ማህበረሰቡ የሚያቀርቧቸው ምክንያቶች አሉ:: ከእነዚህ ምክንያቶች መካከልም ወላጆች በህይወት እያሉ እና በጠንካራ እድሜያቸው የልጆቻቸውን ወግ ማዕረግ ማየት መፈለጋቸው፤ ከጥሎሽ በሚገኘው ገንዘብ ኑሯቸውን ለማሻሻል፣ በሁለቱ ቤተሰብ መካከል ግንኙነት ለመፍጠር፣ ሴቷ ጨዋነቷን እንደጠበቀች ትዳር በመመስረቷ ከጨዋ ቤተሰብ መገኘቷን ለማስመስከር እንዲሁም ሴቷ በማህበረሰቡ በተደነገገው የትዳር እድሜ ማግባት ስላለባት የሚሉት ይገኙበታል::

# ዘመን የተሻገረው የከተማችን ወንዞች ብክለት

በአይቼው ደስአለኝ

አዲስ አበባ ከተማ ከተቆረቆረች ከ120 ዓመታት በላይ አሳልፋለች:: የስፍራው አቀማመጥም ከባህር ወለል በላይ ከ2780 ሜትር ከፍታ ባላቸው ተራሮች የተከበበ ሲሆን በተለይ በክረምት ወቅት ከፍተኛ የዝናብ መጠን ሲኖር ከተማዋን አቋርጠው የሚያልፉ በርካታ ጅረቶች በመሙላት አደጋን የማስከተል አቅማቸው ከፍተኛ ይሆናል:: በዚህ ወቅት ግን የሚያስከትለው ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ተጠራርጎ ወደ ከተማዋ ዳርቻዎች መውሰዱ ለተወሰነ ጊዜ ፋታ ቢሰጥም ከቀናት በኋላ ግን ወደ ወትሮው ብክለት ስለሚመለስ ነዋሪዎችን ማስመረሩን ይቀጥላል::

የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ባለፉት ግማሽ ምዕተ ዓመት በፈጣን የከተማ መስፋፋት በህዝብ ቁጥር ዕድገትና በኢንዱስትሪ መበራከት የተነሳ በከተማዋ የሚገኙ ወንዞች ለደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃነት በዋንኛነት ተመራጭ ሆነው ሲያገለግሉ ቆይተዋል::

በከተማዋ አነስተኛ ወንዞችን ሳይጨምር ሰባት ታላላቅ ወንዞች በዙሪያዋ ከሚገኙ ተራሮች ተነስተው ከተማዋን በማቋረጥ ያልፋሉ:: ከከተማዋ በስተሰሜንና ምዕራብ ተራሮች የሚነሱት ወንዞች ገባሮቻቸውን ይዘው ወደ ደቡባዊ ምስራቅ የሚያመሩ ሲሆን ዋንኛ የሚባሉትን ቡልቡላ፣ ቀበና ፣ አቃቂና ግንፍሌ ወንዞችን በማጠናከር ወደታችኛው ተፋሰስ ያመራሉ::

የከተማችን ወንዞች ከሰው ከሚወጣ እዳሪና ፍሳሽ በተጨማሪ በሌላ በአደገኛ የኬሚካል ንጥረ ነገሮች ማለትም ከጋራዥና ከኢንዱስትሪ በሚለቀቁ ክሮሚያም፣ አርሰኒክ፣ ኒኬል፣ መዳብ፣ ዚንክ፣ ማንጋንስ ካድሚያምና ኮብልት በተባሉ ኤለመንቶች ክፉኛ የተበከለ ነው:: እነኚህ ኬሚካሎች በውሃ ውስጥ የሚገኙ ህያው ነገርን በሙሉ ያወድማሉ:: ከዚህ በተጨማሪም በወንዞቹ ውስጥ በመሆናቸው በትነት መልክ ወደ ከባቢ አየር ሲመጡ የሰዎችን የመተንፈሻ አካላት በመጉዳት ከፍተኛ ተፅዕኖ ያሳርፋሉ::

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጥናት ይፋ እንዳደረገው በከተማችን የሚገኝ 35 ፋብሪካዎች የተበከለ ፍሳሽን ወደ ወንዞች ይበቃሉ:: እነኚህ ብክለቶች ከሰሜን አዲስ አበባ ተነስተው 13 ወረዳዎችን በማቋረጥ ወደ አባሳሙኤል ሃይቅ ይገባሉ:: ይህ ሃይቅም የሚገኘው ከከተማችን በስተደቡብ በ30 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ነው:: ጥናቱ እንዳረጋገጠው ከፋብሪካ የመነጨው በካይ ንጥረ ነገር በውሃና በወንዝ ዳርቻ በሚገኙ ፍጥረታት ላይ ጉዳት ያስከትላል:: ከሆስፒታል የሚለቀቁ ፍሳሾችና ደረቅ ቆሻሻዎችም ብክለቱን በማጠናከር የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ያደርጋሉ:: በአቃቂ ወንዝ የብክለቱ ዋንኛ ተሸካሚ ሲሆን ወደ አባ ሳሙኤል ሃይቅ ያመራል:: መነሻውም ከሰሜን ምዕራብ ከተማዋ ዳርቻዎች ከሚገኙ ተራች ነው:: ትንሿአቃቂ ወንዝ ከአቅራቢያው በመነሳት በወጣጫ ተራራን በማካለል ወደ አባሳሙኤል ያመራል:: በዚህም ከመነሻ እስከ መዳረሻው 40 ኪሎ ሜትሮችን ያቆራርጣል::

የከተማዋ ታሪክ እንደሚያመለክተው ኢንዱስትሪዎች፣ ሆስፒታሎችና ህንጻዎች ከመስፋፋታቸው በፊት ወንዞች እጅግ በጣም ንጹህ ነበሩ:: ነገር ግን ወንዞች በአሁኑ ወቅት ከህብረተሰቡ ግንዛቤ ማነስና በተገቢው የሚመለከተው አካል ቁጥጥር ባለማድረጉ የተነሳ የብክለት መንስኤ ሆነው በአካባቢ፣ በሰውና በእንስሳት ጤና ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ በማድረስ ላይ ይገኛሉ:: ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 44 ህዝብ ለኑሮዎቹ በሆነና ከብክለት በፀዳ አካባቢ የመኖር መብቱ የተጠበቀ ይሆናል ይላል:: ይህ ህግ ምን ያህል ተተግብሯል የሚለው ያው የሚታወቅ ነው:: ሕግ በወረቀት ላይ መፃፍ አንድ ነገር ሆኖ እንዲተገበር ማድረግ ደግሞ የሁሉም ባለድርሻ አካላት መረባረብን ይጠይቃል:: በተለይም ሕጉ የወጣለት ህብረተሰብ መብቱን የሚጠይቅና የሚያስከብር ካልሆነ ውጤታማ ይሆናል ማለት ዘበት ነው::

አቶ አዱኛ መኮንን የአዲስ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ምክትል ስራ አስኪያጅ ናቸው:: እንደ እርሳቸው ገለፃ የከተማዋ ወንዞች መበከል ከከተማዋ መቆርቆር ጋር በቀጥታ ይዛመዳል:: በዛን ወቅት የህብረተሰቡ ንቃተ ህሊና ገና እጅግና ያልዳበረ በመሆኑና የአካባቢ ጥበቃ ጉዳይም ጭራሹን የማይታወቅ ስለነበር ወንዞች በቆሻሻ ማስወገጃነት የተፈጠሩ አድርጎ የመውሰዱ ጉዳይ በጣም የተለመደ ነበር:: ይህን ሁኔታ ለመከታተል የህግም ሆነ የተቋም መሠረት አልነበረም:: ከዚያ በኋላ በነበሩት አስርታት ፋብሪካዎች እየተገነቡ ሲመጡም ፋብሪካዎች መገንባታቸውና የስራ እድል መፍጠራቸውን እንጂ የሚለቋቸው ፍሳሾች በአካባቢና በህብረተሰብ ጤና ላይ ሊያደርሷቸው የሚችሉትን ተፅዕኖዎች የሚመለከት ሁኔታ በፍፁም አለመኖሩ ችግሩ እየተንከባለለ መጥቶ አሁን ላለንበት ዘመን እንዲደርስ አድርጓል:: ፍሳሾች ታክመው እንዲለቀቁ የማድረጉ ጉዳይም የማንንም ትኩረት አላገኘም ነበር::

በአሁኑ ወቅት ሁሉም ኢንዱስትሪዎች ሆስፒታሎችና ሌሎች ተቋማት ጥልቅ ጥናት ከተደረገባቸው በኋላ በተቆረጠ የጊዜ ገደብ የብክለት ማከሚያ ማሽነሪዎችን በየተቋማቸው እንዲተክሉ ትዕዛዝ የተሰጣቸው ሲሆን ከዚህ ወቅት በኋላ ወደ ወንዝ የሚለቋቸው ፍሳሾች የታከሙ እንደሆነ ጥብቅ መመሪያ ተሰጥቷል:: ይህን ካላደረጉ ግን የህግ ተጠያቂነት እንደሚያስከትልባቸው ተገልፆላቸዋል:: የመጨረሻው ርምጃም ተቋማቱን እስከመዝጋት የሚደርስ ነው::

እንደ ምክትል ስራ አስኪያጁ ገለፃ አካባቢን በመበከልና ፍሳሽን ወደ ወንዞች በመልለቅ አንዳንድ ትላልቅ የመንግስት ተቋማት ጭምር ይታወቃሉ:: ስለሆነም ከችግሩ ውስብስብነት የተነሳ መፍትሄ ለመስጠት ከሚመለከታቸው ተቋማት በተጨማሪ የሌሎች ባለድርሻ አካላት ትብብርን ይጠይቃል:: "ወንዞች በየቀኑ በጣም በሚያሳዝን ሁኔታ እየተበከሉ ነው" የሚሉት አቶ አዱኛ ችግሩን ለመቅረፍ መስሪያቤታቸው በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት ደፋ ቀና እያለ እንደሚገኝ ተናግረዋል:: ለዚህ እንዲያግዝም ከጤና ቢሮና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተጋገዝ ስራው እየተከናወነ መሆኑም ለዚህ አብይ ማሳያ ነው ሲሉም ተናግረዋል:: በሆስፒታችና በተጠቀሱት ኢንዱስትሪዎችም ለሠራተኞች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ተከናውኗል:: የቁጥጥር ስራም የተሰራ ሲሆን ከዚህ ባለፈም ፍሳሾቻቸውን በተገቢው በማከም ወደ ወንዞች በማይለቁ 10 ኢንዱስትሪዎች ማስጠንቀቂያ የተሰጠ ሲሆን በስድስት ኩባያዎች ላይ ደግሞ ክስ ተመስርቶባቸዋል:: ወደፊትም ቢሮው ለሌሎች መቀጣጫና ትምህርት እንዲሆን በሚል ክስ የተመሰረተባቸውን ኩባንያዎች ለህዝብ ይፋ ያደርጋል::

በከተማ ግብርና የተሰማሩ ሙያተኞች በተለይ አትክልትን ከወንዞች በሚገኝ ውሃ በማምረት ለህብረተሰቡ ያቀርባሉ:: በተበከለ ውሃ የሚመረት ዕፅዋት ከብክለት ነፃ ሊሆን አይችልም:: ይህም በአካባቢና በሰው ጤና እንዲሁም በእንስሳት ላይ ጉዳት በማስከተል ላይ ይገኛል:: በዚህ ረገድ በርካታ አካባቢዎችን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል:: እንደሚታወቀው በተለምዶ ቄራ ተብሎ የሚታወቀው አካባቢ ጋራዦች ማምረቻ ተቋማትና አገልግሎት አቅራቢዎች የሚገኙበት እንዲሁም ቁጥሩ ከፍተኛ ነዋሪ የሚገኝበት አካባቢ ነው:: በዚያ አካባቢ ከተለያዩ ስፍራዎች በማምጣትና ቆሻሻን በማግበሰበስ በአካባቢው የሚያልፉ ጅረቶች ይገኛሉ:: ከአካባቢ ጋራዦች የሚለቀቀው የተቃጠለ ጋዝና የመኪና እጣቢ ወደ ውሃው ይገባል ቀላል የማይባል መሬት ከቄራ ጀርባ ጀምሮ እስከ መካኒሳ ባለው የወንዝ ዳርቻ ላይ ሰላጣ፣ ጎመን፣ ቆስጣ ወዘተ በስፋት ይመረታል:: ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በወንዝ ውስጥ እጅግ አደገኛ የሆኑ እንደ መዳብና ዚንክ የመሳሰሉ ንጥረ ነገሮች በአትክልቶች ስራ በመግባት ቅጠሎች ውስጥ ይደበቃሉ:: በተለይ ተቀቅሎ የማይበላ ሰላጣ ሰዎች ሲመገቡት ካንሰርን ጨምሮ ለተለያዩ በሽታዎች እንደሚያጋልጥ ሙያተኞች ይገልጻሉ:: በርግጥ በግብርና ስራ የተሰማሩት ሰዎች ለራሳቸው መተዳደሪያ የሚሆን ሥራ መፍጠር ቢችሉም በተጓዳኝ ለተመጋቢው ይዞ የሚመጣው ዳፋን በተገቢው የተረዱት አይመስልም:: ይህን በተመለከተም ለአምራቾቹ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በተለያዩ ወቅት ስለጉዳዩ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ትምህርት ቢሰጥም ስራው ግን እንደቀጠለ ነው:: የአትክልትና ቅጠላቅጠል ተመጋቢው ህብረተሰብ ቁጥርም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመሄድ ላይ ይገኛል:: የህክምና ባለሙያዎች እንደሚገልጹት በተበከለ ውሃ የሚለማ አትክልት ውስጥ በካይ ንጥረ ነገሮች ተመችቷቸው ይቀመጣሉ:: ሰው ከተመገባቸው በኋላም በሰውነት አካላት ውስጥ ክፍል ውስጥ ይቀመጣሉ:: ጉዳታቸው ወይም ምልክታቸው ግን በፍጥነት አይከሰትም:: ነገር ግን ከረጅም ዓመታት በኋላ ተፅዕኖአቸው መከሰት ይጀመራል:: ከዚያ በኋላም በህክምና ለመዳን ከፍተኛ ወጭን ያስወጣሉ:: በአዲስ አበባ ከተማ የወንዞች ብክለት ከዕፅዋትና ከሰው ላይ ከሚያደርሰው ጉዳት አልፎ በአቃቂ አካባቢ በከብቶች ላይ ጉዳት እያደረሰ እንደሚገኝ ከአመታት በፊት ተገልፆ እንደነበርና ይህን ጉዳዳይም ተበዳዮች ወደ ሕግ ወስደው ውሳኔ ለማግኘት በሂደት ላይ መሆኑ ከተሰማ በኋላ መጨረሻው ሳይታወቅ ለህዝብም ይፋ ሳይደረግ እንደቀረ አይዘነጋም::

ከዚህ አኳያ ችግሮቹን በሕግ አግባብ ለመፍታት የሚደረገው ጥረት እጅግ በጣም ደካማ መሆኑን መረዳት አያዳግትም:: በተለምዶ ሰዎች በድብደብና በመሰል ሁኔታዎች በአካላቸው ላይ ጉዳት ሲደርስ ጉዳዩ ሕግ ፊት ቀርቦ በአፋጣኝ ውሳኔ እንደሚያገኝ ይታወቃል:: ነገር ግን በብክለት አማካኝነት በተዘዋዋሪ ሁኔታ በሰው ጤና ላይ ለሚደርሰው ጉዳት የጠያቂም ተነሳሽነት አናሳ መሆንና የተጠያቂነት አለመኖር ችግሩን ለመፍታት ገና ረጅም ርቀት መጓዝ እንደሚጠይቅ አመልካች ነው::

በሌላም በኩል በከተማ የተበከሉ ወንዞችን እንደገና ለማንፃት በአንዳንድ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሙከራ እየተደረገ ሲሆን የተገኘውን ተሞክሮ ወደ ሌሎች አካባቢ ለማድረስ ጥረቱ መቀጠል ይኖርበታል:: ለምሳሌ በቀልና አካባቢ በግንፍሌ ወንዝ ዳር ቬቲቫር የተባለውን እስከ ሁለት ሜትር የሚደርስ ስር ያለውን ሳር በመትከል ቆሻሻው በተክሉ ስሮች አማካኝነት እንዲመጠጥ የማድረጉ ጥረት ተስፋን የሚሰጥ ውጤት ስላስገኘ እንዲስፋፋ ማድረጉ ጠቀሜታው የጎላ ነው:: የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣንም በበኩሉ የወንዝ ዳርቻዎችን በማጠርና በማጽዳት ወደ መናፈሻነት ለመቀየር ዕቅድ እንደነበረው አቶ አዱኛ የገለፀ ሲሆን ነገር ግን የከተማዋ የጂኦግራፊ አቀማመጥ ምቹ አለመሆን ወንዞች ከክረምት ወቅት አደጋ በሚያደርስ ደረጃ መሙላታቸው በለጋ ወቅት ደግሞ ጨራሹኑ መድረቃቸው ከዚህ በተጨማሪ በህዝብ ብዛትና ፍልሰት የተነሳ አብዛኛዎቹ የወንዝ ዳርቻዎች በህገ ወጥ ሰፋሪዎ በመወረራቸው የሁኔታው አዋጭነትና አጠያያቂ እንዳደረገው አመልክተዋል::

እንዲያም ሆኖ ግን ሁኔታው ከእነ ጭራሹ እንዲቀር አልተደረገም:: በከተማዋ ማስተማር ፕላን መሰረት የወንዝ ዳርቻዎች ሊታጠሩ የሚችሉበት ዝግጅት ለማድረግ ጥረት ይደረጋል:: ከዚያም አካባቢ ከሰውና ከእንስሳት ነፃ ሲሆን ባለሀብቶች መንግስትና ባለድርሻ አካላት በመተጋገዝ አካባቢው ሰዎች የገቢ ማስገኛ መናፈሻ የማድረግ ዕቅድ አለ:: ውጤቱም ወደፊት የሚታይ ይሆናል::

# ስሥራ አዎንታዊ አመለካከት ይኑርህ

በአስሙ ታዬ

የምትሠራው ሥራ የአእምሮ ሥራ ወይም የጉልበት ሥራ አሊያም ደግሞ ሁለቱንም የሚያጠቃልል ሊሆን ይችላል፤ ይሁንና በየትኛውም የሥራ መስክ ቢሆን "ለፍተው የሠሩት ሁሉ ትርፍ እንደሚያስገኝ ማወቅ ያስፈልጋል። ጠንክረን መሥራታችን የሚያስፈልጉንን ቁሳዊ ነገሮች ለማሟላት ያስችለናል።

በመሆኑም ሥራ ግባችን ላይ እንድንደርስ የሚረዳን መሣሪያ ነው ሊባል ይችላል። ሥራ ኃላፊነታችንን በአግባቡ እንድንወጣ ያስችለናል። ራስህን መቻል ትልቅ ስኬት ነው። የሚያስፈልግህን ነገር መግዛት ከቻልክ ከሥራ ማግኘት ያለብህን ጥቅም እያገኘህ ነው ሊባል ይችላል።

ከዚህም በላይ ጠንክሮ መሥራት ለራሳችን አክብሮት እንዲኖረን ይረዳናል። ጠንክሮ መሥራት ድካምና ልፋት እንደሚጠይቅ ግልጽ ነው። ሥራችን አሰልቺ ወይም ከባድ ቢሆንም እንኳ ከራሳችን ጋር ታግለን በትጋት መሥራታችንን የምንቀጥል ከሆነ ግን የሚፈልግብንን ነገር እያደረግን እንደሆነ ስለምናውቅ የአእምሮ እርካታ እናገኛለን። ስለሆነም ሥራ ከፍተኛ እርካታ ያስገኝልናል።

## በሥራህ ውጤታማ ሁን

አንድ ሰው ምንም ጥረት ሳያደርግ በሥራው ውጤታማ ሊሆን አይችልም። ደግሞም ብዙ ሰዎች በደንብ የማይችሉትን ሥራ ማከናወን አያስደስታቸውም። ምናልባትም ብዙዎች በሥራቸው የማይደሰቱት በሥራቸው ውጤታማ ለመሆን አስፈላጊውን ጥረት ስላላደረጉ ይሆናል።

እንደ እውነቱ ከሆነ አንድ ሰው ለሚሠራው ማንኛውም ሥራ ተገቢ አመለካከት ካለው ማለትም በሥራው ውጤታማ ለመሆን የሚጥር ከሆነ ከሥራው ደስታ ማግኘት ይችላል። አንድን ሥራ አቅምህ በፈቀደው ሁሉ ሠርተህ ውጤቱን ስትመለከት እርካታ ታገኛለህ። አቋራጭ መንገድ የምትፈልግ ወይም የሚጠበቅብህን ብቻ በማድረግ የምትወሰን ከሆነ ግን እንዲህ ዓይነት ስሜት አይኖርህም።በማለት የስነ ልቦና ባለሙያዎች ይመክራሉ።

## ሥራህ ምን ጥቅም እንደሚያስገኝ አስብ

ከሥራህ ስለምታገኘው የገንዘብ መጠን ብቻ ከማሰብ ተቆጠብ። ከዚህ ይልቅ ራስህን እንደሚከተሉት ያሉትን ጥያቄዎች ጠይቅ፦ 'ይህ ሥራ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? ሥራው በትክክል ሳይሠራ ቢቀር ወይም ጭራሹኑ ባይሠራ ምን ሊፈጠር ይችላል? ሥራዬ ለሌሎች ጥቅም የሚያስገኘው እንዴት ነው?'

በተለይ በመጨረሻው ጥያቄ ላይ ማሰብ ጥሩ ነው፤ ምክንያቱም ከሥራችን የበለጠ እርካታ የምናገኘው ሥራው ሌሎችን እንዴት እንደሚጠቅማቸው ስንመለከት ነው። ደንበኞቻችንና አሠሪዎቻችን ከእኛ አገልግሎት በቀጥታ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ የታወቀ ነው፤ ሆኖም ሥራችን ጥቅም የሚያስገኘው ለእነዚህ ሰዎች ብቻ አይደለም። የቤተሰባችን አባላትና ሌሎች እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ሰዎችም እኛ ከምንሠራው ሥራ ጥቅም ያገኛሉ።

አንድ አባወራ የቤተሰቡ አባላት የሚያስፈልጋቸውን ለማቅረብ ጠንክሮ የሚሠራ ከሆነ ቢያንስ በሁለት መንገዶች ይጠቅማቸዋል። አንደኛ፣ ለኑሮ የሚያስፈልጓቸውን ቁሳዊ ነገሮች ማለትም ምግብ፣ ልብስና መጠለያ እንዲያገኙ ያደርጋል። ይህን በማድረግም 'የራሱ ለሆኑት የሚያስፈልጋቸውን ነገር እንዲያቀርብ' ተፈጥሮ የሰጠውን ኃላፊነት ይፈጽማል።

ሁለተኛ አንድ ታታሪ የቤተሰብ አስተዳዳሪ ጠንክሮ መሥራት ያለውን ጥቅም ለልጆቹ በተግባር ያስተምራል። "አንድ ሰው ጠንክሮ በመሥራት ረገድ ምሳሌ የሚሆን ሊሆን ይችላል። አንድ ሰው የእጅ ሙያ ኖሮት ሰዎችን የሚጠቅሙ ነገሮችን መሥራቱ ምን ያህል እርካታ እንደሚያስገኝለት ከእሱ መማር ይቻላል።

ለራሳችንና ለቤተሰባችን የሚያስፈልገውን ነገር ለማቅረብ ጠንክረን የምንሠራ ከሆነ እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ሌሎች ሰዎችም ለመርዳት የሚያስችል አቅም ይኖረናል። በመሆኑም ጠንካራ ሠራተኛ መሆን የሚያስገኘውን ደስታ እንድናጣጥም ያስችለናል።

## የሚጠበቅብህን ብቻ በማድረግ አትወሰን

የሚጠበቅብህን ብቻ በመሥራት ከመወሰን ይልቅ ከሚጠበቅብህ በላይ ማድረግ የምትችልባቸውን መንገዶች ፈልግ። ግብ አውጣ፤ ሥራህን ከበፊቱ በተሻለ ጥራት ወይም ቅልጥፍና ለማከናወን ጥረት አድርግ። ጥቃቅን ነገሮችን ሳይቀር በጥራት ለመሥራት ሞክር።

ከሚጠበቅብህ በላይ ለመሥራት የምትጥር ከሆነ ሥራህ ይበልጥ አስደሳች ይሆንልሃል። ምክንያቱም ሥራህ በአንተ ቁጥጥር ሥር እንደሆነ ይሰማሃል። ተጨማሪ ነገር እያደረግክ ያለኸው ሌላ ሰው ስላስገደደህ ሳይሆን በራስህ ፍላጎት ነው። "የትጉ ሰዎች እጅ ገዢ ትሆናለች፤ ሥራ ፈት እጆች ግን ለባርነት ይዳረጋሉ" የሚለው ሀይማኖታዊ አስተምህሮት ጠቃሚ ሐሳብ ይሆናል። እርግጥ ነው፣ አንዳንድ ሰዎች አሁንም ቃል በቃል በባርነት ሥር ሊሆኑ ይችላሉ፤ ወይም ደግሞ የግዳጅ ሥራ ያከናውኑ ይሆናል። ይሁን እንጂ የሚጠበቅበትን ነገር ብቻ በማድረግ የሚወሰን ሰው ሁልጊዜ የሚያከናውነው ሌሎች የሚነግሩትን ብቻ ስለሆነ በባርነት ሥር እንዳለ ሊሰማው ይችላል።

**አንድ ሰው ጠንክሮ በመሥራት ረገድ ምሳሌ የሚሆን ሊሆን ይችላል። አንድ ሰው የእጅ ሙያ ኖሮት ሰዎችን የሚጠቅሙ ነገሮችን መሥራቱ ምን ያህል እርካታ እንደሚያስገኝለት ከእሱ መማር ይቻላል**

በራሱ ፍላጎት ተነሳስቶ ከሚጠበቅበት በላይ ለማድረግ ፈቃደኛ የሆነ ሰው ግን ሕይወቱ በራሱ ቁጥጥር ሥር እንደሆነ ይሰማዋል። ይህ ሰው የራሱ ጌታ ይሆናል ማለት ነው።

## ለሥራ ከልክ ያለፈ ቦታ አትስጥ

ጠንክሮ መሥራት ጥሩ እንደሆነ የታወቀ ነው፤ ሆኖም ሕይወት ማለት መሥራት ብቻ እንዳልሆነ ማስታወሳችን ጠቃሚ ነው። እርግጥ ነው በትጋት መሥራት እንዳለብን ይታወቃል። ይሁን እንጂ የሥራ ሱሰኛ መሆን አይበረታታም። "ብዙ በመልፋትና ነፋስን በማሳደድ ከሚገኝ ሁለት እፍኝ ይልቅ ጥቂት እረፍት በማድረግ የሚገኝ አንድ እፍኝ ይሻላል" የሚለው ጥቅስ የሚያስተላልፈው ፤ አንድ ሰው ሥራው ጊዜውንና ጉልበቱን ሙሉ በሙሉ የሚያሟጥጥበት ከሆነ በሥራው ውጤት የሚደሰትበት ጊዜ አይኖረውም። በመሆኑም ሥራው 'ነፋስን የማሳደድ' ያህል ትርጉም የለሽ ይሆንበታል እንደማለት ነው።

ሥራችንን በትጋት ማከናወን እንዳለብን የሚናገር ቢሆንም 'ይበልጥ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ለይተን ማወቅ ይገባናል።

በህይወታችን ውስጥ ይበልጥ አስፈላጊ የሆኑት ነገሮች ምንድን ናቸው? ከእነዚህ ነገሮች መካከል ከቤተሰብና ከወዳጆች ጋር ጊዜ ማሳለፍ ይገኝበታል። ለቤተሰቦቻቸው ተገቢውን ቦታ የሚሰጡ ሰዎች ደስታ ያገኛሉ።

ከመረጃ መረብ ተ ወስዶ የተስተካከለ■





# ትዝብትን በጨዋታ

በአሸናፊ ደምሴ ......... demissieashenafi@gmail.com

# “ከማይረባ ጉልበት፣ ል’ባርጉልኝ ማለት”

ኀበዝ ዘንድሮ ሕግን ብቻ ሳይሆን አቅምንም አለማወቅ ከተጠያቂነት አያድንም:: አንበሳ ባለበት ጫካ ውስጥ ውሻ ለአደን እንደማይገባ ሁሉ፤ ጅብ ባለበት ዋሻ ውስጥ አህያ እንደማታናፋ ሁሉ “አቅምን አውቆ መኖር ጥሩ ነው፤ ታላቅ ችሎታ ነው” ብሎ ዞር ማለቱ ማንን ገደለ?

እውነቱን ለመናገር “ከማይረባ ጉልበት፣ ልብ አርጉልኝ ማለት” አስር እጅ ሳይሻል አይቀርም:: እዚህች’ጋ አንዲት ወጣ ትዝ አለችኝ::. . . ሰውዬው በሚስቱ ፀብ የለሽ በዳቦ ምክንያት ከጎረቤቱ ጋር ይጣላል:: የጎረቤታሞቹ የፀብ ንትርክ ግለቱ እየጨመረ፤ ጩኸቱ እየከረረ፤ ወደዱላ ተቀየረ:: በዚህ ጊዜ የነገረኛዋ ሴትዮ ባል ከአንዴም ሁለት፣ ሶስቴ ደህና ደህና ቡጢ አርፎበት ኖሮ እንደቦክሰኛ ተዘረረ::

ከቆይታ በኋላ ሲነቃ ቤቱ መደብ ላይ ተዘርግቶ ራሱን አገኘሁ:: ታዲያ ሚስቱ ወትሮም ነገረኛ ነበረችና ባሏን ከማስታመምና ከመንከባከብ ይልቅ በነገር ትጎነታትለው ጀመር:: “ እኔ የምለው አሁን አንተ ለዚህ ሽንፍላ ሰውዬ አንሰህ ነው? አንተም የምትበላው አንድ እንጀራ፤ እርሱም የሚበላው አንድ እንጀራ ምን አባክ ሆነህ ነው የተዘረርከው?. . . አንተን ብሎ ባል! ወንድ አሰዳቢ” ብትለው ሰውዬውም አቅሙን ያውቅ ኖሮ፣ “የኔ እመቤት ለነገሩማ ሁላችንም የምንበላው አንድ እንጀራ ነው፤ ዳሩ ግን ወጡስ!?” ሲል የምግብ አሰራሯን ሁኔታ በጎን ነገራት አሉ::

እስይ እንዲህ እንነጋገር እንጂ እኛስ ብንሆን የምንበላው ያው እንጀራ አይደለም እንዴ? የቸገረን “ወጡ” ነው እንጂ:: ሰው እንደቤቱ እንጂ እንደጎረቤቱ መች ይኖርና? መስሪያ ቤቶቹ ከመስሪያ ቤቶች፤ ተቋማት ከተቋማት፤ ኮሌጆች ከኮሌጆች፤ መምህራኖች ከመምህራኖች ተማሪዎችም ከተማሪዎች የሚለያዩት “በወጡ” ምክንያት ነው::

በአንዱ መስሪያ ቤት ውስጥ የሚሰሩ ሰዎች ወጣቸው ደሞዛቸው ነው:: ወጣቸው የሚያገኙት ምስጋናና ክብር ነው፤ ወጣቸው እውቅናቸው ነው:: አንድ ተቋም ለሠራተኞቹ ጥሩ ደሞዝ ቢከፍል፤ መልካም ማበረታቻ ቢያደርግ፣ እውቅናና ምስጋናን በመስጠት ምቹ የስራ ቦታን ቢያመቻች ውጤቱን ሳይውል ሳያድር ያገኘዋል:: በምን ቢባል ሰራተኛው ወጡን ማለትም ደሞዙን፣ ምስጋናውን፣ እውቅናውንና ምቹ የስራ አካባቢን ካገኘ የተሻለ ለምርታማነት መትጋቱ አይቀርም::

በሬ ጉልበት አግኝቶ፣ በልቶና ጠጥቶ ገበሬውን የበለጠ ይረዳው ዘንድ አሞሌ ጨው ቢያልሰው መልካም እንደሆነ ሁሉ ሰውም ተግቶ ይሰራ ዘንድ መደገፉና ማበረታታቱ አቅምን ከፍ የሚያደርግ “ወጥ” እንደሆነ ልብ ሊባል ይገባል::. . . እዚህች’ጋ ለጨዋታችን ማዋዣ ትሆን ዘንድ አንዲት የጋብሮቮችን ተረት ልጥቀስ::

ጋብሮቭ ነጋዴዎች ፈረሶቻቸው ዳገት በቀላሉ እንደወጡላቸው ሲፈልጉ፤ በከረጢት ገብስ ይሞሉና ከፈረሱ ኋላ ጋሪው ላይ ተቀምጠው በረጅም እንጨት በማሰር ከፈረሱ ፊት ላይ ያንጠለጥሉታል:: በዚህም መላ ሳቢያ ፈረሱ ገብሱን ከአሁን - አሁን አገኘሁት እያለ አንገቱን አስግጎ ሲገሰግስ በአንድ አፍታ ካሰቡበት ይደርሳሉ ማለት ነው::

በፍቅርም ውስጥ ቢሆን “ወጡስ?” የሚያስብሉን ብዙ ነገሮች አሉ:: ፍቅር የማናውቅ፣ የምንጨቃጨቅ፣ የምንነታረክና ሰላም የምንነሳ አይነት ሰዎች ሆነን ኋላ ላይ ፍቺው ሲመጣ “ፍቅሬን ሜዳ ላይ ጥሎ ጠፋ!” እንባባላለን:: ሲደመር የፍቅር ቅመሙ (ወጡ) የሚባሉት እነመተሳሰብ፣ እነመቻቻል፣ እነመተዛዘንና እነመተማመን ከሌሉ ፍቅሩ የሰይጣንን ጉልበት እንዴት ተቋቁሞ ሊቀጥል ይችላል:: ሰውዬው እንዳለው፤ “ሁለታችንም የምንበላው አንድ እንጀራ ቢሆንም ልዩነታችን ወጡ ላይ ነው” የሚያስብል መገማመቻ እንዳይኖር ጠንቀቅ ማለቱ አይከፋም::

> እርሱም የሚበላው አንድ እንጀራ ምን አባክ ሆነህ ነው የተዘረርከው?. . . አንተን ብሎ ባል! ወንድ አሰዳቢ” ብትለው ሰውዬውም አቅሙን ያውቅ ኖሮ፣ “የኔ እመቤት ለነገሩማ ሁላችንም የምንበላው አንድ እንጀራ ነው፤ ዳሩ ግን ወጡስ!?”

ሰው የዘራውን ነው የሚያጭደው:: ልጆች እንኳን በህፃንነት ዘመናቸው የሚገባቸውን እንክብካቤና አመጋገብ አግኝተው ካላደጉ፤ አቋማቸውም ሆነ አስተሳሰባቸው ያዘገመ እንደሚሆን ሳይንስ ይመሰክራል:: ስለዚህ እንጀራው አንድና ተመሳሳይ ቢሆንም “ወጡ” ግን አንዳችን ከሌላችን የመለያያችን ምክንያት ሊሆን ይችላል ማለት ነው::

ለዛሬ ከመሰነባበታችን በፊት፤ ከማይረባ ጉልበት ልብ አርጉልኝ ማለት የምትለዋን ለማጉላት የምትሆነኝን አንዲት የአፄ ቴዎድሮስን ታሪክ እንካችሁ:: ታሪኳን ያገኘኋት ማርቆስ የሻነው ካዘጋጁት “አፄ ቴዎድሮስ፤ የሺህ ዓመቱ ጀግና አጫጭር ታሪኮች” የተሰኘ መፅሐፍ ነው::

ካሳ (በኋላ አፄ ቴዎድሮስ) ራስ አሊን ድል ካደረጓቸው በኋላ ወደመጡበት ለመመለስ በደጋ ዳሞት በኩል ሲያልፉ የአካባቢው ህዝብ አጠቃቸው:: የአካባቢው ህዝብ በተከታታይ ውጊያዎች ከተዳከመው የካሳ ሰራዊት ፈረስና በቅሎ መማረክ ቻለ:: በየጥሻው እየተደበቀና አፋፍ ላይ እየሆነ፣ “የጎሹን ደመኛ የአሊን ወደረኛ ትለቀዋለህን?” እያለ በመፎከር በጣም አስቸገረ:: ያላሰቡት ችግር ያጋጠማቸው ካሳም በሆደሰፊነት የባላገሩን ትንኮሳ ሲታገሱ ቆዩ::

የአካባቢው ህዝብ ጥቃት ግን ይበልጥ እየጨመረ ሄደ:: በዚህ ምክንያት ካሳ ወታደሮቻቸው ከህዝቡ ጋር ውጊያ እንዲገጥሙ ትዕዛዝ አስተላለፉ:: በርካታ የአካባቢው ህዝብም ተገደለ:: አንዲት ባሏ ከካሳ ወታደሮች ፈረስ ለመዝረፍ ከቤቱ ወጥቶ የተገደለባት ሴትም በለቅሶ ላይ፤ የሚከተለውን ተቀኘች::

አመጣለሁ ብሎ
የካሳን ፈረስ፣
ሳያርመው ሞተ
የዘራውን ገብስ::

. . . እናላችሁ “ከማይረባ ጉልበት፣ ልብ አርጉልኝ ማለት” የዘራነውን እንኳን እናጭድ ዘንድ ዕድሜ ይሰጠናልና መታገስ ደግ ነው፤ ቸር እንሰንብት::

## ኪነጥበብ-ዜና


በአሸናፊ ደምሴ

## “የሸገር ወጎች 2” መጽሐፍ ለንባብ በቃ

የ“ቦሌ ፒኮክ ጋ ጠብቂኝ” እና “የሸገር ወጎች” መጽሐፍ ደራሲ የሆነው ጋዜጠኛ ሰለሞን ታደሰ ሦስተኛ ስራውን “የሸገር ወጎች - 2” በሚል ለንባብ አበቃ::

ከሃያ ያላነሱ ወጎችና እውነተኛ ታሪኮች የተካተቱበት ይህ መጽሐፍ በውስጡ የተለያዩ ትርከቶችን ይዟል:: ከአዲስ አበባ እስከ ዱባይ የተዘረጋን ስውር መስመር ተከትሎ እውነተኛ ታሪኮችን የሚያስነብበው መጽሐፉ፤ በከተማችን ውስጥ ያሉ ነጋዴ ሴተኛ አዳሪዎችንና ታዋቂ ሰዎችን ምስጢር ይገላልጣል:: “የሸገር ወጎች 2” መጽሐፍ የገፁ ብዛት 182 ሲሆን፤ ዋጋው ደግሞ 50 ብር ከ90 ሳንቲም መሆኑ ተጠቅሷል::

ጋዜጠኛ ሰለሞን ታደሰ ከዚህ ቀደም ያሳተመው “ቦሌ ፒኮክ ጋ ጠብቂኝ” የተሰኘ መጽሐፍ ከእስራኤል ሀገር በመጡ ሁለት ኢትዮጵያውያን ባለሀብቶች አማካኝነት በተመረጡ አርቲስቶች ተተርኮ በሲዲ ለገበያ ሊቀርብ መሆኑንም ነግሮናል:: “በተውኩት” የሚል ርዕስ በተሰጠው በዚህ የትረካ ሲዲ ውስጥ የተመረጡ ወጎች በድምፅ ተቀናብረው ቀርበዋል ብሏል:: ከሲዲው ሽያጭ የሚገኘው ገቢም ሙሉ በሙሉ ለወላጅ አልባ ህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት ይውላል ተብሏል::■




## “አዲስ ፎቶ ፌስት” አውደ-ርዕይ በሸራተን ተካሄደ

ከ35 አገራት የተውጣጡ ከ95 በላይ ፕሮፌሽናል የፎቶግራፍ ባለሙያዎች የተሳተፉበት “አዲስ ፎቶ ፌስት” የተሰኘው አውደ-ርዕይ ለአንድ ስምንት ሲታይ ቆይቶ ባሳለፍነው እሁድ ተጠናቀቀ::

የፎቶ የአውደ-ርዕይው አዘጋጅ ደስታ ፎቶ አፍሪካ ክርኤቲብ ኮንሰልቲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ሲሆን፤ በፕሮግራሙ መክፈቻ ዕለትም በክብር እንግድነት የኢፌድሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስተሩ ዶ/ር ቴዎድሮስ አድሃኖምን ጨምሮ በአዲስ አበባ የዩኔስኮ ዳይሬክተር ፍሪማን ኤድዋርድ ተገኝተዋል::

የፎቶ አውደ-ርዕይው መስራችና ዳይሬክተር የሆነችው አይዳ ሙሉነህ “ፎቶግራፎች የዓለም ገፅታን የሚያንፀባርቁ ሐብቶች ናቸው” ከማለቷም በተጨማሪ የዝግጅቱን አላማና አስፈላጊነት ለታዳሚው አስረድታለች::

ዘንድሮ ለ3ኛ ጊዜ የተካሄደው ይህ የፎቶ አውደ-ርዕይ በቀጣይም በየዓመቱ የሚጠበቅ ሆኗል ሲሉ ታዳሚያኑ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል::■

# የገሞራው በሀገሩ...

ባይ ናቸው፡፡ ግን ይህ አቋማቸው ትክክል ነው ወይ? ብሎ መጠየቅም ተገቢ ነው፡፡

ኢትዮጵያዊው ባለቅኔ ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድህን አሁን በስልጣን ላይ ካለው መንግሥት ጋር የማይስማማ ነበር፡፡ አያሌ የተቃውሞ ግጥሞችን ፅፏል፡፡ ግን ኒውዮርክ ከተማ ውስጥ ሕይወቱ ስታልፍ አስክሬኑ ወደ ሐገሩ ኢትዮጵያ መጥቶ ነው የተቀበረው፡፡ ፀጋዬ ከመንግሥት በተፃራሪ ስለቆመ ቀብሩም በውጭ ሀገር ይፈፀም ማለት ይቻላል ወይ?

በዘመነ ደርግ ሰዓሊውና ገጣሚው ገብረክርስቶስ ደስታ ከሀገሩ ተሰዶ ወጣ፡፡ በኬንያ አድርጎ፣ ወደ ጀርመን ተጉዞ እዚያም የተወሰነ ጊዜ ቆይቶ፣ በኋላ ወደ ሰሜን አሜሪካ ተጓዘ፡፡ አሜሪካ ኦክላሆማ ውስጥ በ1974 ዓ.ም ህይወቱ አለፈች፡፡ በነበረው የፖለቲካ አቋም በሚል እዚያው ኦክላሆማ ውስጥ ተቀበረ፡፡ እስከ ዛሬ ድረስ የዚህ ሰው አፅም ወደ ሀገሩ የሚያመጣው ወዳጅም ሆነ ጓደኛ ብሎም ቤተሰብ የለም፡፡ ከሀገሩ እንደወጣ የቀረ ታላቅ የኪነ-ጥበብ ፈርጥ ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ የነበሩ ሰዎች ከፊታቸው የነበረውን ስሜት ተከትለው ገብረክርስቶስን ኦክላሆማ እንዲቀበር አደረጉት፡፡ ዘመን አለፈ፡፡ ገብረክርስቶስም እንደወጣ ቀረ፡፡

እኔ በበኩሌ የገሞራው አስክሬን ወደ ሀገሩ ኢትዮጵያ መጥቶ መቀበሩ ትልቅ ደስታ ሰጥቶኛል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ይህ ሰው እንደ ገብረክርስቶስ ደስታ ሆኖ እንዲያልፍ አልፈልግም፡፡ የገሞራው አስክሬን ለሀገሩ አፈር እንዲበቃ ያደረጉት አካላትም መወቀስ የለባቸውም፡፡ አንዳንድ ፀሐፊያን እነዚህን አካላት ሲወቅሷቸው ስላነበብኩ ነው፡፡ የሰዎቹ ጥፋትም አልገባኝም፡፡ መልካም ተግባር ፈፅመዋልና ነው፡፡

ከመፅሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ሁሉ በጣም ደስ የሚለኝ 'ይህም ያልፋል. . .' እያለ የሚፅፋቸው ነገሮች ናቸው፡፡ በምድር ላይ የማያልፍ የለም፡፡ ፖለቲካውም፣ አስተሳሰባችንም፣ ጦርነቱም፣ ችግሩም፣ ስርዓቶችም ሁሉም ነገሮች ያልፋሉ፡፡ ግን ይህች የተወለድንባት፣ እትብታችን የተቀበረባት ሐገራችን የምንላት ኢትዮጵያ ድሮም ነበረች ገናም ትኖራለች፡፡ ስለዚህ የገሞራው አስከሬን በኢትዮጵያ ማረፉ በዘላለማዊቷ ሀገሩ ውስጥ እንጂ ነገ በምትፈራርሰው፣ በምትጠፋው ምድር አይደለም፡፡ ገሞራው ያረፈው ከወላጆቹ፣ ከዘመዶቹ ጎን ነው፡፡ ይህ እንዴትስ ሊያበሳጨን፣ ይችላል? እስኪ ሰከን ብለን እናስበው!

# በረከተ መርገም...

ሁሉ የዚህ ግጥም ተፃራሪዎች ናቸው፡፡

መከራውን አይቶ ከዚህች ዓለም በሞት የተለየው ኃይሉ ገ/ዮሐንስ /ገሞራው/ ከዛሬ 12 ዓመታት በፊት ለኢትዮጵ መፅሔት ቃለመጠይቅ ሰጥቶ ነበር፡፡ በዚህ ቃሉ እንዲህ ብሎም ነበር፡-

"ከሀገሬ ከወጣሁ ጀምሮ ለሩብ ምዕተ-ዓመታት እዚህና እዚያ ስንከራተት የኖኩትን ፀሊም ሕይወት በማስመልከት የፃፍኳት "ሞቼም እኖራለሁ" የምትል ትንግርተኛ ግጥም አለችኝ፡፡ ግጥሚቱን የፃፍኳት እዚህ ያለሁበት ሀገር ውስጥ፣ ሀገሬንና ወገኔን ለመታደግ የምፅፋቸውን ምግታራዊያን ፅሁፎች መነሻ በማድረግ፣ ባልፈፀምኩት አንዳች ወንጀል፣ ከታላቁ የፍትህ አደባባይ ላይ የፊጢኝ አስረው አቅርበው 'እብድ ነህ' የሚል መንግሥታዊ ውሳኔ በተሰጠበት ማግስት ነው፡፡ እነሱ በሀገሬ የውስጥ ጉዳይ ባይገቡ ኖሮ ባልተቸነፉ ነበር፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ሕይወቴ ቀልቤን እንዳጣ ይገኛል፡፡ ሁኔታዎችን ከኔ አንፃር ሳያቸው 'ደግ አድርገዋል ይበለኝ!' የምልበት ጊዜ አለ፡፡ ወትሮስ ቢሆን እንደኔ ያለ ሰው የመጣው ቢመጣ ከሀገሩ መውጣት አልነበረበትም፡፡ ይሔ ኋላ መጥ አስተያየቴ፣ ፍዳዬን እና መከራዬን በጥሞና ሳስታውሰው ነው፡፡ ግን እኮ ከገዛ ሀገሬም ውስጥ የነበረኝ እድል ስስ ነበርኮ፡፡ እስቲ አንዱን ለምሣሌ ይሆነኝ ዘንድ ልጥቀስ፡፡

"እኔን በቅርብ የሚያውቁኝ ወገኖች ሁሉ እንደሚያስታውሱት በንጉስ ነገስት የዘውድ ግዛት ዘመን፣ ነፍሴ ለጥቂት ዳነች እንጂ (በሆነ ልዩ ተአምር) እንደተንፈራጋጭ እምቦሳ ጥጃ በየወሩ ስታሰር እንደእንቦሳም ስቀጠቀጥ ነበር ለምለሙን የወጣትነት ዘመን ያሳለፍኩት፡፡ ከምፅፈው የግል ታሪካዊ ሁኔታ ውስጥ፣ አንድ ታሪከኛ ትንግርት ይኸውላችሁ፡፡

". . . አንድ ሳምንት ያህል ፔኪንግ እንደቆየሁ፣ ትቼው ከሔድኩት ሀገር አንድ ትንግርተኛ ደብዳቤ ለመጀመሪያ ጊዜ ደረሰኝ ". . . እግዜር በክንፈ ምህረቱ ከልሎ እንደሚጠብቅህም፣ ዘንድሮ በገቢር አረጋገጥኩ፤ ይኸውም . . ." በሚል መነሻ ርዕስ አለው፡፡ ይህንን ያስባለው ምን ነገር ቢገኝ ነው ብዬ ደብዳቤውን በጥሞና ማንበብ ጀመርኩ፡፡ እንዲህ ይላል፡- " አንተ ሀገሩን ለቀህ በሔድክ ማግስት፣ ሁለት ባለቋሚ ተጠሪ ጂፖችና ቁጥራቸው ከአስር በላይ የሆኑ ክላሺንኮቭ ያነገቡ ታጣቂ ወታደሮች፣ ከሌሊቱ 11 ሰዓት ላይ ከቤታችን መጥተው በመውረር 'ኃይሉን ለመውሰድ ከባለሥልጣን ታዘን ነው የመጣነው፣ እዚህ ከሌለ ያለበትን ንገሩን፣ ኃይሉን ካልወለዳችሁ. . .' እያሉ፣ ቀኑን ሙሉ ከግቢያችን የገባ እንዳይወጣ፣ የወጣውም እንዳይገባ አግረው፣ አግረው፣ ሲያስቸግሩን ውለው፣ ማምሻው ላይ ተመለሱ" የሚል የትንቅንቅ ሪፖርታዥ ነው. . .

". . . በዚያን ዕለት አረጋዊ አባቴን እየጨቀጨቁ 'ልጅዎን ይውለዱ' ቢሏቸው 'ትናንት ሔዶ፤ በምድርና በየብስ ሳይሆን፣ በሰማይ ላይ ደመና ሰነጣጥቆ፣ እንደ ቅዱሳኖች እንደነ እዝራና እንደነ ኤልያስ!. . . እናንተው አይደላችሁም እንዴ የፈቀዳችሁለት? እዚህ ያለነው እኛ ነን፤ እኛን እንደብጤታችሁ ማድረግ ትችላላችሁ፤ ሌላም መሔጃ የለንም፤ እሱ ግን ሲሰቃይ ኖሮ ዘንድሮ አዶናይ ረድቶት እጁን አውጥቷል፤ አዶኒስ ይቀደስ!. . ." እያሉ ሲያበግኗቸው ዋሉ አሉ ወታደሮቹን፡፡ ድርጊታዊ ትንግርቱ አንድ ቀን ሙሉ ሲያስቀኝ ዋለ፡፡ አዎ እያንዳንዱ ሰው በዕለተ ልደቱ ቁጥር መጠን፣ ትንንሽ ሞት አሉበት ይባላል፡፡ እኔም በ16ቱ የልደት ቀኔ መጠን፣ የዚያን ቀኑ ትንሽ ሞቴ 7ኛው መሆኑን አስባለሁ፡፡ እዚያ ቻይና እያለሁም በምድር መንቀጥቀጥ ምክንያት ከምኖርበት 4ኛ ፎቅ ስዘል፣ 8ኛ ሞቴ መሆኑን ተረድቻለሁ፡፡ እዚሁ ስዊዲን ደግሞ፣ ያለ ወንጀሌ ከፍተኛ ፍርድ ቤታችው አቅርበው "እብድ ነው" ብለው ሲፈርዱብኝ 9ኛው ትንሹ ሞቴን መሆኑን ቆጥሬያለሁ፡፡ የሚቀሩኝን ትንንሽ ሞቴን እናንተው ልታሰሏቸው ትችላላችሁ፡፡

የባለቅኔው የኃይሉ ገ/ዮሐንስ ሕይወትና ሥራ አስደናቂ ነው፡፡ አሳዛኝም ነው፡፡ 40 ዓመታት በስደት ርቆን ቆይቶ ሞቱ ደግሞ ከፋብን፡፡

# ስለ ታቦተ-ጽዮን ያለው...

Christianity).››

ከዚሁ የአይሁዳውያኑ ሃይማኖት በአክሱማውያን ዘንድ የነበረውን ጉልህ ስፍራና ያሳደረውን የባህል ውርርስና ተጽእኖ ከሚያብራሩ ታሪክ መረጃዎች ባሻገርም የክብረ ነገሥት መጽሐፍ ሰፊ ቦታ ሰጥቶ ስለሚተርክለት ስለ ታቦተ ጽዮን ጉዳይ የሴማውያን ቋንቋ ምሁርና ተመራማሪ የሆነው ዶ/ር ቲዮዶር ኖልዲክ ‹‹ታቦት›› የሚለው ቃል ከዚህ በፊት በአክሱማውያን ዘንድ ያልነበረ መሆኑንና ምናልባትም በንጉሥ ሰለሞን ዘመነ መንግሥት ወደ አክሱም ግዛት ሳይገባ እንዳልቀረ እንደሚያምን አትቶ ጽፏል።

በተመሳሳይም ዶ/ር ሻያም ራቢን የተባለ አይሁዳዊ የቋንቋ ሊቅና የታሪክ ተመራማሪም ‹‹ታቦት›› የሚለው ቃል ጥንታዊ ቃል መሆኑንና ምናልባትም አክሱማውያን ከመካከለኛው ምሥራቅ ጋር በነበራቸው ግንኙነት ከአረቢያ ምድር ከመዲና ግዛት ከነበሩ የአይሁዳውያን ማኅበረሰብ ፍልሰት ጋር ተያይዞ ወደ አክሱም ግዛት ገብቶ ሊሆን እንደሚችል ግምቱን አስቀምጧል።

እነዚህ ታሪካዊ መረጃዎችና የምርምር ሥራዎች የሚነግሩን አንድ ሐቅ ቢኖር የኢትዮጵያ ቤ/ን ታቦተ ጽዮን አስመልክታ የምታቀርበው ታሪክም ሆነ ትውፊት ጥልቅ የሆነ ሃይማኖታዊ፣ ታሪካዊና ባህላዊ መሠረት እንዳላቸው የሚያስረግጡ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ በሌላ አንጻር ደግሞ የሚያሳፍረው ለዚህ ጽሑፌ መረጃ ለማሰባሰብ በሞከርኩ ጊዜ ታቦተ ጽዮንን በተመለከተ በአገራችንም ሆነ በቤተ ክርስቲያናችን ምሁራን ዘንድ የተሠራ በቂ የሆነ የጥናት ሰነድ ማግኘት አልቻልኩም፡፡ ታቦተ ጽዮንን በተመለከተ እኛ ባለቤቶቹ ኢትዮጵያውያን ከእምነት ባሻገር በእውቀት ላይ የተደገፈ መረጃ ለሚፈልጉ ኹሉ እውነታውን ለማስረዳት ሰፊ የሆነ ጥናት ማድረግና በቂ የሆነ ዝግጁነት ሊኖረን የሚገባን ይመስለኛል፡፡

ታቦተ ጽዮንን አስመልክቶ ያሉትንና የተጻፉትን ታሪካዊ መረጃዎችና ሰነዶች ኹሉ ማንሳት አዳጋች ቢሆንም ይህን ጽሑፌን ከማጠቃለሌ በፊት ግን አንድ ኹለት የታሪክ ሰነዶችንና ምስክርነቶችንለማንሳት እወዳለሁ፡፡ የመጀመሪያው ለቤተ መንግሥት የሚሆኑ አልባሳትንና የወግ ዕቃዎችን ይሸጡ የነበሩና በ፲፰ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያን የጎበኙት ዮሐንስ ቶቭማካን የተባሉ አርመናዊ ነጋዴ በ፲፯፻፷፬ ዓ.ም. ገደማ ወደ አክሱም ተጉዘው በዚያም ጽላተ ሙሴን ማየት እንደቻሉ በማስታወሻቸው አስፍረዋል።

ሌላኛው አርመናዊ ጎብኚ ደግሞ አባ ዲሞቴዎስ ሻርታቤት የሚባሉ ሲሆኑ ወደ ኢትዮጵያ የመጡት በዐፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት ነበር፡፡ እኚህ የሃይማኖት አባት ከኢየሩሳሌም ፓትርያርክና ልዑካን ጋርበመቅደላ ተግዘው የነበሩትን የእንግሊዝ ዲፕሎማቶችንና ሚሽነሪዎችን ለማስለቀቅ ሚቻልበትን መንገድ ለማፈላለግ ለድርድር የመጡ አባት ነበሩ፡፡ እኚህ አባት በ፲፰፻፷፩ ዓ.ም. በጽዮን ማርያም ቤ/ን የሚገኘውን በሳዩ ዐሥርቱ ትእዛዛት የተጻፈበትን ጽላት ለማየት ተፈቅዶላቸው እንደነበር ጽፈዋል።

**ምክንያቱም አይሁዳውያን የጥንቱን የቃል ኪዳን ታቦት የሚሸከሙት አራት ሌዋውያን ካህናት መሆናቸውን የኦሪት/ የሙሴመጽሐፍ ይነግረናል**

እነዚህ የውጭ አገር ሰዎችና ተጓዦች ታቦተ ጽዮንን በትክክል ስለማየታቸው ግን አንዳንችም ማረጋገጫ መስጠት አይቻልም፡፡ ምክንያቱ ደግሞ አንደኛው ታቦተ ጽዮንን በተመለከተ በኢትዮጵያ ቤ/ን ዘንድ ያለው ክብርና ሥርዓት እንኳን ለውጭ አገር ሰዎች ቀርቶ ለራስዋ ለቤተ ክርስቲያኒቱ አባቶች እንኳን ጥብቅና ምስጢራዊ መሆኑ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህ የውጭ አገር ሰዎች በሄዱባቸው ገዳማትና አድባራት ያዩትን ታቦታት ሁሉ ልክ ታቦተ ጽዮንን እንዳዩ አድርገው ስለሚጽፉ ነው። እዚህ ላይ ማለት የምንችለው አንድ ነገር ቢኖር ከዛሬ ሁለትና ሦስት ዓመታት በፊት እንኳን የታቦተ ጽዮን ጉዳይ የብዙዎች ተጓዦችና የክርስትናው ዓለም ናፍቆትና መነጋገሪያ ጉዳይ እንደነበር ነው።

በመጨረሻም በተለምዶ ‹‹የግራኝ አህመድ ወረራ›› በሚባለው የጦርነት ወቅት ወደ ኢትዮጵያ ምድር የመጣው ፖርቱጋላዊው ሚሽነሪ ቄስ አልቫሬዝ ከ፭፻ ዓመታት በፊት የኢትዮጵያ ጉዞውን አስመልክቶ በተወው የጉዞ ማስታወሻው ላይ፣ የኢትዮጵያ ቤ/ን እጅጉን የአይሁዳውያን ሃይማኖት፣ ትውፊትና ባህል ተጽእኖ የገነነባት መሆኑኗን በመገረምና በመደነቅ በሰፊው አትቶ ጽፏል፡፡

ቄስ አልቫሬዝና ሌሎች የሮማ ካቶሊክ ቤ/ን ሚሽነሪዎች ከዚህ የተነሣም የኢትዮጵያ ቤ/ን በብሉይ ዘመን ቆማ ያለች ወደ ሐዲስ ኪዳን ዘመን ያልተሻገረች ቤ/ን ናት በሚል በጀመሩት የኢትዮጵያን ቤ/ን ወደ ሮማ ካቶሊክ የመለወጥ ያልተሳካ ሂደት/ዘመቻ የሃይማኖት እንቅስቃሴ የተነሣም በሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ማለቃቸውን የታሪክ ድርሳናት ይመሰክራሉ። የዚህ የሃይማኖት ክርክር ጉዳይና የሮማ እኩይ ዓላማ አገሪቱን ወደባሰ ጥፋትና እልቂት እንዳያመራት ያሰቡት ዐፄ ገላውዴዎስ ባወጡት የሃይማኖት መግለጫ፣ ኢትዮጵያ ቤ/ን አይሁዳዊት ሳትሆን ብሉይን ከሐዲስ አስማምታ አምላኳን የምታመልክ ጥንታዊትና ሐዋርያዊት የአዲስ ኪዳን ቤ/ን መሆኗን በግልጽ አስታውቀዋል።

ሌላው ቄስ አልቫሬዝ በዚሁ የጉዞው ማስታወሻው ላይ የታቦት ሥርዓትን በተመለከተ ያየውን ምስክርነቱን እንዲህ ዘግቦታል፡፡ ይኸውም በአንድ የቤ/ቱ ታላቅ በዓል ላይ ካህናቱ ታቦቱን ለዐራት ተሸክመው በቤተ ክርስትያን ዓውደ ምሕረት ላይ ዑደት ሲያደርጉ ማየቱ ነው፡፡ ይህ የአልቫሬዝ ገለጻ ምናልባት በበዓሉ ወቅት ዑደት ሲያደርግ ያየው በአክሱም የሚገኘውን ታቦተ ጽዮንን ሊሆን ይችላል፡፡

ምክንያቱም አይሁዳውያን የጥንቱን የቃል ኪዳን ታቦት የሚሸከሙት አራት ሌዋውያን ካህናት መሆናቸውን የኦሪት/የሙሴመጽሐፍ ይነግረናል፡፡ አሊያም ደግሞ በጥንት ዘመን በአገራችን የሚቀረጸው ታቦት የአይሁዳውያኑን ጥንታዊየታቦት አሠራርን አሊያም ታቦተ ጽዮንን መሠረት አድርጎ ይሠራ እንደነበር መረጃ ፍንጭ የሚሰጥ ይመስለኛል፡፡ በእርግጥ እዚህ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ በቤተ ክርስቲያኒቱ ሊቃውንትና በታሪክ ምሁራኑ ዘንድ ሰፋ ያለ ምርምርና ጥናት ሊደረግ የሚገባ ይመስለኛል፡፡

ይህም ብቻ ሳይሆን ታቦተ ጽዮን በተመለከተ ዓለም የተፈቀደለትንና ማወቅ ሚገባውን ኹሉ እንዲያውቅና ተገቢውን መረጃ እንዲያገኝ የጉዳዩ ባለቤቶች የሆንን እኛ፣ የቤተ ክርስትያናችን የሃይማኖት አባቶች፣ የታሪክ ተመራማሪዎችና ቅርስ ባለ ሙያዎችና ምሁራን በሰፊው ሊጽፉ ሊናገሩ ይገባል፡፡

ቸር ሳምንት!

# በኬኒያ ባንኮች የሳይበር ጥቃት...

ሰብሮ ለመግባት የሚያስችላቸውን ቴክኖሎጂ በመዘርጋት ላይ ነበሩ፡፡ የቴሌኮም ሰብሮ የመግባቱ የመጨረሻ ግብ የነበረው የበንኮችን የመረጃ ስርአት አዛብቶ የኬኒያ ባንኮች ለውጪ ባንኮች ክፍያ እንዲፈፅሙ በማድረግ ቀጣይነትያለው ህገወጥ የገንዘብ ዝውውር እንዲኖር ማድረግ ነበር፡፡

የኬኒያ ፖሊስም ሆነ የሀገሪቱ ደህንነት በጉዳዩ ዙሪያ ምንም አይነት መረጃ ያልነበረው ሲሆን ግለሰቦቹ ለመያዝ የቻሉት በስራ ላይ ከነበሩት ኮምፒዩተሮች መካከል በአንደኛው የተነሳው እሳት ወደ ቤቱ ከተዛመተ በኋላ ፖሊስና እሳት አደጋ በቦተው ደርሰው አደጋውን የመከላከል ስራን ሰርተው ማጠናቀቃቸውን ተከትሎ በቤቱ የተተከሉት ልዩ ልዩ መሳሪያዎች ጉዳይ ጠረጣሬን ማሳደራቸው በተፈጠረው አደጋ አንድ ሰው መሞቱ ታውቋል፡፡ ጥርጣሬውን ተከትሎ ፖሊስ ባደረገው ምርመራም ቻይናውያኑ በኬኒያ ባንኮች ላይ የሳይበር ጥቃትን በማካሄድ በህገወጥ መንገድ የባንክ የገንዘብ ዝውውርን ለማካሄድ የሚያስችሉ ሶፍትዌሮችና የተለያዩ ውስብስብ የቴሌኮም መሳሪያዎች ተገኝተዋል፡፡ ጥቃቱም በዋነኝነት ኤቲኤም ማሽኖችን፣ የውጪ የገንዘብ ዝውውር ስርአቶችን እንደዚሁም ኤም-ፔሳ የተባለውን የኬኒያ ብሄራዊ የሞበይል ስልክ የገንዘብ ዝውውር ኢላማ ያደረገ እንደነበር የኬኒያ ፖሊስን የመርመራ መረጃ መሰረት አድረጎ ደይሊ ኔሽን ሰሞኑን ባሰራጨው ዘገባ ገልፃዋል፡፡ ፖሊስ ምርመረውን አጠናቆ ግለሰቦችን ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ በጉዳዩ ግራ የተጋበው የኬኒያ መንግስት በውጪ ጉዳይ ሚኒስተሩ አማካኝነት በኬኒያ የቻይናውን አምባሳደር በመጥራት የቴሌኮም መሳሪያዎቹ በምን መልኩ ወደኬኒያ መግባት እንደቻሉ ማብራሪያ ጠይቀዋል፡፡ በአምባሳደሩ በኩል የተሰጠው ማብራሪያ ወይም ምላሽ በጋዜጣው ዘገባ አልተካተተም፡፡

# በምርጫ ለማሸነፍ...

ወደር የሌለውን ሥልጣኑን ይረከባል።

ከዚህ በላይ እንደቀረበው በመጀመሪያው ምዕተ ዓለም የነበረውን የሮማን የምርጫ ሥርዓት ማወቅና ለማርከስ ቺቺሮ የተጻፈውን ደብዳቤ በማነበብ ማድነቅ ይቻላል። ከሁሉ ደግሞ የሚበልጠው አንባቢ የኩንተስ ምክር ምንኛ ምርጫን በማሸነፍ የፖለቲካ ሥልጣንን መረከብ እንደሚቻል የሚማርበትና ኩንተስ የነፃ አስተሳሰብ አራማጅ እንደነበር ያሳያል።

የኮንተስ ደብዳቤ በዋጋ የማይተመን ምክርን ለዘመነኞቹ የምርጫ ዕጩዎች የሚያቀርብ ሲሆን ቀጥሎ ምርጥ ሀሳቦቹ ቀርበዋል፡-

ለውድ ወንድሜ ማርከስ፣

አንድ ሰው ሊኖረው የሚገባውን በተፈጥሮ ችሎታ፣ በልምድና በጠንካራ ሥራ የሚገኘውን ክህሎት እንዳለህ ቢታወቅም ስለመጪው ምርጫህ ቀንና ሌሊት እያሰብኩበት ስለሆነ በዚህ ረገድ ሀሳቤን ላካፍልህ እወዳለሁ።

በእጅህ የያዝከውን ብዙ በጐ ነገሮችህን ተጠቀምበት .... የያዝካቸው ህዝባዊ ግንኙነቶች ሁሉ በአንተ ወገን ናቸው። በተጨማሪ የነጋዴው ማህበረሰብም እንዲሁ። የኢጣልያ ከተሞችም ይደግፉሃል። ከዚህ ቀደም በፍርድ ቤት የቆምክላቸውን ሰዎች አትርሳ፣ እነዚህ ከተለያዩ ማህበራዊ መሠረት የመጡ ደንበኞችህ ናቸው። ከሁሉም ደግሞ አንተን የሚደግፉትን ከልዩ ማህበራዊ ቡድን የመጡትን አስታውሳቸው። በመጨረሻም የሚያደንቁህን፣ ካንተ ለመማር የሚፈልጉትን ወጣቶች በሚገባ ተጠቀምባቸው። በተጨማሪም በየቀኑ ካንተ ወገን የሆኑ የሚታመኑ ጓደኞችህን ሁሉ ልትገለገልባቸው ያስፈልጋል።

የእነዚህን ቡድኖች መልካም ነገር ለማግኘት ጠቃሚ ምክር ለግሳቸው፣ በምላሹም የእነሱን ምክር ጠይቅ። ጊዜው ማግኘት ያለብህን ጥቅም የምታሰባስብበት ወቅት ነው። ሁሉም እዳቸውን የሚከፍሉህ ወቅቱ አሁን መሆኑን አስታውሳቸው፣ በተመሳሳይም የእነሱ ወቅታዊ እርዳታ አንተን ባለ እዳ እንደሚያደርግህ እንዲያውቁ አድርግ። እንደ አንድ ባዕድ ሰው የመኳንንቱ ድጋፍ በተለይም ከዚህ ቀደም በምክር ቤት ያገለገሉት ድጋፍ ያስፈልግሃል። ለእነሱም አንተ ጠቃሚያቸው እንደሆንክ እንዲያውቁት ያስፈልጋል።

ከእነዚህ መኳንንቶች ጋር ግንኙነትህን በሚገባ መኰትኰት ይኖርብሃል። አንተም ሆንክ ጓደኞችህ አንተ ሁሌም ልማዳዊነትን የምትከተል እንደነበርክ የማሳመን ሥራ ልትሠራ ይገባል። ስለ ተራ ሕዝባዊነት ለአፍታ እንኳ እንዲያስቡ አታድርግ። ከተራው ሕዝብ ጋር የተቀራረበ የሚያስመስልህ እንኳን ከሆነ ይህን ያደረከው የፓምፔይን (ዕውቅ ጀኔራል ነው) ድጋፍ ለማግኘት መሆኑን ንገራቸው። ፓምፔይም ተጽእኖውን ሁሉ ላንተ ሲል ይጠቀማል ወይም ቢያንስ ካንተ በተቃራኒ አይቆምም።

እንደ ባይተዋርነትህ ሌላው የሚጠቅምህ ነገር ካንተ ጋር የሚፎካከሩት መኳንንት ብቃት ጉዳይ ነው .... እነ አንቶኒዩስና ካቲላይን የመሳሰሉ ዕጩዎችስ ጉዳይ? አደገኛ ተቀናቃኞች ናቸውን? በትክክል ናቸው፤ እንዳንተ ላሉ ዕጩዎች ግን አይደሉም ....

እንዲያውም እንደ ሁለቱ ካሉ ሰዎች ጋር በመፎካከርህ ዕድለኛ ነህ። ከልጅነታቸው ጀምሮ በጨካኝነታቸው የሚታወቁ ናቸው፤ አሁን ደግሞ ሴሰኞችና አባካኞች። አንቶኒዩስ ከምክር ቤት እንዴት እንደተባረረ ታስታውሳለህ? ያኔ ለምክር ቤቱ የፍትህ ጉዳይ ሲወዳደር ሳባዲዩስንና ፖንቴራን ብቻ ነበር ከጐኑ ሊያቆም የቻለው። ከተመረጠ በኂላ ወደ ገበያ ሄዶ ራሱን ዝቅ አድርጓል፣ በይፋ አንዲት ወጣት ሴት ልጅን ለወሲባዊ ባርነትም ገዝቷል።

ካቲላይን ከደሃ ቤተሰብ የተወለደና ከእህቱ ጋር በፈንጠዚያ ያሳለፈ፣ከአምባገነኑ ሱላ ጋር በማበር የሮማን ዜጐችና ነጋዴዎችን በመግደል እጁ በደም የተጨማለቀ ነው። ሌላው ቀርቶ ካኤሲሊያስን የገደለ ነው። በሮማ ህዝብ ዘንድ ታዋቂ የነበረውን ማሪዮስንም ገድሏል። ካቲላይን የተዋናዮችና የግላዲያተሮች ጓደኛ ነው - ትገምታለህ? ጋጠ-ወጥ ከመሆኑ የተነሳ ወጣት ወንዶችን በወላጆቻቸው ፊት ለወሲብ ሲያቆሻብል ነበር። አፍሪካ ውስጥ ምን እንዳደረገ ላስታውስህ? በደንብ ቁጭ ብለህ ጊዜ ሰጥተህ ልትመዝነው የሚገባ ማስረጃ ያኔ በተከሰሰ ጊዜ ቀርቦበታል።መርምር።

ውድ ወንድሜ!

- ተስፋ አትቁረጥ

የምርጫ ዘመቻህን እንዴት ማካሄድ እንዳለብህ ካንተ ጋር ለመነጋገር እፈልጋለሁ .... በግልጽ ለመናገር ያህል በሮም ከፍተኛውን የመንግሥት ኃላፊነት ለመያዝ እንደተዘጋጀ ሰው እጅግ ብዙ ጠላቶች ስላለህ ምንም ዓይነት ስህተት መፈፀም የለብህም።

ለመንግሥት ኃላፊነት መወደደር በሁለት ተግባራት ይከፈላል፣ ይኸውም የጓደኞችህን ድጋፍ በአስተማማኝ ሁኔታ ማግኘትና አጠቃላይ የምላተ ህዝቡን ድጋፍ ማግኘት። የጓደኞችህን መልካም ድጋፍ በበጐ ምግባር፣ በጥቅማ ጥቅም፣ በቆየ ግንኙነት፣ ሁሌም በመቀራረብና በተፈጥሮአዊ ስበትህ ማግኘት ይቻልሃል። በምርጫ ጊዜ ግን ጓደኝነትን ከዕለት ተዕለት ኑሮ አንፃር ሳይሆን ከዚያ ባለፈ ሰፊ ሁኔታ ማሰብ ያስፈልግሃል።

ቤተሰቦችህንና ከቅርብ ካንተ ጋር የተቀራኙትን ሰዎች እንደዋዛ አትመልከት። ታማኝነት የሚጀምረው ከቤት ነው። የዕጩን ውድቀት የሚያፋጥኑ አፍራሽ ወሬዎች የሚመነጩት ከቅርብ ሰዎች ነው። ሁሉም ካንተ ጋር መሆናቸውንና ውጤታማ እንደምትሆን እንደሚፈልጉ አረጋግጥ። ይህም ጐሳዎችህን፣ ጐረቤቶችህን፣ ደንበኞችህን፣ የቀድሞ ባሮችህንና አሽከሮችህን ጭምር ያጠቃልላል።

በምርጫ ጊዜ ድምጽ የሚያስገኙ ዋስትናዎች ሦስት ናቸው። እነሱም ጥቅማ ጥቅም፣ ተስፋና ግላዊ ቅርበት። እነዚህን ማበረታቻዎች ለትክክለኛ ሰዎች ለመስጠት መሥራት ይኖርብሃል። ካልወሰኑ ድምጽ ሰጪዎች እንኳ ጥቂት ጥቅማ ጥቅም በመስጠት ድምጻቸውን ልታገኝ ትችላለህ። ገጽ በገጽ እነዚህን ሰዎች አግኝተሃቸው የደገፉህ ከሆነ ነገ እዳ ከፋያቸው እንደሆንክ እንዲያውቁት አድርግ።

በተስፋ ያንበሸበሽካቸው ሁሉ በዘላቂነት እንዲያምኑህ ሁሌም ለእርዳታ እጅህን ለመዘርጋት ዝግጁ እንደሆንክ አስመስክር። ታማኝህ ለመሆናቸው ምስጋናህን ቸራቸው፣ ለአንተ ለሚያደርጉልህ ሁሉ በቅርበት እንደምታውቅ አድናቆትህን ለግሳቸው።

ሦስተኛዎቹ ደጋፊዎችህ በግላዊ ቅርበት መልካምነትን የሚያሳዩህ ናቸው። እነሱ መልካምነትን እንዳሳዩህ ሁሉ አንተም ለእነሱ በሚሆን ሁኔታ ቅርበትህን የሚገልጽ መልእክት አቅርብላቸው። ለምርጫህ በሰሩልህ ቁጥር ከእነሱ ጋር ትስስራችሁ እንደጠበቀ አመላክታቸው። ከላይ ለቀረቡት ሦስቱ ደጋፊ ቡድኖች እንዴት በምርጫው ሊረዱህ እንደሚችሉ ወስን፤ ለእያንዳንዱ ቡድንም ልዩ ትኩረት በመስጠት ከነሱ ምን እንደምትሻ አስታውቅ።

በየመንደሩና በየከተማው ሥልጣናቸውን የሚጠቀሙ ቁልፍ ሰዎች አሉ .... ዕውነተኛ ሥልጣን ከሌላቸው መደዴዎች እነዚህን ቁልፍ ሰዎች ለይተህ እወቅ። በትክክለኛ ሰዎች ተከበብ። የምታምናቸውንና ብሩህ አእምሮ ያላቸውን ሰዎች በአጠገብህ ኮልኩል። በአንድ ድርጅት ውስጥ ጠቃሚና ጠቃሚነት የሌላቸውን ሰዎች አስቀድሞ መለየት ጊዜህንና ጥሪትህን ከማባከን ይታደግሃል።

ውድ ወንድሜ!

እነሱ ለምክር ቤት (ለወንበር) የሚሯሯጡ እስኪመስል ድረስ የሚረዱህን የቅርብ ሰዎች ፈልግ። ጐብኛቸው፣ አነጋግራቸው፣ በትክክል እወቃቸው። በሚገባቸው ቋንቋ ታማኝነታቸውን አጠንክረህ ለማግኘት ሞክር። አንተ ጓደኛቸው መሆን እንደምትፈልግ ሁሉ እነሱም ጓደኞችህ መሆንን ይፈልጋሉ። የአነስተኛ ከተማና የገጠር ሰዎችም ያንተ ጓደኞች መሆን ይፈልጋሉ። በስማቸው እወቃቸው፤ ግን ደግሞ የዋሆች አይምሰሉህ። አንድ ነገር ካንተ የሚያገኙ መሆኑን ሲያውቁት ብቻ ነው የሚደግፉህ። ይህ ከሆነ አንተን ከመርዳት አይቆጠቡም።

ለነጋዴው ማህበረሰብና ለሀብታም ዜጐች ልዩ ትኩረት ስጥ .... በቁጥራቸው ብዙ ስላልሆኑ የነዚህ ቡድኖች መሪዎችን ለይተህ እወቅ። የወጣቶችን የመነሳሳት ስሜትና ትኩስ ጉልበት ለመጠቀም ወጣቶችን ከጐንህ አሰባስብ። ወጣቶች የድምጽ ሰጪዎችን ድጋፍ ያስገኙልሃል፣ ደጋፊ ያሰሩልሃል፣ ወሬ ያሰራጩልሃል፣ በተጨማሪም መልካም እንደሆንክ ሁሉ እነሱም መልካም ያደርጉልሃል።ዝናህን ይነዙልሃል።

- ○ ጓደኞችህን አቅርብ፣ ጠላቶችህን ደግሞ በጣም አቅርብ

በየዕለቱ የተለያዩ ሰዎች እንዲከቡህ ማድረግ ያስፈልጋል። ምን ያህል ሕዝብ በብዛትና በጥራት እንደከበበህ ሲያዩ ድምጽ ሰጪዎች ይመዝኑሃል። ሦስት አይነት ተከታዮች አሉ፤ እነሱም ቤትህ መጥተው ሠላም የሚሉህ፣ ወደ አደባባይ የሚያጅቡህና የትም በሄድክ ቁጥር የሚከተሉህ ናቸው።

የመጀመሪያዎቹ አይነት ሰዎች እጅግም እምነት የሚጣልባቸው አይደሉም፣ ከአንድ ዕጩ በላይ ግንኙነት ያደርጋሉ። ቢሆንም ግን ወደ ቤትህ ስለመጡ መደሰትህን ግለጽላቸው። ባገኘሃቸው ቁጥር አንተን ለመጐብኘት ስለመጡ ምስጋናህን አቅርብላቸው። ምንም እንኳ ብዙ እጩዎችን የሚጐበኙ ቢሆንም ልዩ ትኩረት በማድረግህ ብቻ ወደ ራስህ በመሳብህ ጠንካራ ደጋፊዎች ልታደርጋቸው ትችላለህ። አንዳንዴ ሊሆን እንደሚችለው እንደነዚህ ሰዎች ድጋፋቸው ጠንካራ አለመሆኑን ከሰማህ ወይም ከጠረጠርክ እውነት እንዳልሆነ አድርገህ አስመስል። የቀረበባቸው ስሞታ እውነት አይደለም የሚሉም ከሆነ የእነሱን ታማኝነት ተጠራጥረህ እንደማታውቅ አስረዳ። እንደ ጓደኛ እንደምታምናቸው አበክረህ ግለጽላቸው። ይህን በማድረግህ የመታመን ደረጃቸውን ታሳድጋለህ።

ወደ አደባባይ ለሚያጅቡህ ደግሞ በየዕለቱ ጥዋት ወደ ቤትህ ከሚመጡት የበለጠ ድርጊታቸውን እንደምታደንቅላቸው እንዲያውቁ አድርግ። በየእለቱም በየአደባባዩ በመገኘት አጀቡ እንዲደምቅ አድርግ። ይህ ሁኔታ ብዙ ሰዎችን የሚያስደምም ይሆናል።

**በኩንተስ የተጠቀሱ የምርጫ ደንቦችን በመጠቀም ማርከስ የምክር ቤት ምርጫን አሸነፈ፤ ከማናቸውም ዕጩ ተወዳዳሪ በላይ የድምጽ ብልጫ አገኘ።**

ቀኑን ሙሉ ለሚከተሉህ ደግሞ፣ በፍላጐታቸው ተነሳስተው የሚያደርጉት መሆኑን በመግለጽ ምስጋናህን ቸራቸው።

ስለ ወዳጅነት አስመልክቼ ብዙ የጻፍኩ ቢሆንም አንዳንድ ማስጠንቀቂያዎችን መስጠት ያስፈልገኛል። ፖለቲካ በማታለል፣ በእምነት የለሽነትና በክህደት የተሞላ ነው .... "ሰዎችን በቀላሉ አትመን" የሚለውን የፀሐፌ ተውኔት ኤፒካርመስን ድንቅ ቃላት አስታውስ።

ወዳጆችህ እነማን እንደሆኑ ካወቅህ፣ ለጠላቶችህ ደግሞ የተወሰነ እሳቤን ስጥ። በጠላትነት ሊቆሙ የሚችሉ ሦስት አይነት ሰዎች አሉ፤ እነሱም፡- የበደልካቸው፣ የተጨበጠ ምክንያት ሳይኖራቸው የሚጠሉህና የተቀናቃኞችህ የቅርብ ጓደኞች ናቸው። ለበደልካቸውና ለጓደኛህ ስትል በተቃራኒያቸው የቆምካቸውን ሰዎች ደግ አድራጊና ይቅርታ ጠያቂ ሁን። የቅርብ ወዳጅህን ለመርዳት ስትል በተጻራሪነት እንደቆምክና እነሱም ጓደኛህ ከሆኑ ተመሳሳይ ሁኔታ እንደምትፈጽምላቸው አስታውሳቸው። ካለምክንያታዊነት ለሚጠሉህ ደግሞ፣ ቀና በመሆን አሸንፋቸው። ወይም በጐ ሥራ አድርግላቸው ወይም እንደምትጠነቀቅላቸው በተግባር አሳይ። የተቀናቃኞችህ ጓደኛ ለሆኑት ተመሳሳይ ስልት በመጠቀም ርህሩህነትህን አሳያቸው።

- ማናቸውንም ነገር ቢሆን ቃል-ገባ

ድምጽ ሰጪዎችን ለማስደመም ሌላው ስልት እነማን እንደሆኑ በትክክል ስታውቅ፣ ግላዊ ትውውቅ ስትፈጥር፣ እጀ ሰፊ ስትሆን፣ ራስህን ስታስተዋውቅ፣ ሁሉም ቦታ ስትገኝና እጅ የማትሰጥ ስትሆን ነው። አንድን መራጭ ለማስደመም አንዱ ዘዴ ስታስታውሰው ነውና ስሙንና መልኩን ለመለየት በየቀኑ ተግተህ መስራት አለብህ።

ወንድሜ ሆይ!

ምንም እንኳ ብዙ ብቃቶች ቢኖርህም፣ የሌለህን ደግሞ መያዝ አለብህ። እጅግ በጣም አርኪ ባህርይ አለህ፣ ሁሌም ምግባረ-ቀና ሰው ነህ። ግን ደግሞ የማሞካሸትን ጥበብ መማር ይኖርብሃል። ለመደበኛ ህይወት የማሞካሸት ባህርይን መያዝ አዋራጅ ቢሆንም ለሥልጣን ስትሮጥ ግን ጠቃሚ ነው። ሰውን ሙሰኛ ለማድረግ ካለ ይሉኝታ ማሞካሸትን ከተጠቀምክ ይቅርታ አይደረግልህም፤ ዳሩ ግን ልዩ ፖለቲካዊ ጥቅም ለማግኘት ስትል ግን ካሞካሸህ ተቀባይነት አለው። አንድ ዕጩ ተወዳዳሪ እስስት ሆኖ ከተገናኘው ሰው ጋር መግጠም፣ አተያዩን የሚገለባብጥና ቢቻልም አነጋገሩን በየሂደቱ የሚለዋውጥ መሆን አለበት .....

ሮም ከተማን ለቀህ ዬትም አትሂድ!

..... በምርጫ ወቅት ለአንድ ተወደዳሪ እረፍት የለም። በከተማውና በየአደባባዩ በመገኘት ለመራጮች ዲስኩር አድርግ፣ በሚቀጥለው ቀንም በተከታታይ እንዲሁ አድርግ።

በቀጥታም ቢሆን ብዙ መራጮች ላይ ቀጥተኛ ተጽእኖ ባይኖረውም ለአንድ ዕጩ ተወዳዳሪ እጅ-ሰፊነት አስፈላጊ ነገር ነው። በድግስ ላይ ለጓደኞችህ መልካም እንደሆንክ ሰዎች ሁሉ መስማት ይፈልጋሉ። ስለዚህ ለሁሉም ጐሣ መሪዎች አንተና ወዳጆችህ በግብዣው ላይ በመገኘታችሁ መደሰታችሁን አረጋግጥ። ካንተ ለሚጠብቁ ሁሉ ቀድመህ በመድረስ እጅ-ሰፊነትህን አስመስክር። ቤትህ ለሁሉም ክፍት ይሁን፣ ከሁሉ ደግሞ አቀራረብህንና የፊት ገጽህ ግልጽ እንዲሆን አድርግ፣ ይህ ዜዴ ነው ወደ ሰው ነብስ መሹለኪያ መስኰት።

አንድ ሰው የማይቻል ነገር እንድታደርግለት ሲጠይቅህ፣ ለምሳሌ ያህል ከጓደኛህ በተቃራኒ እንድትቆም ሲፈልግ አጥብቀህ ተቃወም፤ ለጓደኛህ ከፍተኛ ኃላፊነት እንዳለብህ ግለጽለት። በሌላ ነገር ልትክሰው እንደምትፈልግ ንገረው ....

ያ የምርጫ ዘመቻ ጠቢብ ፖለቲከኛው ኮታ (Cotta)፣ "ለማንም ማናቸውንም ነገር ቃል ግባ!" ያለውን አባባል አስታውስ። ቃል የገባኸውን ነገር ሳትፈጽም ከቀረህ ጉዳቱ ቀላል ነው፤ የሚጐዳውም ሰው መጠን አነስተኛ ነው። ዳሩ ግን ቃል ያልገባህ እንደሆን ውጤቱ ከባድ ይሆናል፤ በብዙ ድምጽ ሰጪዎች ዘንድም ንዴትን ያጭራል። ካንተ ርዳታ የሚፈልጉ ሁሉ ይህን መስማት አይሹም። በአደባባይ ላይ ተስፋ ያልሰጠሃቸው አነስተኛ ሰዎች ቢከፉ ይሻላል ከቤትህ ፊት ለፊት የተሰበሰቡ ብዙ ሰዎች ተስፋ ከሚያጡብህ ....

ዋነኛው የምርጫ ዘመቻህ አካል ለሕዝቡ ተስፋ መስጠትና በአንተ መልካም እምነት እንዲኖራቸው ማድረግ ነው። በሌላ በኩል ለምክር ቤቱም ሆነ ለህዝቡ አንተ የምትሰጠው ልዩ ተስፋ የለም። ሁሌም ቢሆን ደብዛዛ የሆነ አጠቃላይ ጉዳይ ላይ አትኩር። ለምክር ቤቱም ቢሆን ነባር ሥልጣኑንና ልዩ ክብሩን እንደምትጠብቅ ተናገር። ነጋዴዎችና ሀብታሞች አንተ ለመረጋጋትና ሰላም መቆምህን ይወቁ። ለተራው ሰው ደግሞ የእነሱ ወገን እንደሆንክ በንግግርህና በፍርድ ቤት ተግባርህ አስተማምነህ ንገራቸው።

የእኛ ከተማ የሰው ልጅ የተበሻቀጠበት፣ የሸፍጠኞችና የሴራ ማደራጃ፣ የሰይጣናዊ ምግባሮች ማከማቻ ሥፍራ ናት። ዞር ባልክ ቁጥር የምትመለከተው መታበይን፣ ልበ-ደንዳናነትን፣ ክፋትን፣ ኩራትንና ጥላቻን ነው። በዚህ ዓይነት ምስቅልቅል ዓለም የመረጥከውን መንገድ የሙጥኝ ብለህ መጓዝ አለብህ። የሮማን ሕዝብ ወደ ራስህ ወገን ለመሳብ አቻ የሌለው የንግግር ችሎታህ ይጠቅምሀል። ተቀናቃኞችህ መደለያ በመጠቀም ደጋፊዎችን ወደ ራሳቸው ሊያዞሩ ይችላሉ። ብዙ ጊዜ ደግሞ ይኸ ይሠራል። ግን ታዲያ ድርጊታቸውን በቅርበት እንድትከታተልና ወደ ፍርድ እንደምታቀርባቸው ሊያውቁት ይገባል። ትኩረትህንና የንግግር ችሎታህን እንዲሁም በነጋዴው ማህበረሰብ ዘንድ ያለህን ተጽእኖ ስለሚያውቁ ግን ሊፈሩህ ይችላሉ። በሙስና ጉዳይ ተቀናቃኞችህን ወደ ክስ ትወስዳለህ ማለት ግን አይደለም፤ ዳሩ ልትገትራቸዉ እንደምትችል ብቻ ይወቁት። ከመደበኛ ክስ በላይ ፍራቻ ይበልጥ ይሠራል። በተጭበረበረ የምርጫ ሂደት ውስጥ እንኳ ቢሆን ብዙ ድምጽ ሰጪዎች ለሚያምኑበት ሰው ድጋፋቸውን ይሰጣሉ።

ወንድሜ ሆይ!

ማለት የምችለው ይህን ብቻ ነው። ካንተ በላይ ስለ ፖለቲካና ምርጫ አውቃለሁ ማለት አይደለም። ዳሩ ግን ባተሌ መሆንህን ስለማውቅ እነዚህን ተራ ህጐች በጽሑፍ ላቅርብ ስል ነው መሞጫጨሬ።

***

ከዚህ በኂላ ምን ሆነ? በኩንተስ የተጠቀሱ የምርጫ ደንቦችን በመጠቀም ማርከስ የምክር ቤት ምርጫን አሸነፈ፤ ከማናቸውም ዕጩ ተወዳዳሪ በላይ የድምጽ ብልጫ አገኘ። አንቶኒዩስ ካቲላይንን በአንስተኛ ልዩነት አሸንፎ የሁለተኛው ምክር ቤት አባል ሆነ። ካቲላይን በሚቀጥለው ዓመት ተወዳድሮም ተሸነፈ። ሪፑብሊኩን በኃይል ለመጣል ሠራዊት አደራጀ። ማርከስ በምክር ቤት አባልነቱ ሴራውን በማጋለጥ ምክር ቤቱ በካቲላይን ላይ ጦርነት እንዲያውጅ አደረገ። ካቲላይን በዚያ ጦርነት ተገደለ። ሁለቱ ወንድማማቾች ማርከስና ኩንተስ ከሁለት አሥርተ ዓመታት በኂላ በተደረገው የርስ በርስ ጦርነት ተገደሉ። የርስ በርሱ ጦርነትም የሪፐብሊኩ ውድቀት ሆኖ የሮማ ኢምፓየር እንዲመሠረት መንገድ ከፈተ።■

# “የክብር ዶክተር” የሚለው ማዕረግ መጠሪያ ይሆናል?

በማዕረጉ በዛብህ

በአገራችን ከጥቂት ዓመታት ወዲህ በመንግሥት ዩኒቨርስቲዎች “ዶክተር” የተባለው የክብር ማዕረግ በልዩ ልዩ ሙያ ከፍተኛ አገልግሎት ላበረከቱ ሰዎች መስጠት ተጀምሯል። ለምስጉን ሰው የሚገባውን ክብር መስጠት ወይም ዋጋ መክፈል ተገቢ ስለሆነ የሚመሰገን ተግባር ነው። የሚያጠያይቅ ነገር ቢኖር ሊያገኙ የሚገባቸው ሁሉ እያገኙ ነው ወይ? ክብሩን የሚሰጠው በሕይወት ላሉ ሰዎች ብቻ ነው ወይስ በሕይወት ለሌሉም ነው? አሁን ካገኙት ሰዎች ቀድመው ሊያገኙ የሚገባቸው የሉም ወይ? ያመራረጡ ስርዓት ምን ያህል ፍትሀዊ ነው? ወዘተ የሚሉት ጥያቄዎች ሊታሰቡ ይችሉ እንደሆነ ነው እንጂ እስከዛሬ ባገኙት ላይ አይገባቸውም የሚል ጥያቄ የሚነሳ አይመስለኝም።

ይህን ጉዳይ በሚመለከት ሊነሳ የሚገባው አንድ ሌላ ጥያቄ ግን በእርግጥ አለ። ጥያቄው የክብር ዶክተር ማዕረግ ልክ በትምህርት ዓለም የሚፈለገውን የትምህርት ምርምርና ጥናት አድርገው ዶ/ር የሚለውን ማዕረግ እንዳገኙት ምሁራን ሊጠሩበት ይችላሉ ወይ? የሚለው ነው። ለዚህ ጥያቄ ትክክለኛውን መልስ ሊሰጥ የሚገባው አንጋፋው የትምህርት ተቋም የሆነው የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ሲሆን እስከዛሬ ምንም ድምጽ አላሰማም። እኔ እስከማውቀው፣ ከምሁራን ግለሰቦችም የተሰጠ ማብራሪያ እስካሁን ያለ አይመስለኝም። ይህም በመሆኑና ሌላም መደባዊ መግለጫ ጉዳይ ከሚመለከታቸው ተቋማት ባለመሰጠቱ ሰዎች አንዳንዶቹ መጠሪያ ሊሆን ይችላል ሲሉ ሌሎቹ ደግሞ አይሆንም በማለት ሲከራከሩ ይሰማል። ክርክሩ ጥሩ ነው። ጉዳዩ ግን የየአገሩ ዩኒቨርስቲዎችን የረጅም ዘመን አሰራርና ልምድን ማየት የሚጠይቅ ነው።

ጋዜጠኞች እንደዚህ ባለ ለአገራችን ባህል አዲስ በሆነ ጉዳይ ላይ መልስ ሊሰጡ የሚችሉ ምሁራንና የትምህርት ተቋሞችን አነጋግረው ትክክለኛውን እውነት ለሕዝብ ሊያሳውቁ ሲገባ (እነርሱም ራሳቸው በውዥንብር ውስጥ በመሆናቸው ይመስላል) ትክክለኛውን ማብራሪያ ሲሰጡ አይሰሙም።

በዚህ ፀሐፊ ግንዛቤ (Honorary) የክብር ዲግሪ መጠሪያ ሆኖ አይታየውም። ይህ የክብር ዲግሪ የሚያገለግለው ክብሩን ያገኘው ሰው ግለታሪክ ሲፅፍ፣ ስለሱ ሌሎች ሲጽፉ ወይም ስለሱ አስተዋጽኦ ሲነገር ወይም ከዚህ ዓለም በማለፉ የሕይወት ታሪኩ ሲነበብ በመጥቀስ እንጂ ከስሙ በፊት በማስቀመጥ፣ ልክ በዩኒቨርስቲ ዶ/ር የሚለውን እጅግ ከፍተኛ የትምህርት ዲግሪ እንዳገኘ ሰው ሊጠራበት የሚችል አይመስለኝም።

እንደ አሜሪካና ብሪታኒያ ባሉ አገሮች ብዙ ሰዎች የዶክትሬት ዲግሪ እያላቸው ዶ/ር የሚለውን አይጠሩበትም። በሶስተኛው ዓለም አገሮች ግን አንዳንድ ሰዎች እንኳንስ ያገኙትን ባላገኙትም ዶክተር ተብለው ለመጠራት ብዙ እንደሚጓጉ ይታያል። አንዱ የዚህ ምክንያት ምናልባት የኛ ሕዝብ ዶክተር ለሚለው ማዕረግ የሚሰጠው የተጋነነ ክብር ይመስለኛል። ሌላው ከዚህ ከክብር ዶ/ር አጠራር ጋር ሲነገር የሚሰማው ስህተት ክቡር ወይም ክብርት የሚለው በመንግሥት ፕሮቶኮል በአስፈፃሚው ቅርንጫፍ ለሚሾሙ ከፍተኛ ባለሥልጣናት የሚሰጥ የማዕረግ መጠሪያ ነው። ክቡር የሚለው አጠራር በፖለቲካ ፕሮቶኮል ውስጥ ያሉ ወይም ያለፉ ባለስልጣናት ስም ላይ የሚጨመር የክብር ወይም የማዕረግ መግለጫ ነው። ለምሳሌ በኢትዮጵያ አንድ ሰው ከአምባሳደርነት ጀምሮ ምክትል ሚኒስትር፣ ሚኒስትር ዴታ፣ ሚኒስትር፣ ም/ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ፕሬዝዳንት ሲሆን የሚጠራበት የፕሮቶኮል ሹመት መግለጫ ማዕረግ ነው። አንድ ሰው ሀብታም ስለሆነ ወይንም ሰውነቱ ግዙፍ ስለሆነ ክቡር ሊባል አይችልም። ክብርትንም በሚመለከት ያው ነው። እነኚሁንም ሆነ ሌሎች የፕሮቶኮል ጉዳዮች ሰዎች ባለማወቅ አሳስተው እንደመጣላቸው በመፃፍ ሕብረተሰቡን ማሳሳት አይገባቸውም። ከመፃፍ መጠየቅ፣ ማጥናት ሊቀድም ይገባል።

*የተከበረ የሚለው ቃል የአንድ ሀገር የፓርላማ (ምክር ቤት) አባላት የሚጠሩበት ማዕረግ ነው። የፓርላማ አባል ያልሆነ ሰው በዚህ ማዕረግ ሊጠራ አይችልም።*

አንድ ጋዜጣ በ2006 ዓ.ም የትምህርት ዓመት መጨረሻ ላይ የክብር ዲግሪ ስለተሰጣት አትሌት ሲዘግብ “ከዛሬ ጀምሮ ክብርት ዶክተር እገሊት” እየተባለች ነው የምትጠራው ሲል በድፍረት ጽፏል። ይህ የግሉ ብያኔ ይመስላል። ስለዚህ ጉዳይ ያጫወትኩት አንድ ወዳጄ “ሰዎቹ ከፈለጉ ቢጠሩበት አንተ ምን ቸገረህ፣ ቅናት ነው?”አለኝ። የኔ አቅዋም የማናውቃቸውን ከውጭ ባህል ጋር የተቆራኙ ስርዓቶችን በደንብ እንድናውቃቸው ጉዳዩን ይበልጥ የሚያውቁ ሰዎችም ሆኑ ተቋሞች ያስተምሩን በዚህም መልክ እውነተኛውን ነገር እንወቅ ነው። ሌላ አይደለም። ቅናትም አይደለም።

ሌላው አልፎ አልፎ በመገናኛ ብዙሃን ሳይቀር በስህተት ሲጠቀስ የሚሰማው የተከበሩ የሚለው ቃል ነው። ይህ የፕሮቶኮል ቃል የአንድ ሀገር የፓርላማ (ምክር ቤት) አባላት የሚጠሩበት ማዕረግ ነው። የፓርላማ አባል ያልሆነ ሰው በዚህ ማዕረግ ሊጠራ አይችልም።

ይህቺ አጭር ጠቋሚ ፅሁፍ የተዘጋጀችው በተነሳው ጉዳይ ላይ ውይይት እንዲደረግ ለማነሳሳት ነው እንጂ፣ እኔ አውቃለሁ ከሚል መመፃደቅ በመነሳት አይደለም፤ ለዚህም ነው ነገሩ የሚመለከታቸውንና ስለጉዳዩ ይበልጥ የሚያውቁትን ምሁራን በመቀስቀስ ትምህርት በሰፊው ይገኛል የሚል እምነት አለኝ የምለው። ስለሆነም በተለይ የመገናኛ ብዙሃን በዚህ ርዕስ ላይ ውይይት እንዲደረግ ቢያመቻቹ ጠቃሚ ይመስለኛል።

## ከመሻሻል ይልቅ እየከፋ...

አቅጣጫ እንዳያመራ የብዙዎች ስጋት ነው። በነገራችን ላይ የሀገራችንን የዜጎች የገቢና የሀብት ልዩነት በተመለከተ መረጃ ለማግኘት ጥረት አድርጌአለሁ። እናም ያገኘሁት መረጃ በኢትዮጵያ በዜጎች መካከል ያለው የገቢና የሀብት ልዩነት አሁን ላይ በሚያሰጋ ሁኔታ ውስጥ አለመሆኑን ያረጋግጣል መረጃው። ያም ሆኖ እየታዩ ያሉ ፍንጮችን ከወዲሁ ማስወገድ የቀደመውን አጠናክሮ መቀጠልና ድህነትን ማስወገድን ማዕከላዊ ያደረጉ ሥራዎች በስፋት ተጠናክረው መካሄድ እንዳለባቸው የሚያስገነዝብ ነው።

### የሀብትና የገቢ ልዩነት እየከፋ የመጣባቸው ምክንያቶች

### በባለሙያዎች ዕይታ

በተለያዩ ጊዜያት የኢኮኖሚ ጽንሰ-ኀሳቦችን (Economics Theory) ይዘው ብቅ በማለት ከሚታወቁት መካከል የቀድሞው አስተሳሰቦችን አሁንም ድረስ ይዘው የዘለቁት /Neoclassical/ ይጠቀሳሉ።

እነዚህ ባለሙያዎች በሀብትና የገቢ ልዩነት እየከፋ መምጣት ዙርያ ምክንያት ካሉት ውስጥ ዋነኛው ከምርታማነት ጋር ይያያዛል። እንደ እነሱ አባባል አንድ የተሻለ ሙያተኛ ከምርታማነት ጋር በተያያዘ የተሻለ ተከፋይ ሲሆን፤ በአንፃሩ በዝቅተኛ የሙያ መረብ ውስጥ የሚገኘው ደግሞ ክፍያው በዚያው ልክ ስለሚሆን የገቢና የሀብት ልዩነቱ ከዚያ ይነሳል የሚል ሃሳብ ያቀርባሉ። የአንጋፋው የማርክሲስት ኢኮኖሚክስ አስተሳሰብ አራማጆች በበኩላቸው ክስተቱን የካፒታሊስት ሥርዓት መገለጫ ሲሉ ይገልፃሉ። ካፒታሊስቶች በነፃ ገበያ ውስጥ ያለውን ውድድር ለማሸነፍ እና ዳጉስ ያለ ትርፍ ለማካበት የማምረቻ ወጪዎችን የመቀነስ ስትራቴጂ ቀርፀው ይተገብራሉ።

በዚህ ሂደትም ሠራተኞች በካፒታል ዕቃዎች /Capital Equipment/ እንዲተኩ በማድረግ ሀብት ያጋብሳሉ። እነሱ በሀብት ላይ ሀብት ሲያካብቱ ሠራተኛው ገቢውና ኑሮው ቁልቁል ይንደረደራል።

ግብር ሌላው የገቢና የሀብት ልዩነት መንስኤ ተብሏል። በተለይ በሀብታም ሀገራት የተተገበረው ሪግሪሲብ ታክስ /Regressive tax/ በድሃ ሀገራት ካለው ፕሮግረሲብ ታክስ /Progressive tax/ በተቃራኒ የሚገኝ በመሆኑ ሌላው መገለጫ ሆኗል። በሀብታም ሀገራት ገቢ ሲጨምር የታክስ መጠን በአማካይ እየቀነሰ ስለሚሄድና በድሃ ሀገራት ደግሞ ገቢ እየጨመረ ሲሄድ በዚያው ልክ የታክስ መጠኑ ከፍ ስለሚል በዚያው ልክ የሀብታሞቹ ሀብታም ሰዎች በተመቻቸላቸው ዕድል በመጠቀም በሀብት ጉዳና ይራመዳሉ።

ዓለምን አንድ መንደር ያደረገው /Globalization/ ከምክንያቶቹ ውስጥ ተጠቅሷል። ሀብታም ሀገራት ከድሃ ሀገራት ጋር በሚያደርጉት የንግድና የኢኮኖሚ ግንኙነት የመጠቀም ሚዛኑ ወደ ሀብታሞቹ ያጋድላል። የዚህ ምክንያትም በድሃ ሀገራት ያለው የሠራተኛ ኃይል ባለው የሥራ መደብ ዝቅተኛ ተከፋይ ሲሆን የሀብታሞቹ ሀገራት ዜጎች ግን በብዙ ዕጥፍ የሚበልጥ ደመወዝተኛ ይሆናሉ። ይህም ብዙ ሀብትና ገቢ ወደ እነሱ እንዲፈስ ያደርጋል። በእነዚህና ሌሎችም ምክንያቶች የዓለም መገለጫ ከፍተኛ እና እየከፋ የሄደ የገቢና የሀብት ልዩነት እንዲሆን ግድ ሆኗል።

### መፍትሄውስ?

ችግሩን ማወቅ የመፍትሄ ግማሽ አካል ነው ይባላል። /Identification of a problem reshelf of the solution/ እናም የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም /UNDP/ በቅርቡ ለችግሩ መፍትሄ ይሆናል ያለውን የጥናት ውጤት ይፋ አድርጓል። ይኸውም በዋናነት በዓለም ዙሪያ በተለይ በድሃና ትዳጊ ሀገራት በከፍተኛ ሁኔታ የሚታየውን የሥራ አጥነት ችግር ለመቅረፍ ይቻል ዘንድ የሥራ ዕድሎችን ከመቼውም በላቀ ደረጃ መፈፀም ከዚህም ጐን ለጐን ለሥራ አጥነት የማጋለጡ ሁኔታዎችን ተከታትሎ ስጋቱን አስቀድሞ ማስወገድ።

ሌላው መፍትሄ የተባለው፤ የዜጐችን መሰረታዊ ፍላጐት ማሟላት የሚያስችሉ የማኅበራዊ ዋስትና ሥራዎች ላይ አተኩሮ መሥራት የሚለው ነው። ሲጠቃለል ፕሬዚዳንት ኦባማ እንዳሉትና የዘርፉ ባለሙያዎችም በተጨባጭ እንዳረጋገጡት በዓለም ዙሪያ የገቢና የሀብት ልዩነት ከመቼውም በበለጠ የከፋ ደረጃ ላይ ደርሷል። ችግሩን ከወዲሁ መቆጣጠር ካልተቻለ ሁኔታው በአጭር ጊዜያት ውስጥ ከቁጥጥር ውጭ መሆኑ አይቀሬ ነውና ሀገራት ለጉዳዩ ከወዲሁ ተጨባጭ መፍትሄ ሊያፈላልጉ ይገባል።■

## ለዓለም አቀፉ ነዳጅ ዋጋ...

ሰዑዲ አረቢያ በኩል ተቀባይነትን ማጣቱ ለዋጋው መወደቅ አንዱ ምክንያት መሆኑን የቢቢሲ ዘገባ ያመለክታል።

በርካታ ነዳጅ አምራች አገራት ዋነኛ የኢኮኖሚ ምንጫቸውን የነዳጅ ገቢን በማድረጋቸው የነዳጅ ዋጋ መውረድ በከፍተኛ ደረጃ የበጀት ጉድለትን እያስከተለባቸው ሲሆን ሳዑዲ አረቢያ ግን ከተወሰኑ ዓመታት ወዲህ በወሰደቻቸው እርምጃዎች አኮኖሚዋን ከነዳጅ ጥገኝነት የማላቀቅ ስራን በመስራት ላይ ናት። ከዓለም አቀፉ የአየር ብክለትና ሙቀት መጨመር ጋር በተያያዘ ነዳጅን በሌሎች አማራጭ የኢነርጂ ምንጮች ለመተካት እየተደረገ ያለው ጥረት ውጤትን እያስመዘገበ መሄዱ ለበርካታ ነዳጅ አምራች አገራት ከፍተኛ ስጋትን እያጫረ ሲሆን በአውሮፓና በአሜሪካ በኤሌክትሪክ ባትሪና በሶላር የሚሰሩ ቀላል ተሽከርካሪዎች ብቅ ብቅ ማለታቸውም ስጋቱን የበለጠ አባብሶታል።

ከዚህም በተጨማሪ ከተወሰኑ ጊዜያት ወዲህም የነዳጅ ምርት ባለቤት እየሆኑ ያሉ ሀገራት ቁጥር እየጨመረ መሄድም ሌላኛው የኦፔክ አባል አገራት የወደፊት የገበያ ስጋት ነው። የኦፔክ አባል አገራት የነዳጅ አቅርቦት መጠን አርባ በመቶውን የዓለም አቀፉን ፍላጎት ይሸፍናል።

አሜሪካም ቢሆን በከፍተኛ ደረጃ አላት ከሚባለው ክምችት ውስጥ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን መጠቀም መጀመሯ በዓለም አቀፉ የነዳጅ ዋጋ መውረድ ላይም የራሱን አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደሩ ነው የሚነገረው። በዚሁ የነዳጅ ዋጋ ማሽቆልቆል አኮኖሚያቸው ክፉኛ እየተጎዱ ካሉት አገራት መካከል አንዷ ሩስያ ስተሆን ለአለም አቀፉ ነዳጅ መውደቅም አሜሪካንን ተጠያቂ አድርጋለች።

ከዩኩሬን ፖለቲካ ጋር በተያያዘ በተነሳው ውዝግብ ሩስያ በአሜሪካና በአውሮፓ ህብረት አባል አገራት ተደጋጋሚ ማዕቀቦች የተጣሉባት ሲሆን በቅርቡ አሜሪካ የራሷን የነዳጅ አቅርቦት መጠን ከፍ በማድረግ የኢምፖርት መጠኗን መቀነሷ ደግሞ ለአለም አቀፉ የነዳጅ ፍላጎት መቀነስ አይነተኛ ምክንያት ሆኗል። በዚህም ከማዕቀቡ በላይ ሩስያ አኮኖሚዋ ክፉኛ የተጎዳ መሆኑ ታውቋል።

በነዳጅ የወደፊት እጣ ፈንታ ብዙም ያልተማመኑት የሳዑዲ ባለስልጣናት የአገሪቱን ኢኮኖሚ ቀስ በቀስ ከነዳጅ ጥገኝነት ለማላቀቅ ረዘም ያለ ጊዜን እቅድ ነድፈው መንቀሳቀስ ከጀመሩ ዓመታት ተቆጥረዋል። በዚህም የሳዑዲ ባለሀብቶች ከራሷ ከሳውዲ ጀምሮ በተለያዩ አገራት ሰፊ የኢንቬስትመንት ስራን በማከናወን ላይ ናቸው። በየአሁኑ የዓለም አቀፉ የነዳጅ ዋጋ መውረድም የሳዑዲ አኮኖሚ ያን ያህል ፈተና ያልገጠመው መሆኑ ታውቋል። የአለም አቀፉ የነዳጅ ዋጋ ማሽቆልቆል ለነዳጅ ላኪ አገራት ከባድ ፈተና ቢሆንም ለነዳጅ ሸማች አገራት ግን በመልካም አጋጣሚነት እየታየ ነው።

# ስለ ሕገ መንግሥት ማሻሻያ...

በየደረጃው ሕዝቡ ከተወያየበት በኋላ አሁን በሥራ ላይ ያለው ህገመንግስት ህዳር 29 ቀን 1987 ዓ.ም ሊጸድቅ እንደቻለ ከፌዴሬሽን ምክርቤት ያገኘነው መረጃ ይጠቅሳል፡፡

የኢትዮጵያ ሕገመንግስት መሰረታዊ የሚባሉ መብትና ነጻነቶችን በማኅናጸፋ በብዙዎች ዘንድ የሚወደስ ነው፡፡ ይሁንና መብትና ነጻነቶች መደንገጋቸው ብቻውን ነጻነቶቹን አያመጣም፡፡ የሕገመንግስቱ ድንጋጌዎች በማወቅም ባለማወቅም ተጥሰው ሲገኙ ሊያስተካክል የሚችል ሥርዓት መዘርጋት ይኖርበታል፡፡ ለሕገመንግስቱ መከበር ዋስትና ከሚሰጡ ሥርዓቶች አንዱ ደግሞ የፍትህ ሥርዓቱ መሆኑ ይጠቀሳል፡፡

## ሕገ መንግሥቱን ማሻሻል ይቻላልን

የኢፌዲሪ ሕገመንግሥት ከጸደቀ 20 ዓመቱን ደፍኗል፡፡ ወቅት የሚፈጥራቸው አዳዲስ ክስተቶችና አስተሳሰቦች ለማካተት እንዲሁም በአንዳንድ ወገኖች የሚቀርቡ ቅሬታዎች አስፈላጊነት በመመርመር ማሻሻል የሚቻልበት ዕድል ዝግ አይደለም፡፡ የኢፌዲሪ ሕገመንግሥት ማሻሻያን በሚመለከት የሚለው አለ፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሥርዓት የፌዴራል ሥርዓቶች ጠቅላላ መርህን በመከተል የሕገ መንግሥትን መሻሻል በተመለከተ በአንቀጽ 104 እና 105 ተደንግጎ ይገኛል፡፡ የሕገ መንግሥቱን አንቀጾች የማሻሻል ሀሳብ ከፌዴራል መንግሥትም ሆነ ከክልል መንግሥት ሕግ አውጪ አካላት ሊመነጭ ይችላል፡፡ ከክልል መንግሥታት የሚመነጭ ከሆነ የሕገ መንግሥቱን ማሻሻያ ሀሳብ ከፌዴሬሽኑ አባል ክልሎች ውስጥ አንድ ሦስተኛው የክልል ምክር ቤቶች በድምጽ ብልጫ የደገፉት መሆን ይኖርበታል፡፡ ከፌዴራል መንግሥት የሚመነጭ ሲሆን፤ የሕገ መንግሥት ማሻሻያ ሀሳብ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምጽ የደገፈው እንዲሁም የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምጽ የደገፈው መሆን ይኖርበታል፡፡ ከዚህ በኋላ ነው የሕገ መንግሥት ማሻሻያ ሀሳብ ለውይይትና ለውሳኔ ለመላው ሕዝብና የሕገ መንግሥቱ መሻሻል ለሚመለከታቸው ክፍሎች የሚቀርበው፡፡

ሕገ መንግሥታችን የሕገ መንግሥት መሻሻል ሂደትን በሁለት ከፍሎ የሚያይ ሲሆን፤ አንደኛው የሕገ መንግሥት መሻሻል በሕገ መንግሥቱ ምዕራፍ ሦስት የተዘረዘሩትን

**ሁለተኛው የሕገ መንግሥት መሻሻል ሂደት በምዕራፍ ሦስት የተዘረዘሩትን መብቶችና ነፃነቶችን በሙሉ ያጠቃልላል። በተጨማሪም አንቀጽ 104ን የሚሸፍን ነው**

መብቶችና ነፃነቶችን እንዲሁም አንቀጽ 104ን የማይመለከት የሕገ መንግሥት መሻሻል ሂደት ነው፡፡ ይህን መደበኛ የሕገ መንግሥት መሻሻል ሂደት ልንለው እንችላለን፡፡ ሁለተኛው የሕገ መንግሥት መሻሻል ሂደት በምዕራፍ ሦስት የተዘረዘሩትን መብቶችና ነፃነቶችን በሙሉ ያጠቃልላል፡፡ በተጨማሪም አንቀጽ 104ን የሚሸፍን ነው፡፡ ይኸኛው ልዩ የሕገ መንግሥት መሻሻል ሂደት ልንለው እንችላለን፤ ልዩ የሕገ መንግሥት መሻሻል ሂደት ከመደበኛው የሚለየው ሥርዓቱ የድምጽ ሰጪውን ቁጥር ከፍ በማድረጉ ነው፡፡ ይህንንም ያደረገበት ምክንያት መብቶችና ነፃነቶች በቀላሉ እንዳይሸረሸሩ ነው፡፡

መደበኛ የሕገ መንግሥት መሻሻል ሂደት ከሕገ መንግሥት ማሻሻያ ሀሳብ ማመንጨት ተነስቶ ውሳኔ የሚያገኘው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት በጋራ ስብሰባ በሁለት ሦስተኛው ድምጽ የቀረበውን ማሻሻያ ሲያፀድቁና ከፌዴሬሽኑ አባል ክልሎች ምክር ቤቶች ውስጥ የ2/3ኛ ክልሎች ምክር ቤቶች በድምጽ ብልጫ የቀረበውን ማሻሻያ ሲያፀድቁት ነው፡፡

መብቶችና ነፃነቶችን እንዲሁም የሕገ መንግሥት ማሻሻያ ሃሳብን ማመንጨት የሚመለከት ልዩ የሕገ መንግሥት መሻሻል ሂደት ሁሉም የፌዴሬሽኑ አባል ክልሎች ምክር ቤቶች የቀረበውን ማሻሻያ በድምጽ ብልጫ ማጽደቅ ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት እያንዳንዳቸው የቀረበውን ማሻሻያ በሁለት ሦስተኛ ድምጽ ሲያፀድቁት ነው፡፡■

# ፍቺና የንብረት ክፍፍል...

ላይ እኩል መብትና እኩል ድርሻ አላቸው፡፡ ቤቶቹ በተለያየ ከተሞች እንደመገኘታቸው ዋጋቸው እንደሚለያይ መገመት አይከብድም፡፡ አሰራራቸው ያሉበት ልዩ ቦታም ዋጋቸው ላይ የራሱ አስተዋፅኦ አለው፡፡ ተከራካሪዎች ቢስማሙ ኖሮ ልዩነቶቹ ቢኖሩም በስምምነት መካፈል ይችሉ ነበር፡፡ ካልተስማሙ ግን ሕጉን መሰረት በማድረግ ማከፋፈል ግድ ነው፡፡

የበለጠ በንብረቱ የመጠቀም ሁኔታ መሰረት በማድረግ የሥር ፍ/ቤት የሀዋሳው ቤት ለሲ/ር አስቴር እንዲሰጥ መወሰኑ የሕግ መሰረት የሌለውና ትክክለኛ ያልሆነ ክፍፍል ነው፡፡ በመሆኑም በቅድሚያ ሁለቱ ቤቶች የገበያ ዋጋ እንዲታወቅ ማድረግ ከዚያም ተፋቺዎቹ በገበያ ዋጋው መሰረት በአይነት ለመከፋፈል ከተስማሙ የበለጠ ዋጋ ያለውን ቤት የሚወስደው ልዩነቱን እንዲያካክስ ማድረግ፣ ይህ ካልተቻለ ደግሞ በመጨረሻው አማራጭ ቤቶቹ ተሸጠው የሚገኘውን ገንዘብ እኩል እንዲካፈሉ ማድረግ ነበረበት፡፡ በማለት የሰር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ ሽሮ በትክክለኛው ከላይ በተጠቀሰው አግባብ እንዲካፈሉ ወስኗል፡፡

5.2 በእጣ መካፈል፡- የወ/ሮ ጥሩ ወርቅና የአቶ ታፈሰን ሁለት የጋራ ቤቶች በእጣ እንዲከፋፈሉ የተሰጠውን ውሳኔ ደግሞ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር በሰ/መ/ቁ 61788 ሰኔ 14/2003 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ የደቡብ ክልልም ሆነ በፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ በፍቺ ጊዜ የጋራ ንብረትን ተፋቺዎቹ ካልተስማሙ በስተቀር ፍ/ቤቱ በራሱ ተነሳሽነት በእጣ ማካፈል እንደማይችል ገልጿል፡፡ የዕጣ ክፍፍልን አግባብነት ያላቸው የቤተሰብ ሕጉ አንቀፅች በአማራጭነት አላስቀመጡትም፡፡ ስለዚህ የስር ፍ/ቤቶች ተፋቺዎች በአይነት እኩል ለመካፈል ካልተስማሙ ወደ ቀጣዮቹ የስምምነት ሽያጭና የሀራጅ ሽያጭ አማራጮች ማለፍ ነበረባቸው፡፡

5.3 ከጋብቻ በኋላ የታደሰው ንብረት፡- ይህ ነባር የአንዱ ተጋቢ ንብረትና የጋራ ንብረቶች የክፍፍል መርህ ላይ በወ/ሮ አየለችና በአቶ በላቸው መካከል የነበረው ክርክር በሰ/መ/ቁ 45207 ሰኔ 16/2002 ውሳኔ አግኝቷል፡፡ በጉለሌ የሚገኘውን ቤት በተመለከተ ቤቱ የእድሳት ፈቃድ በወ/ሮ አየለችና በልጆቻቸው የወጣ፣ ቤቱም በስማቸው የተመዘገበ ነው፡፡ ቤቱ የታደሰው ወ/ሮ አየለችና አቶ በላቸው ተጋብተው በነበሩበት መሆኑ ብቻ የጋራ አያደርገውም፡፡ በቤተሰብ ሕጉ አንቀፅ 57 ተጋቢው ጋብቻው ሲፈፀም የነበረው ንብረት የግል ሆኖ ይቀጥላል ይላል፡፡ በሌላ በኩል ስለንብረታቸውም ተጋቢዎች በአንቀፅ 42(1) መሰረት በውል መስማማት ቢችሉም ቤቱ የጋራ እንዲሆን ያደረጉት ስምምነት የለም፡፡ ስለዚህ የጋራ መባሉ አለአግባብ ነው፡፡ አቶ በላቸው ለቤቱ እድሳት ገንዘብ ስላወጡ የወጣው ወጪ ከጋራ ሀብት በመሆኑ 50 በመቶ ብቻ ሊከፈላቸው ይገባል፡፡ ሌሎቹ ብሎኬት ማምረቻ የገበያ ማዕከል የሱሉልታ ኢንቨስትመንትን በተመለከተም ወ/ሮ አየለች አልስማማም እያሉ አቶ በላቸው ግማሹን ከፍለው እንዲያስቀሩ መወሰኑ የእኩልነትና የክፍፍል መርህን ያላገናዘበ ነው፡፡ ተፋቺዎቹ ካልተስማሙ ሕጉ ባስቀመጠው ስርዓት በአይነት መከፋፈል ከተቻለ በአይነት ይህ ካልተቻለ በአንቀፅ 42 መሰረት ንብረቶቹ ተሸጠው የሚገኘውን ገንዘብ ወ/ሮ አየለችና አቶ በላቸው እኩል እንዲካፈሉ ወስኖ የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ አሻሽሎታል፡፡


# ክፍት የሥራ መደብ ማስታወቂያ

የሚድሮክ ኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ግሩፕ አባል የሆነው ሬይንቦ ኤክስክሉሲቭ የመኪና ኪራይና አስጎብኝ አገልግሎት ኃ.የተ.የግል.ማህበር ከዚህ በታች በተገለፀዉ ክፍት የሥራ መደብ መስፈርቱን የሚያሟሉ አመልካቾችን አወዳድሮ ለመቅጠር ይፈልጋል፡፡

| ተራ.ቁ | የሥራ መደቡ መጠሪያ | ፆታ | የተፈላጊ የትምህርት ደረጃ | ተፈላጊ የሥራ ልምድ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ቪኸክል ኦፕሬተር (የመኪናዎች አሽከርካሪ) | አይለይም | በሙያዉ/ዋ 2 ዓመትና ከዚያ በላይ በተመሳሳይ የሰራ/ች | 10/12ኛ ክፍል እና ከዚያ በላይ ያጠናቀቀ እና ቢያንስ 3ኛደረጃ መንጃ ፈቃድ ያለዉ/ያላት |

ደመወዝ------------------- በስምምነት
ብዛት --------------------12
የቅጥር ሁኔታ------------- በቋሚነትና በጊዜያዊነት
የሥራ ቦታ ----------------- አዲስ አበባ
መስፈርቱን የሚያሟሉ አመልካቾች የትምህርትና የሥራ ልምድ ዋናዉና የማይመለስ ፎቶ ኮፒ በመያዝ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 7 ተከታታይ የሥራ ቀናት ቅዳሜ ጠዋት ጨምሮ በኩባንያዉ ዋና መስሪያ ቤት በአካል በመገኘት መመዝገብ ይችላሉ፡፡
<u>አድራሻ፡-</u> አዲስ አበባ ከአፍሪካ ሕብረት ወረድ ብሎ ሳርቤት ፑሽኪን አደባባይ በሚገኘው የሰው ኃይል አገልግሎት ክፍል

ለበለጠ መረጃ ስልክ ቁጥር 011372-26-38 ደውለው መጠየቅ ይችላሉ፡፡
ሬይንቦ ኤክስክሉሲቭ የመኪና ኪራይና አስጎብኝ አገልግሎት ኃ.የተ.የግል.ማህበር

በቀንዲት ተሾመ

# ሜሲና ሮናልዶ በሪከርዶች ተፋጠዋል




የሊዮኔል ሜሲና ክርስቲያኖ ሮናልዶ ንጽጽር አሁንም መቋጫ አላገኘም፡፡ ንጽጽሩ ከአመት አልፎ በየወሩ በየግላቸው የሚያስመዘግቡት ውጤትና ብቃት መነጻጸር ጀምሮ ነበር፡፡ አሁን ደግሞ ንጽጽራቸው በየሳምንቱ የሆነበት ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ ሁለቱ ኮከቦች በየሳምንቱ ከቡድናቸው ጋር የሚያስመዘግቡት ውጤት በግላቸው አዳዲስ ሪከርዶችን እንዲያስመዘግቡ አድርጓቸዋል፡፡ ሪከርዶቻቸው እየተነጻጸሩም አንዳቸውን ከአንዳቸው መብለጣቸውን ለማሳያነት እየቀረቡ ነው፡፡

የሁለቱ ተጫዋቾች ስም ተያይዞ የሚነሳባቸው አጋጣሚዎች እንደቀድሞው በወራት ሳይሆን በየሳምንቱ እየተከሰቱ መሆናቸው አስገራሚ ሆኗል፡፡ አንደኛው ሲናገር ሌላኛው መልስ መስጠቱ የማይቀር ሆኗል፡፡ በስፔን ላሊጋ በሳምንቱ መጨረሻ ቀናትም ይኸው ነው የታየው፡፡ ቅዳሜ እለት ሮናልዶ ሀትሪክ ሰርቶ የአለም ኮከብነቱን ሲያረጋግጥ፣ እሁድ እለት ደግሞ ሜሲ ሶስት ግቦችን አስቆጥሮ ከሮናልዶ እንደማያንስ መልስ ሰጥቷል፡፡

ባለፉት ሶስት ሳምንታት የሊዮኔል ሜሲ ስም ነበር በብዛት ሲጠራ የከረመው፡፡ አርጀንቲናዊው የፊት መስመር ተጫዋች በስፔን የምንግዜም ግብ አስቆጣሪነት ክብረወሰንን በመስበር የተጎናጸፈውን ታላቅ ክብረወሰን የአለም መነጋገሪያ አድርጎት ነበር፡፡ ተቀናቃኙን ሮናልዶን ለመብለጡም ማነፃጸሪያ ሆኖ ቀርቦ ነበር፡፡ ፖርቱጋላዊው አጥቂ ሮናልዶ ደግሞ በዚያው ሰሞን ግቦችን ከማስቆጠር ይልቅ ለቡድን ጓደኞቹ ለግብነት ኳስን አመቻችቶ በማቀበል ከሜሲ ብቻ ሳይሆን ከየትኛውም የላሊጋ ተጫዋች የበለጠ ነበር፡፡ ለቡድን ጓደኞቹ ግብ መሆን የቻሉ ስምንት የተመቻቹ ኳሶችን አቀብሏል፡፡ በዚህም ሮናልዶ ራስ ወዳድ ያልሆነና ብስለት ላይ የደረሰ ተጫዋች መሆኑን ያረጋገጠበት ነው ተብሎ ተወድሷል፡፡

ሊዮኔል ሜሲ በዚህ ወር የስፔንን የምንግዜም ግብ አስቆጣሪነት ክብረወሰንን ለመጋራትና ለመስበር የቻለው በሁለት ጨዋታዎች ላይ ነበር፡፡ ሮናልዶ ግን በአንድ ጨዋታ በቅዳሜ እለቱ ሁለት ክብረወሰኖችን የሰበረው፡፡ ይህም የሁለቱን ተጫዋቾች ብቃት መለኪያ ሆኖ ቀርቧል፡፡

ከቅዳሜው ጨዋታ በፊት ክርስቲያኖ ሮናልዶ በ197 ጨዋታዎች 177 ግቦች ነበሩት፡፡ ሪያል ማድሪድ ሪያል ቫልካኖን ሲያሸንፍ ሶስት ግቦችን አስቆጥሮ በ198 ጨዋታዎች 200 ግቦች ባለቤት መሆን ችሏል፡፡ 200 ግቦችን ላይ ለመድረስ አጭር ጊዜ የወሰደበት ተጫዋች ሆኗል፡፡ ከሜሲ የበለጠም በፍጥነት ብዙ ግቦችን በማስቆጠር ብልጫ አለው፡፡ ሜሲን ብቻ ሳይሆን ቀድሞ 200 ግቦችን በማስቆጠር ክብረወሰኑን ይዘው የነበሩትን አልፍሬድ ስቴፋኖና ቴልሞ ዛራንም ጭምር ነው የበለጠው፡፡ ዲ ስቴፋኖ 200 ግቦችን ያስቆጠረው በ250 ጨዋታዎች ሲሆን፣ ቴልሞ ዛራ ደግሞ በ219 ጨዋታዎች ላይ ነበር፡፡

ሊዮኔል ሜሲ ሰሞኑን 200 ግብ በማስቆጠር ከሁለት አስርት አመታት በላይ የቆየውን ክብረወሰን ለመስበር የቻለው በ235 ጨዋታዎች በመሰለፍ ነበር፡፡ ሮናልዶ ግን 200 ግቦች ላይ የመድረስ ስኬትን ያገኘው በ178 ጨዋታዎች ላይ ነው፡፡

የሚነጻጸሩበት ነጥብ የማይጠፋቸው ሮናልዶና ሜሲ በሚያስቆጥሯቸው አጠቃላይ ግቦች ብቻ ሳይሆን በአንድ ጨዋታ ባስቆጠሯቸው ሶስት ግቦች መጠንም ነው፡፡ ባለፈው ሳምንት መጨረሻም ሁለቱም ክለቦቻቸው ሲያሸንፉ ሶስት ሶስት ግቦችን አስቆጥረው ለሌላ ንጽጽር ቀርበዋል፡፡ በአጠቃላይ ያላቸው የሀትሪክ ብዛትም ለስሌት ቀርቧል፡፡

የክርስቲያኖ ሮናልዶ ቅዳሜ እለት ያስቆጠራት ሶስተኛዋ ግብ ከቡድኑ በላይ ለእሱ በጣም ጠቃሚ ነበረች፡፡ ከማርሴሎ በአጭሩ የተሻገረችለት ኳስ ከመረብ ሲያሳርፋት በጨዋታው ሀትሪክ እንዲሰራ ከማስቻልም በላይ በአጠቃላይ በስፔን ሊግ 23ኛው ሀትሪክ ሆናለታለች፡፡ ይህም በስፔን ብዙ ሀትሪክ የሰራ ተጫዋች በመባል ክብረወሰንኑን ለብቻው እንዲይዝ አድርጎታል፡፡ ቀድሞ 22 ጊዜ ሀትሪክ በመስራት ክብረወሰኑንን ከዛራ እና ዲ ስቴፋኖ ጋር በመጋራት መቆየቱ ይታወሳል፡፡

ሊዮኔል ሜሲ ደግሞ 21 ጊዜ ሀትሪክ ለመስራት አራት የውድድር አመት ፈጅቶበታል፡፡ እሁድ እለት ኢስፓኞል ላይ ሀትሪክ ሲሰራ ዘንድሮ ለሶስተኛ ጊዜ ነው፡፡ በስፔን ሊግም የግቦቹ መጠን 13 ደርሷል፡፡ ሮናልዶ ደግሞ በዚህ አመት አራት ጊዜ ሀትሪክ የሰራ ሲሆን፣ በላ ሊጋው በ14 ጨዋታዎች ተሰልፎ 23 ግቦችን ለሪያል ማድሪድ አስቆጥሯል፡፡ ይህም ሊዮኔል ሜሲ፣ ሉዊስ ሱዋሬዝና ኔይማር በጋራ ለባርሴሎና ካስቆጠሯቸው አጠቃላይ 24 ግቦች በአንድ ብቻ ያነሰ ነው፡፡

ሁለቱ ተጫዋቾች ቅዳሜና እሁድ በተሰለፉባቸው ጨዋታዎች ሀትሪክ ካስቆጠሩ በኋላ የተለያዩ አድናቆቶች ጎርፈውላቸዋል፡፡ የሁለቱም የቡድን አጋሮች የዘንድሮው የፊፋ የአለም ኮከብ ተጫዋችነት ሽልማትን ለራሳቸው ክለብ ተጫዋች መስጠት እንዳለበት ተናግረዋል፡፡

ዘንድሮ ሪያል ማድሪድን የተቀላቀለው ኮሎምቢያዊው አጥቂ ሀማዝ ሮድሪጌዝ የክለብ ጓደኛው "ሮናልዶ የአለም ኮከብነት ለሶስተኛ ጊዜ እንደሚመረጥ ምንም ጥርጥር የለኝም" ብሏል፡፡ የቡድኑ አምበል ተከላካዩ ሰርጂዮ ራሞስ በበኩሉ "እባካችሁ እስቲ ሮናልዶን የሚገልጸው አዲስ ቃል ፈልጉ" በማለት ፖርቱጋላዊውን ተጫዋች የሚገልጽበት የአድናቆት ቃል ማግዐት እንደተቸገረ ተናግሯል፡፡ ሮናልዶ በሪያል ማድሪድ ለቡድናችን ብቻ ሳይሆን በግሉም የሚያስመዘግባቸው ስኬቶች በጣም አስገራሚ ናቸው፡፡ ስለሱ የሚናገሩ ቁጥሮች የእርሱን ምርጥነት የሚያስረዱ ናቸው" ሲልም ስፔናዊው ተከላካይ ለሮናልዶ ያለውን አድናቆት ገልጿል፡፡

የሊዮኔል ሜሲም የቡድን ጓደኞች በበኩላቸው የአለም ኮከብነት ዘንድሮ ሜሲን የሚነጥቀው ማንም አይኖርም እያሉ ነው፡፡ ብራዚላዊው ኔይማር እርሱ አሁንም የአለማችን ቁጥር አንድ ተጫዋች ነው፡፡ ምትሀተኛ ያስባለው ችሎታውን የሚበልጥ ተጫዋች የለም ሲል ሜሲን አሞካሽቶታ፡፡ ሰርጂዮ ቡስኬት ደግሞ "ክርስቲያኖ ሮናልዶ የወቅቱ የአለም ኮከብ ተጫዋች ቢሆንም ዘንድሮ ግን ሜሲ ሽልማቱን መውሰድ የሚችልበት ብቃቱን እያሳየ እንደሚገኝ ማመን አለብን" ብሏል፡፡■

## ቬንገር ከደጋፊዎች ተቃውሞ ገጥሟቸዋል

በእንግሊዝ ፕሪሚየር ሊግ ቅዳሜ እለት አርሴናል በስቶክ ሲቲ 3ለ2 ከተሸነፈ በኋላ አሰልጣኝ አርሰን ቬንገር ከደጋፊዎች ከፍተኛ ተቃውሞ ገጥሟቸዋል፡፡ ወደ ጋዜጣዊ መግለጫ ክፍል ሲያመሩም ሆነ ከስታዲየሙ ሲወጡ ደጋፊዎች መንገዳቸውን ዘግተውባቸው ቁጣቸውን አውርደውባቸዋል፡፡ ፈረንሳዊው አሰልጣኝ ግን ከደጋፊዎች በደረሰባቸው ተቃውሞ እንዳልተበሳጩና አሁን ስለ ቆይታቸው የሚወራበት ጊዜ እንዳልሆነ ነው የተናገሩት፡፡

ስቶክ ሲቲ በመጀመሪያው የጨዋታ ክፍለ ጊዜ በተከታታይ ሶስት ግቦችን ማስቆጠሩ ያበሳጫቸው ደጋፊዎች አሰልጣኝ አርሴን ቬንገር ክለቡን መልቀቅ እንዳለባቸው በቁጣ ተናግረዋል፡፡ በሊጉ ዘንድሮው ለአራተኛነት የሚታገለውን አርሴናልን ማየት አንፈለግም ሲሉም ተሰምተዋል፡፡

አሰልጣኝ አርሰን ቬንገር በትናንቱ የቻምፒየንስ ሊግ ጨዋታ በፊት በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫዎች ቁጣቸውን መግለጻቸው መብታቸው እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ ይሁንና የእሳቸውን የክለብ ቆይታም ሆነ የቡድናቸውን የዋንጫ ተፎካካሪነት የሚወሰንበት ጊዜ አሁን እንዳልሆነ ነው የገለጹት፡፡

"የፕሪሚየር ሊጉ እያንዳንዱ ጨዋታ በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ እኛም መመዘን ያለብን በውድድር አመቱ መጨረሻ እንጂ በእያንዳንዱ ጨዋታ ውጤት መሆን የለበት፡፡ በስቶክ ሲቲ በመሸነፋችን በጣም አዝነናል፡፡ ለእኛ በጣም የሚጠቅመን ግን ቀጣይ ጨዋታችን ነው፡፡ ቀጣይ ጨዋታዎችን ለማሸነፍ ጠንክረን እንሰራለን"■

# ኃይሌ በሲንጋፖር 10ኪሎ ሜትርን በሦስተኛነት አጠናቀቀ

አትሌት ኃይሌ ገብረስላሴ አሁንም ከሩጫ መድረክ አልርቅም እንዳለ ነው:: ከሁለት ወር በፊት በስኮትላንድ የ10 ኪሎ ሜትር ሩጫን አቋርጦ ሲወጣ ከእንግዲህ የመወዳደር አቅሙን ጨርሷል የሚሉ አስተያየቶች ተሰንዝረውበት ነበር:: ኢትዮጵያዊው አትሌት ግን በቀላሉ እጅ አልሰጥም ብሏል:: እሁድ እለት ሲንጋፖር ላይ በተካሄደው የ10 ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ ሩጫ ተወዳድሮ በሶስተኝነት አጠናቋል:: በቀጣዩ አመት ደግሞ የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ እንደሚዘጋጅ ተናግሯል::

ኃይሌ የ10 ኪሎ ሜትር ርቀቱን በሶስተኛነት ሲያጠናቅቅ ያስመዘገበው ሰአት 30 ደቂቃ ነበር:: ውድድሩን ኬንያዊው ሶሎሞን ኪፕዬጎ ኪተር በ29 ደቂቃ ከ47 ሰከንድ በመግባት አሸንፏል:: እሱን ተከትሎ በሁለተኛነት የገባው ሌላው ኬንያዊ ቶማስ ማሪቲም ደግሞ ርቀቱን 29 ደቂቃ ከ53 ሰከንዶች ጨርሷል::

የ41 አመቱ አትሌት ኃይሌ ከብዙ ወጣት አትሌቶች ጋር ተፎካክሮ ያስመዘገበው ሰአትና ያገኘው ደረጃ አድናቆትን አስገኝቶለታል:: ቀደም ሲል በርቀቱ የነበረው ምርጥ ሰአት 27 ደቂቃ ከሰከንድ ሲሆን እ.ኤ.አ. በ2002 ላይ ያስመዘገበው እንደነበር ይታወሳል::

ከውድድሩ በኋላ አስተያየቱን የሰጠው ኃይሌ "ማናጀሬ የነገረኝ በውድድሩ ላይ የሀገር ውስጥ አትሌቶች ብቻ እንደሚሳተፉ እንጂ ኬንያውያን እንደሚኖሩ አይደለም:: ሆኖም ባገኘሁት ውጤትና ባስመዘገብኩት ሰአት ደስተኛ ነኝ:: በቀጣዩ አመት በደንብ ተዘጋጅቼ እመጣለሁ" ብሏል::

በእለቱ የማራቶን ውድድርም የተካሄደ ሲሆን በሴቶች መካከል በተካሄደው ፉክክር ኢትዮጵያዊቷ ዋጋነሽ አማረ አሸንፋለች:: ርቀቱንም 2 ሰአት ከ46 ደቂቃ ከ54 ሰከንድ ስትጨርስ ኬንያዊያኑ ኤልሳቤዝ ቼምዌኖ እና ፖሊን ዋንጉዊን ሁለተኛና ሶስተኛ ሆነው ገብተዋል:: የወንዶቹን ፉክክር ኬንያውያን ከአንድ እስከ ሶስት ያለውን ደረጃ ይዘው በመግባት የበላይነታቸውን አሳይተዋል::■

# የጎትዝ የአለም ዋንጫ ጫማ በጨረታ ተሸጠ



የጀርመን ብሔራዊ ቡድን በብራዚሉ የአለም ዋንጫ ሻምፒዮን እንዲሆን ያስቻለችዋን ግብ ያስቆጠረው የማሪዮ ጎትዝ የግራ እግር ጫማ በጨረታ ተሸጠ:: የባየር ሙኒኩ የፊት መስመር ተጫዋች በአለም ዋንጫ ፍጻሜ አርጀንቲና ላይ ብቸኛዋን ግብ ያስቆጠረባት የግራ እግሩ ጫማ በጨረታ 2 ሚሊዮን ፓውንድ ተሽጦ በጀርመን ህጻናትን ለሚረዳ የበጎ አድራጊ ድርጅት ተሰጥቷል:: ይህም የእግር ኳስን ሰላማዊ ገጽታና መልካም ስጦታነቱን የሚያስረዳ ነው ተብሏል::

ማሪዮ ጎትዝ የአርጀንቲና ግብ ጠባቂን ሮሜሩን አልፏ ከመረብ ያረፈችዋን ኳስ የመታበትን ጫማውን ከአለም ዋንጫው በኋላ ምንም ሳይጠርገውና ሳያጥበው፣ ላዩ ላይ ያሉትንም ሳሮች እንኳ ሳይነካ በመኖሪያ ቤቱ በጥንቃቄ አስቀምጦ እንዳቆየው ተናግሯል::■

# አል አህሊ የካፍ ኮንፌዴሬሽን ዋንጫን አሸነፈ

የግብጹ አል አህሊ የ2014 የአፍሪካ ኮንፌዴሬሽን ዋንጫን ለመጀመሪያ ጊዜ አሸነፈ:: ክለቡ በአፍሪካ ምድር በርካታ ዋንጫዎችን በመሰብሰብ የያዘው ክብረወሰን ላይ የሚደርስበት አልተገኘም::

ቅዳሜ እለት ካይሮ ላይ የ2014 የካፍ ኮንፌዴሬሽን ዋንጫ ፍጻሜ ጨዋታ በግብጹ አል አህሊና በኮትዲቯሩ ሴዌ ስፖርት መካከል ሲካሄድ ከ25ሺ በላይ ግብጻውያን በስታዲየም ተገኝተው ነበር:: በመጀመሪያው ጨዋታ 2ለ1 የተሸነፈው አል አህሊ ጨዋታው ሊጠናቀቅ ሲል ኢማድ ሞቴብ ባስቆጠራት ብቸኛ ግብ ከሜዳው ውጪ ባስቆጠረ በሚለው ህግ ተጠቃሚ ሆኖ በድርሶ መልስ 2ለ2 ውጤት ሻምፒዮን መሆን ችሏል:: ከአንድ አመት በኋላ ስታዲየም መግባት የተፈቀደላቸው ደጋፊዎቹ ከተማዋን በደስታ ሲዞሩ ማምሸታቸው ታውቋል::

አል አህሊ ቅዳሜ እለት የኮንፌዴሬሽኑን ዋንጫ ሲያነሳ በአፍሪካ ምድር ያገኛቸው ዋንጫዎች ብዛት 19 ደርሰዋል:: የቻምፒየንስ 8 ሊግ፣ የካፍ ሱፐር ካፕ 6 እና 4 የአፍሪካ የአሸናፊዎች አሸናፊዎች ዋንጫዎችን መውሰዱ ይታወሳል:: ዘንድሮ ለመጀመሪያ ጊዜ በኮንፌደሬሽኑ ዋንጫ ያነሳ ሲሆን፣ አሰልጣኙ ሁዋን ካርሎስ ጋሪዶ የካፍን ዋንጫ ያነሱ የመጀመሪያው ስፔናዊ አሰልጣኝ አድርጓቸዋል::

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን አጥቂ ሳላዲን ሰኢድ በአል አህሊ የሚገኝ ቢሆንም ቢሆንም ከቀድሞ ክለቡ ከወዲ ዳግላ ጋር በዚህ አመት ኮንፌዴሬሽን ውድድር ላይ በመጫወቱ ለአል አህሊ ሊሰለፍ አልቻለም:: በአሁኑ ወቅትም ከደረሰበት ጉዳት በማገገም ላይ መሆኑ ታውቋል::■



# ደርባ ሲሚንቶ
# DERBA CEMENT



## ክቡራትና ክቡራን ደንበኞቻችን!

ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ላለፉት ጥቂት ወራት በጥገናና እድሳት ላይ ቆይቶ ሥራውን በማጠናቀቅ ወደ ሙሉ ምርታማነቱ ተመልሷል፡፡

የሲሚንቶን ዋጋ በማረጋጋት የሚታወቀው ፋብሪካችሁ እንደተለመደው ከፍ ያለ ጥራት ያላቸውን OPC እና PPC ሲሚንቶ በተለየ አደረጃጀት እደጃፋችሁ ድረስ ማድረሱን ከህዳር 29 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ የተለመደውን አገልግሎት መስጠት ጀምሯል፡፡

በዚህ አጋጣሚ በእድሳትና ጥገና ወቅት አብራችሁን ለቆያችሁት ደንበኞቻችን ወደር ለሌለው ትዕግሥታችሁ የደርባ ማኔጅመንትና ሠራተኞቹ ከፍ ያለና የከበረ ምስጋናቸውን ለእናንተ ለደንበኞቻቸው ያቀርባሉ!!

**“ለሁሉም ሥራ በሁሉም ሥፍራ ነገን ዛሬ እንስራ”**

**“ደርባ ሲሚንቶ”**